# መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ።

(ክለሳ.1.20020507)

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሰሎሞን ፡ በመንግሥቱ ፡ በረታ ፤ አምላኩም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ እጅግም ፡
አገነነው ።

2 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፥ ለሻለቃዎች ፥ ለመቶ ፡ አለቃዎችም ፥ ለፈራጆችም ፥ በእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡
ለነበሩ ፡ መሳፍንት ፡ ኹሉ ፥ ለአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ተናገረ ።

3 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሠራው ፡
የእግዚአብሔር ፡ መገናኛ ፡ ድንኳን ፡ በዚያ ፡ ነበረና ፡ በገባዖን ፡ ወዳለው ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃ ፡ ኼዱ ።

4 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ግን ፡ ዳዊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ድንኳን ፡ ተክሎለት ፡ ነበርና ፥ ዳዊት ፡ ከቂርያትይዓሪም ፡
ወዳዘጋጀለት ፡ ስፍራ ፡ አምጥቶት ፡ ነበር ።

5 ፤ የሆርም ፡ ልጅ ፡ የኡሪ ፡ ልጅ ፡ ባስልኤል ፡ የሠራው ፡ የናስ ፡ መሠዊያ ፡ በዚያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ፊት ፡
ነበረ ፤ ሰሎሞንም ፡ ጉባኤውም ፡ ይህን ፡ ይፈልጉት ፡ ነበር ።

6 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ወደናሱ ፡ መሠዊያ ፡
ወጣ ፥ በዚያም ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ።

7 ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ እግዚአብሔር ፦ ምን ፡ እንድሰጥኽ ፡ ለምነኝ ፡ ሲል ፡ ለሰሎሞን ፡ ተገለጠ ።

8 ፤ ሰሎሞንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለው ፦ ከአባቴ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ ምሕረት ፡ አድርገኻል ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡
አንግሠኸኛል ።

9 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ቍጥሩ ፡ እንደምድር ፡ ትቢያ ፡ በኾነው ፡ በብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡
አንግሠኸኛልና ፥ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠኸው ፡ ተስፋ ፡ ይጽና ።

10 ፤ አኹንም ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ እወጣና ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ስጠኝ ፤ ይህን ፡ በሚያኽል ፡
በዚህ ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ የለምና ።

11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰሎሞንን ፦ ይህ ፡ በልብኽ ፡ ነበረና ፥ ባለጠግነትንና ፡ ሀብትን ፡ ክብርንና ፡ የጠላቶችኽን ፡ ነፍስ ፡
ረዥምም ፡ ዕድሜን ፡ አልለመንኽምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ባነገሥኹኽ ፡ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ ትችል ፡ ዘንድ ፡
ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ለራስኽ ፡ ለምነኻልና ፥ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ሰጥቼኻለኹ ፤

12 ፤ ከአንተ ፡ በፊትም ፡ ከነበሩት ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ከሚነሡት ፡ ነገሥታት ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የሚመስልኽ ፡
እንዳይኖር ፡ ባለጠግነትንና ፡ ሀብትን ፡ ክብርንም ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለው ።

13 ፤ ሰሎሞንም ፡ በገባዖን ፡ ካለው ፡ ከኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ ከመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
መጣ ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

14 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሠረገላዎቹንና ፡ ፈረሰኛዎችን ፡ ሰበሰበ ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠረገላዎች ፥ ዐሥራ ፡
ኹለት ፡ ሺሕም ፡ ፈረሰኛዎች ፡ ነበሩት ፤ በሠረገላዎች ፡ ከተማዎችና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ።

15 ፤ ንጉሡም ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ እንዲበዛ ፡ አደረገው ፤ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፡ ብዛት ፡
በቈላ ፡ እንደሚበቅል ፡ ሾላ ፡ ኾነ ።

16 ፤ ሰሎሞንም ፡ ፈረሶችን ፡ ከግብጽና ፡ ከቀዌ ፡ አስመጣ ፤ የንጉሡም ፡ ነጋዴዎች ፡ በገንዘብ ፡ እየገዙ ፡ ከቀዌ ፡
ያመጧቸው ፡ ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

17 ፤ አንዱም ፡ ሠረገላ ፡ በስድስት ፡ መቶ ፥ አንዱም ፡ ፈረስ ፡ በመቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፡ ብር ፡ ከግብጽ ፡ ይወጣ ፡
ነበር ፤ እንዲሁም ፡ ለኬጢያውያንና ፡ ለሶርያ ፡ ነገሥታት ፡ ዅሉ ፡ በእጃቸው ፡ ያመጡላቸው ፡ ነበር ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፥ ለመንግሥቱም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ።

2 ፤ ሰሎሞንም ፡ የሚሸከሙትን ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፥ ከተራራዎችም ፡ የሚጠርቡትን ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፥ በእነርሱም ፡ ላይ ፡
የተሾሙትን ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ቈጠረ ።

3 ፤ ሰሎሞንም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ኪራም ፡ ላከ ፦ ከአባቴ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡
እንዳደረግኽ ፥ የሚቀመጥበትንም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ እንደ ፡ ሰደድኽለት ፥ እንዲሁ ፡ ለእኔ ፡
አድርግ ።

4 ፤ እንሆ ፥ ለእስራኤል ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ታዘዘው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የጣፋጩን ፡ ሽቱ ፡ ለማጠን ፥ የገጹንም ፡
ኅብስት ፡ ለማኖር ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ በጧትና ፡ በማታ ፡ በሰንበታቱም ፡ በመባቻዎቹም ፡ በአምላካችንም ፡
በእግዚአብሔር ፡ በዓላት ፡ ለማቅረብ ፡ ለአምላኬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ እሠራና ፡ እቀድስ ፡ ዘንድ ፡ ዐሰብኹ ።

5 ፤ አምላካችንም ፡ ከአማልክት ፡ ዅሉ ፡ በላይ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ የምሠራው ፡ ቤት ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰማይና ፡ ከሰማያት ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሰማይ ፡ ይይዘው ፡ ዘንድ ፡ አይችልምና ፡ ለርሱ ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡
ዘንድ ፡ ማን ፡ ይችላል ፦ በፊቱ ፡ ዕጣን ፡ ከማጠን ፡ በቀር ፡ ቤት ፡ እሠራለት ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፦

7 ፤ አኹንም ፡ አባቴ ፡ ዳዊት ፡ ካዘጋጃቸው ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ካሉት ፡ ብልኀተኞች ፡ ጋራ ፡
የሚኾን ፥ ወርቁንና ፡ ብሩን ፥ ናሱንና ፡ ብረቱን ፥ ሐምራዊውንና ፡ ቀዩን ፡ ሰማያዊውንም ፡ ግምጃ ፡ የሚሠራ ፥ ቅርጽንም ፡
የሚያውቅ ፡ ብልኀተኛ ፡ ሰው ፡ ላክልኝ ።

8 ፤ ደግሞም ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ከሊባኖስ ፡ ዕንጨት ፡ መቍረጥ ፡ እንዲያውቁ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹና ፡ ከሊባኖስ ፡ የዝግባና ፡
የጥድ ፡ የሰንደልም ፡ ዕንጨት ፡ ስደድልኝ ።

9 ፤ የምሠራውም ፡ ቤት ፡ እጅግ ፡ ታላቅና ፡ ድንቅ ፡ ይኾናልና ፥ ብዙ ፡ ዕንጨት ፡ ያዘጋጁልኝ ፡
ዘንድ ፥ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ ይኾናሉ ።

10 ፤ እንሆም ፥ ዕንጨቱን ፡ ለሚቈርጡ ፡ ለባሪያዎችኽ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ የተበጠረ ፡ ስንዴ ፥ ኻያ ፡
ሺሕም ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፥ ኻያ ፡ ሺሕም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ ኻያ ፡ ሺሕም ፡ የባዶስ ፡
መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡ እሰጣለኹ ።

11 ፤ የጢሮስ ፡ ንጉሥም ፡ ኪራም ፦ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ወዷልና ፥ በላያቸው ፡ አነገሠኽ ፡ ብሎ ፡ ለሰሎሞን ፡
መልእክት ፡ ላከ ።

12 ፤ ኪራምም ፡ ደግሞ ፡ አለ ፦ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ለመንግሥቱም ፡ ቤት ፡
ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ጥበበኛና ፡ ብልኀተኛ ፡ አስተዋይም ፡ ልጅ ፡ ለንጉሡ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔር ፡ ቡሩክ ፡ ይኹን ።

13 ፤ አኹንም ፡ ከብልኀተኛዎችኽ ፡ ጋራ ፡ ከጌታዬም ፡ ከአባትኽ ፡ ከዳዊት ፡ ብልኀተኛዎች ፡ ጋራ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡
ኪራምአቢ ፡ የሚባል ፡ ብልኀተኛና ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ሰድጄልኻለኹ ።

14 ፤ እናቱ ፡ ከዳን ፡ ልጆች ፡ ናት ፥ አባቱም ፡ የጢሮስ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ወርቁንና ፡ ብሩንም ፥ ናሱንና ፡
ብረቱን ፥ ድንጋይንና ፡ ዕንጨቱን ፥ ሐምራዊውንና ፡ ሰማያዊውን ፡ ቀዩንም ፡ ግምጃ ፥ ጥሩውንም ፡ በፍታ ፡ ይሠራ ፡
ዘንድ ፥ ቅርጽም ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ያውቃል ።

15 ፤ አኹንም ፡ ጌታዬ ፡ የተናገረውን ፡ ስንዴውንና ፡ ገብሱን ፡ ዘይቱንና ፡ የወይን ፡ ጠጁን ፡ ወደ ፡ ባሪያዎቹ ፡ ይስደድ ፤

16 ፤ እኛም ፡ ከሊባኖስ ፡ የምትሻውን ፡ ያኽል ፡ ዕንጨት ፡ እንቈርጣለን ፥ በታንኳም ፡ አድርገን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ወዳንተ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ እንሰዳለን ፤ አንተም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ታስወስደዋለኽ ።

17 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእስራኤል ፡ ምድር ፡ የነበሩትን ፡ መጻተኛዎች ፡ ዅሉ ፡ አባቱ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ቈጠራቸው ፡
ቈጠረ ፤ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ተገኙ ።

18 ፤ ከነርሱም ፡ የሚሸከሙትን ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፥ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡ የሚጠርቡትን ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፥ በሕዝቡም ፡ ሥራ ፡
ላይ ፡ የተሾሙትን ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ አደረገ ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ ሰሎሞንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአባቱ ፡ ለዳዊት ፡ በተገለጠበት ፡ በሞሪያ ፡ ተራራ ፡ ዳዊት ፡ ባዘጋጀው ፡ ስፍራ ፡
በኢያቡሳዊው ፡ በኦርና ፡ ዐውድማ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ዠመረ ።

2 ፤ በነገሠም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ መሥራት ፡ ዠመረ ።

3 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የጣለው ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ርዝመቱም ፡ በዱሮው ፡
ስፍር ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

4 ፤ በቤቱም ፡ ፊት ፡ የነበረው ፡ ወለል ፡ ርዝመቱ ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ ወርድ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡
ነበረ ፤ ውስጡንም ፡ በጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ።

5 ፤ ታላቁንም ፡ ቤት ፡ በጥድ ፡ ዕንጨት ፡ ከደነው ፥ በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ፤ የዘንባባና ፡ የሰንሰለት ፡ አምሳል ፡
ቀረጸበት ።

6 ፤ ቤቱንም ፡ በዕንቊ ፡ አስጌጠው ፤ ወርቁንም ፡ የፈርዋይም ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

7 ፤ ቤቱንም ፡ ሠረገላዎቹንም ፡ መድረኮቹንም ፡ ግንቦቹንም ፡ ደጆቹንም ፡ በወርቅ ፡ ለበጠ ፤ በግንቦቹም ፡ ላይ ፡
ኪሩቤልን ፡ ቀረጸ ።

8 ፤ ቅድስተ ፡ ቅዱሳኑንም ፡ ሠራ ፤ ርዝመቱም ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ ወርድ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡
ነበረ ፤ ስድስት ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ በሚያኽል ፡ በጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ።

9 ፤ የምስማሮቹም ፡ ሚዛን ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ። የደርቡንም ፡ ጓዳዎች ፡ በወርቅ ፡ ለበጠ ።

10 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳንም ፡ ውስጥ ፡ ከዕንጨት ፡ ሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ኪሩቤልን ፡ ሠራ ፥ በወርቅም ፡ ለበጣቸው ።

11 ፤ የኪሩቤልም ፡ ክንፎች ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ሙሉ ፡ ተዘርግተው ፡ ነበር ፤ የአንዱ ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡
ነበረ ፥ የቤቱንም ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበረ ፤ ኹለተኛው ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የኹለተኛውንም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡
ይነካ ፡ ነበር ።

12 ፤ የኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የቤቱንም ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፤ ኹለተኛውም ፡ ክንፍ ፡
ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የሌላውንም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ይነካ ፡ ነበር ።

13 ፤ የእነዚህም ፡ ኪሩቤል ፡ ክንፎች ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ሙሉ ፡ ተዘርግተው ፡ ነበር ፤ በእግራቸውም ፡ ቆመው ፡
ነበር ፥ ፊቶቻቸውም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ።

14 ፤ ከሰማያዊውም ፡ ከሐምራዊውም ፡ ከቀዩም ፡ ሐር ፡ ከጥሩም ፡ በፍታ ፡ መጋረጃውን ፡ ሠራ ፥ ኪሩቤልንም ፡
ጠለፈበት ።

15 ፤ በቤቱም ፡ ፊት ፡ ቁመታቸው ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ የነበረውን ፡ ኹለቱን ፡ ዐምዶች ፡ ሠራ ፥ በያንዳንዳቸውም ፡
ላይ ፡ የነበረው ፡ ጕልላት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

16 ፤ እንደ ፡ ድሪ ፡ ያሉ ፡ ሰንሰለቶችንም ፡ ሠርቶ ፡ በአዕማዱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አደረጋቸው ፤ መቶም ፡ ሮማኖች ፡ ሠርቶ ፡
በሰንሰለቱ ፡ ላይ ፡ አደረጋቸው ።

17 ፤ አዕማዶቹንም ፡ አንደኛውን ፡ በቀኝ ፥ ኹለተኛውን ፡ በግራ ፡ በመቅደሱ ፡ ፊት ፡ አቆማቸው ፤ በቀኝም ፡ የነበረውን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ስም ፡ ያቁም ፡ በግራም ፡ የነበረውን ፡ ስም ፡ በለዝ ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ ደግሞም ፡ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ የነበረውን ፡ የናሱን ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ።

2 ፤ ከፈሰሰም ፡ ናስ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ በዙሪያውም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ክብ ፡ ኵሬ ፡ ሠራ ።

3 ፤ በበታቹም ፡ ላንድ ፡ ክንድ ፡ ዐሥር ፥ ለአንድም ፡ ክንድ ፡ ዐሥር ፥ ጕብጕቦች ፡ አዞረበት ፤ ኵሬውም ፡ በቀለጠ ፡ ጊዜ ፡ ጕብጕቦቹ ፡ በኹለት ፡ ተራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ቀልጠው ፡ ነበር ።

4 ፤ በዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ በሬዎች ፡ ምስል ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ ከነርሱም ፡ ሦስቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፤ ኵሬውም ፡ በላያቸው ፡ ነበር ፥ የኋላቸውም ፡ ዠርባቸው ፡ በስተውስጥ ፡ ነበረ ።

5 ፤ ውፍረቱም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ያኽል ፡ ነበረ ፤ ከንፈሩም ፡ እንደ ፡ ጽዋ ፡ ከንፈር ፥ እንደ ፡ ሱፍ ፡ አበባ ፡ ኾኖ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ፤ ሦስት ፡ ሺሕም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ይይዝ ፡ ነበር ።

6 ፤ ደግሞም ፡ ዐሥር ፡ የመታጠቢያ ፡ ሰኖች ፡ ሠራ ፥ ለሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቀርበው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ይታጠብባቸው ፡ ዘንድ ፡ ዐምስቱን ፡ በቀኝ ፥ ዐምስቱንም ፡ በግራ ፡ አኖራቸው ፤ ኵሬው ፡ ግን ፡ ካህናት ፡ ይታጠቡበት ፡ ነበር ።

7 ፤ ዐሥሩንም ፡ መቅረዞች ፡ እንደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ ከወርቅ ፡ ሠርቶ ፡ ዐምስቱን ፡ በቀኝ ፥ ዐምስቱንም ፡ በግራ ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።

8 ፤ ዐሥሩንም ፡ ገበታዎች ፡ ሠርቶ ፡ ዐምስቱን ፡ በቀኝ ፥ ዐምስቱንም ፡ በግራ ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ። አንድ ፡ መቶም ፡ የወርቅ ፡ ድስቶች ፡ ሠራ ።

9 ፤ ደግሞም ፡ የካህናቱን ፡ አደባባይ ፥ ታላቁንም ፡ አደባባይ ፥ የአደባባዩንም ፡ ደጆች ፡ ሠራ ፥ ደጆቻቸውንም ፡ በናስ ፡ ለበጠ ።

10 ፤ ኵሬውንም ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፡ በአዜብ ፡ በኩል ፡ አኖረው ።

11 ፤ ኪራምም ፡ ምንቸቶቹንና ፡ መጫሪያዎቹን ፡ ድስቶቹንም ፡ ሠራ ። ኪራምም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ጨረሰ ።

12 ፤ ኹለቱን ፡ አዕማድ ፥ ጽዋዎቹንም ፥ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኹለት ፡ ጕልላቶች ፥ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ የጕልላቶች ፡ ኹለቱን ፡ ጽዋዎች ፡ የሚሸፍኑትን ፡ ኹለቱን ፡ መርበቦች ፡ ሠራ ።

13 ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኹለቱን ፡ ጕልላቶች ፡ ይሸፍኑ ፡ ዘንድ ፥ ለያንዳንዱ ፡ መርበብ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ተራ ፡ ሮማኖች ፥ ለኹለቱ ፡ መርበቦች ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሮማኖች ፡ አደረገ ።

14 ፤ መቀመጫዎቹንና ፡ በመቀመጫዎቹ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡትን ፡ የመታጠቢያ ፡ ሰኖች ፥

15 ፤ አንዱንም ፡ ኵሬ ፥ በበታቹም ፡ የሚኾኑትን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፡ ሠራ ።

16 ፤ ምንቸቶቹንም ፡ መጫሪያዎቹንም ፡ ሜንጦዎቹንም ፡ ዕቃቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ኪራም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከለስላሳ ፡ ናስ ፡ ሠራ ።

17 ፤ ንጉሡም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ሜዳ ፡ በሱኮትና ፡ በጽሬዳ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በወፍራሙ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ አስፈሰሰው ።

18 ፤ ሰሎሞንም ፡ እነዚህን ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ እጅግ ፡ አብዝቶ ፡ ሠራ ፤ የናሱም ፡ ሚዛን ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።

19 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ የወርቁንም ፡ መሠዊያ ፥ የገጹንም ፡ ኅብስት ፡



www.ethiopianorthodox.org

የነበረባቸውን ፡ ገበታዎች ፥

20 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ ፡ መቅረዞችንና ፡ ቀንዲሎቻቸውን ፡ ከጥሩ ፡
ወርቅ ፡ ሠራ ።

21 ፤ አበባዎቹንና ፡ ቀንዲሎቹን ፡ መኰስተሪያዎቹንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሠራ ።

22 ፤ ጕጦቹንም ፡ ድስቶቹንም ፡ ጭልፋዎቹንም ፡ ማንደጃዎቹንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሠራ ። የውስጠኛውም ፡ ቤት ፡
የቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ደጆች ፡ የቤተ ፡ መቅደሱም ፡ ደጆች ፡ የወርቅ ፡ ነበሩ ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ እንዲሁም ፡ ሰሎሞን ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተጨረሰ ። አባቱም ፡ ዳዊት ፡ የቀደሰውን ፡
የብርና ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ሰሎሞን ፡ አምጥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በነበረው ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡
አኖረው ።

2 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰሎሞን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከጽዮን ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡
የእስራኤልን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ የነገድ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ አባቶች ፡ ቤቶች ፡ መሳፍንት ፡ ወደ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ሰበሰበ ።

3 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በበዓሉ ፡ ጊዜ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተከማቹ ።

4 ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ መጡ ፥ ሌዋውያንም ፡ ታቦቱን ፡ አነሡ ።

5 ፤ ታቦቱንም ፡ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፡ በድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የተቀደሰውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡
አመጡ ፤ እነዚህንም ፡ ኹሉ ፡ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፡ አመጡ ።

6 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የተሰበሰቡ ፡ የእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፡ ከብዛት ፡
የተነሣ ፡ የማይቈጠሩትንና ፡ የማይመጠኑትን ፡ በጎችና ፡ በሬዎች ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ።

7 ፤ ካህናቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ አምጥተው ፡ በቅድስት ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡
ከኪሩቤል ፡ ክንፍ ፡ በታች ፡ በነበረው ፡ በስፍራው ፡ አኖሩት ።

8 ፤ ኪሩቤልም ፡ በታቦቱ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ነበር ፥ ኪሩቤልም ፡ ታቦቱንና ፡ መሎጊያዎቹን ፡
በስተላዩ ፡ በኩል ፡ ይሸፍኑ ፡ ነበር ።

9 ፤ መሎጊያዎቹም ፡ ረጓዥሞች ፡ ነበሩና ፥ በቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ፊት ፡ ከመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ጫፎቻቸው ፡ ይታዩ ፡
ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከውጪ ፡ አይታዩም ፡ ነበር ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ እዚያ ፡ አሉ ።

10 ፤ በታቦቱም ፡ ውስጥ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡
ቃል ፡ ኪዳን ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ በኰሬብ ፡ ካስቀመጣቸው ፡ ከኹለቱ ፡ ጽላቶች ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልነበረበትም ።

11 ፤ በዚያም ፡ የነበሩት ፡ ካህናት ፡ ኹሉ ፡ ተቀድሰው ፡ ነበር ፥ በሰሞናቸውም ፡ አልተከፈሉም ፡ ነበር ፤

12 ፤ መዘምራንም ፡ የነበሩት ፡ ሌዋውያን ፡ ኹሉ ፥ አሣፍና ፡ ኤማን ፡ ኤዶታምም ፡ ልጆቻቸውም ፡
ወንድሞቻቸውም ፥ ጥሩ ፡ በፍታ ፡ ለብሰው ፡ ጸናጽልና ፡ በገና ፡ መሰንቆም ፡ እየመቱ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡
በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ካህናት ፡ መለከት ፡ ይነፉ ፡ ነበር ። ካህናቱም ፡
ከመቅደሱ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥

13 ፤ መለከቱንም ፡ የሚነፉ ፡ መዘምራኑም ፡ በአንድነት ፡ ኾነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑና ፡
እያከበሩ ፦ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነውና ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ እያሉ ፡
ባንድ ፡ ቃል ፡ ድምፃቸውን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ በመለከትና ፡ በጸናጽል ፡ በዜማም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ባመሰገኑ ፡ ጊዜ ፥ ደመናው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞላው ።

14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞልቶት ፡ ነበርና ፥ ካህናቱ ፡ ከደመናው ፡ የተነሣ ፡ መቆምና ፡



www.ethiopianorthodox.org

ማገልገል ፡ አልተቻላቸውም ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ምዕራፍ ፡ 6 ።

1 ፤ ሰሎሞንም ፡— እግዚአብሔር ፡— በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ እኖራለኹ ፡ ብሏል ፤

2 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኖርበት ፡ ዘንድ ፡ ማደሪያ ፡ ቤትን ፡ ሠራኹልኽ ፡ አለ ።

3 ፤ ንጉሡም ፡ ፊቱን ፡ ዘወር ፡ አድርጎ ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ መረቀ ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ቆመው ፡
ነበር ።

4 ፤ ርሱም ፡ አለ ፡— ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ በአፉ ፡ የተናገረ ፡ በእጁም ፡ የፈጸመ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይባረክ ፤

5 ፤ ርሱም ፡— ሕዝቤን ፡ ከግብጽ ፡ ካወጣኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ስሜ ፡ የሚጠራበት ፡ ቤት ፡ በዚያ ፡ ይሠራልኝ ፡ ዘንድ ፡
ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ማንኛውንም ፡ ከተማ ፡ አልመረጥኹም ፤ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ይኾን ፡
ዘንድ ፡ ማንንም ፡ አልመረጥኹም ፤

6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስሜ ፡ በዚያ ፡ እንዲጠራባት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ መርጫለኹ ፥ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ እንዲኾን ፡
ዳዊትን ፡ መርጫለኹ ፡ ብሏልና ።

7 ፤ አባቴም ፡ ዳዊት ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ዐስቦ ፡ ነበር ።

8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አባቴን ፡ ዳዊትን ፡— ለስሜ ፡ ቤት ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልብኽ ፡ ዐስበኻልና ፥ ይህን ፡ በልብኽ ፡
መልካም ፡ አደረግኽ ።

9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከወገብኽ ፡ የሚወጣው ፡ ልጅኽ ፡ ርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤትን ፡ ይሠራል ፡ እንጂ ፡ ቤት ፡ የምትሠራልኝ ፡
አንተ ፡ አይደለኽም ፡ አለው ።

10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ፈጸመ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፋንታ ፡
ተነሣኹ ፥ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጥኹ ፥ ለእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ሠራኹ ።

11 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያለበትን ፡ ታቦት ፡ በዚያው ፡ ውስጥ ፡
አኖርኹ ።

12 ፤ 13 ፤ ሰሎሞንም ፡ ርዝመቱ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡
የናስ ፡ መደገፊያ ፡ ሠርቶ ፡ በአደባባዩ ፡ መካከል ፡ ተክሎት ፡ ነበር ፥ በላዩም ፡ ቆመ ፥ በእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡
ፊት ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘረጋ ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ በእግዚአብሔር ፡
መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እጆቹንም ፡ ዘርግቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

14 ፤ አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በሰማይ ፡ ወይም ፡ በምድር ፡ አንተን ፡ የሚመስል ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ በፍጹም ፡
ልባቸው ፡ በፊትኽ ፡ ለሚኼዱ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፥

15 ፤ ለባሪያኽ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠኸውን ፡ ተስፋ ፡ የጠበቅኽ ፤ በአፍኽ ፡ ተናገርኽ ፥ ዛሬም ፡ እንደኾነው ፡
በእጅኽ ፡ ፈጸምኸው ።

16 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ። አንተ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ኼድኽ ፡ ልጆችኽ ፡ በሕጌ ፡ ይኼዱ ፡
ዘንድ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቢጠብቁ ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ በፊቴ ፡ አታጣም ፡ ብለኽ ፡ ተስፋ ፡
የሰጠኸውን ፡ ለባሪያኽ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ ጠብቅ ።

17 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ለባሪያኽ ፡ ለዳዊት ፡ የተናገርኸው ፡ ቃል ፡ ይጽና ።

18 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይኖራልን ፦ እንሆ ፥ ሰማይ ፡ ከሰማያትም ፡ በላይ ፡ ያለ ፡
ሰማይ ፡ ይይዝኽ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ይልቁንስ ፡ እኔ ፡ የሠራኹት ፡ ቤት ፡ እንዴት ፡ ያንስ ፡ ይኾን ፦

19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ወደባሪያኽ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ተመልከት ፥ ባሪያኽም ፡ በፊትኽ ፡


www.ethiopianorthodox.org

የሚጸልየውን ፡ ጸሎትና ፡ ጥሪውን ፡ ስማ ።

20 ፤ ባሪያኽ ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎት ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ። በዚያ ፡ ስሜ ፡ ይኾናል ፡ ወዳልኸው ፡
ስፍራ ፥ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ዐይኖችኽ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ የተገለጡ ፡ ይኹኑ ።

21 ፤ ባሪያኽና ፡ ሕዝብኽ ፡ እስራኤል ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልዩትን ፡ ልመና ፡ ስማ ፤ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡
ስማ ፤ ስምተኽም ፡ ይቅር ፡ በል ።

22 ፤ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ ቢበድል ፥ በላዩም ፡ መሐላ ፡ ቢጫን ፥ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ በመሠዊያኽ ፡ ፊት ፡
ቢምል ፥

23 ፤ በሰማይ ፡ ስማ ፥ አድርግም ፥ በባሪያዎችኽም ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ኹን ፥ በበደለኛውም ፡ ላይ ፡ ፍረድ ፥ መንገዱንም ፡
በራሱ ፡ ላይ ፡ መልስበት ፤ ንጹሑንም ፡ አጽድቀው ፥ እንደ ፡ ጽድቁም ፡ ክፈለው ።

24 ፤ ሕዝብኽም ፡ እስራኤል ፡ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ በጠላት ፡ ፊት ፡ ድል ፡ ተመትተው ፡ ወዳንተ ፡
ቢመለሱ ፥ ስምኽንም ፡ ቢያከብሩ ፥ በዚህም ፡ ቤት ፡ በፊትኽ ፡ ቢጸልዩና ፡ ቢለምኑኽ ፥ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥

25 ፤ የሕዝብኽንም ፡ የእስራኤልን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፤ ለእነርሱም ፡ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደሰጠኻት ፡ ምድር ፡
መልሳቸው ።

26 ፤ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ሰማያት ፡ በተዘጉ ፡ ጊዜ ፡ ዝናብም ፡ ባልዘነበ ፡ ጊዜ ፥ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ ቢጸልዩ ፥ ስምኽንም ፡
ቢያከብሩ ፥ ባስጨነቅኻቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከኀጢአታቸው ፡ ቢመለሱ ፥ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥

27 ፤ የባሪያዎችኽንና ፡ የሕዝብኽን ፡ የእስራኤልን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፥ የሚኼዱበትንም ፡ መልካም ፡ መንገድ ፡
አሳያቸው ፤ ለሕዝብኽም ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ ለሰጠኻት ፡ ምድር ፡ ዝናብን ፡ ስጥ ።

28 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ራብ ፡ ወይም ፡ ቸነፈር ፡ ወይም ፡ ዋግ ፡ ወይም ፡ ዐረማሞ ፡ ወይም ፡ አንበጣ ፡ ወይም ፡ ኩብኩባ ፡
ቢኾን ፥ ጠላቶቻቸውም ፡ የአገሩን ፡ ከተማዎች ፡ ከበው ፡ ቢያስጨንቋቸው ፥ ማናቸውም ፡ መቅሠፍትና ፡ ደዌ ፡ ቢኾን ፥

29 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሕዝብኽ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፥ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሕመሙንና ፡ ሐዘኑን ፡ ዐውቆ ፡
ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ቢያደርግ ፡ እጆቹንም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ቢዘረጋ ፥

30 ፤ 31 ፤ ለአባቶቻችን ፡ በሰጠኸው ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በሚኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ይፈሩኽ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዶችኽም ፡
ይኼዱ ፡ ዘንድ ፥ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ይቅርም ፡ በል ፤ አንተ ፡ ብቻ ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ልብ ፡ ታውቃለኽና ፡
ልቡን ፡ ለምታውቀው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ኹሉ ፡ መጠን ፡ ክፈለው ።

32 ፤ ከሕዝብኽም ፡ ከእስራኤል ፡ ያልኾነ ፡ እንግዳ ፡ ስለ ፡ ታላቁ ፡ ስምኽ ፡ ስለ ፡ ብርቱውም ፡ እጅኽ ፡ ስለተዘረጋውም ፡
ክንድኽ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ መጥቶም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፥

33 ፤ አንተ ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ስምኽን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ እንደ ፡ ሕዝብኽም ፡
እንደ ፡ እስራኤል ፡ ይፈሩኽ ፡ ዘንድ ፥ በዚህም ፡ በሠራኹት ፡ ቤት ፡ ስምኽ ፡ እንደ ፡ ተጠራ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ እንግዳው ፡
የሚለምንኽን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ።

34 ፤ ሕዝብኽም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለመውጋት ፡ አንተ ፡ በምትልካቸው ፡ መንገድ ፡ ቢወጡ ፥ አንተም ፡ ወደመረጥኻት ፡
ወደዚች ፡ ከተማ ፡ እኔም ፡ ለስምኽ ፡ ወደሠራኹት ፡ ቤት ፡ ለአንተ ፡ ቢጸልዩ ፥

35 ፤ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ።

36 ፤ የማይበድል ፡ ሰው ፡ የለምና ፡ አንተን ፡ ቢበድሉ ፥ ተቈጥተኽም ፡ ለጠላት ፡ አሳልፈኽ ፡ ብትሰጣቸው ፥ ሩቅም ፡
ወይም ፡ ቅርብ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ አገር ፡ ቢማርኳቸው ፥

37 ፤ በተማረኩበትም ፡ አገር ፡ ኾነው ፡ በልባቸው ፡ ንስሓ ፡ ቢገቡ ፥ በምርኳቸውም ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡
ተመልሰው ፦ ኀጢአት ፡ ሠርተናል ፥ በድለንማል ፥ ክፉም ፡ አድርገናል ፡ ብለው ፡ ቢለምኑኽ ፥

38 ፤ በተማረኩበትም ፡ በምርኳቸው ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ ወዳንተ ፡
ቢመለሱ ፥ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደሰጠኻት ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ ወደመረጥኻትም ፡ ከተማ ፡ ለስምኽም ፡ ወደሠራኹት ፡



www.ethiopianorthodox.org

ቤት ፡ ቢጸልዩ ፥

39 ፤ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ፤ አንተንም ፡ የበደሉኽን ፡ ሕዝብኽን ፡ ይቅር ፡ በል ።

40 ፤ አኹንም ፥ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ወደሚኾነው ፡ ጸሎት ፡ ዐይኖችኽ ፡ የተገለጡ ፥ ዦሮዎችኽም ፡ የሚያደምጡ ፡ እንዲኾኑ ፡ እለምንኻለኹ ።

41 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከኀይልኽ ፡ ታቦት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዕረፍትኽ ፡ ተነሣ ፤ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ካህናትኽ ፡ ደኅንነትን ፡ ይልበሱ ፤ ቅዱሳንኽም ፡ በደስታ ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።

42 ፤ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ የቀባኸውን ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ አትመልስ ፡ ለባሪያም ፡ ለዳዊት ፡ ያደረግኽለትን ፡ ምሕረት ፡ ዐስብ ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ምዕራፍ ፡ 7 ።

1 ፤ ሰሎሞንም ፡ ጸሎቱን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕቱን ፡ በላ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ቤቱን ፡ ሞላ ።

2 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞልቶት ፡ ነበርና ፥ ካህናቱ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ አልቻሉም ።

3 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ዅሉ ፡ እሳቱ ፡ ሲወርድ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ ሲኾን ፡ ያዩ ፡ ነበር ፤ በወለሉም ፡ ላይ ፡ በግንባራቸው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተደፍተው ፡ ሰገዱ ። ርሱ ፡ መልካም ፡ ነውና ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ ብለውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ።

4 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቡም ፡ ዅሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ።

5 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ በሬዎችና ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ ሠዋ ። እንዲሁ ፡ ንጉሡና ፡ ሕዝቡ ፡ ዅሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ቀደሱ ።

6 ፤ ካህናቱም ፡ በየሥርዐታቸው ፥ ሌዋውያኑም ፡ ደግሞ ፦ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ የሚለውን ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ እየዘመሩ ፥ ንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማመስገን ፡ የሠራውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የዜማ ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ ካህናቱም ፡ በፊታቸው ፡ መለከት ፡ ይነፉ ፡ ነበር ፤ እስራኤልም ፡ ዅሉ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

7 ፤ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ የአደባባዩን ፡ ውስጥ ፡ ቀደሰ ፤ ሰሎሞንም ፡ የሠራው ፡ የናስ ፡ መሠዊያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ ስቡንም ፡ መያዝ ፡ አልቻለምና ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ በዚያ ፡ አቀረበ ።

8 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ የኾኑ ፥ ከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ዠምሮ ፡ እስከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ያሉ ፡ እስራኤል ፡ ዅሉ ፥ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አደረጉ ።

9 ፤ ሰባት ፡ ቀንም ፡ መሠዊያውን ፡ ቀድሰው ፥ ሰባት ፡ ቀንም ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ ነበርና ፥ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰውን ፡ ጉባኤ ፡ አደረጉ ።

10 ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ ሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ ድንኳናቸው ፡ አሰናበተ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊትና ፡ ለሰሎሞን ፡ ለሕዝቡም ፡ ለእስራኤል ፡ ስላደረገው ፡ ቸርነት ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ሐሴትን ፡ እያደረጉ ፡ ኼዱ ።

11 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ጨረሰ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በራሱ ፡ ቤት ፡ ይሠራው ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ያሰበውን ፡ ዅሉ ፡ አከናወነ ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለሰሎሞን ፡ በሌሊት ፡ ተገልጦ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ጸሎትኽን ፡ ሰምቻለኹ ፥ ይህንም ፡ ስፍራ ፡ ለራሴ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ቤት ፡ መርጫለኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

13 ፤ ዝናብ ፡ እንዳይወርድ ፡ ሰማያቱን ፡ ብዘጋ ፥ ወይም ፡ ምድሪቱን ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ አንበጣን ፡ ባዘው ፥ ወይም ፡
በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ቸነፈር ፡ ብሰድ ፥

14 ፤ በስሜ ፡ የተጠሩት ፡ ሕዝቤ ፡ ሰውነታቸውን ፡ አዋርደው ፡ ቢጸልዩ ፥ ፊቴንም ፡ ቢፈልጉ ፥ ከክፉ ፡ መንገዳቸውም ፡
ቢመለሱ ፥ በሰማይ ፡ ኾኜ ፡ እሰማለኹ ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቅር ፡ እላለኹ ፥ ምድራቸውንም ፡ እፈውሳለኹ ።

15 ፤ አኹንም ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ለሚጸለይ ፡ ጸሎት ፡ ዐይኖቼ ፡ ይገለጣሉ ፥ ዦሮዎቼም ፡ ያደምጣሉ ።

16 ፤ አኹንም ፡ ስሜ ፡ ለዘለዓለም ፡ በዚያ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ መርጫለኹ ፡ ቀድሻለኹም ፤ ዐይኖቼና ፡
ልቤም ፡ ዘወትር ፡ በዚያ ፡ ይኾናሉ ።

17 ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ አባትኽ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ኼደ ፡ በፊቴ ፡ ብትኼድ ፥ እንዳዘዝኹኽም ፡ ዂሉ ፡
ብታደርግ ፥ ሥርዐቴንና ፡ ፍርዴንም ፡ ብትጠብቅ ፥

18 ፤ ከአባትኽ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ። በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፥ የሚኾን ፡ ከዘርኽ ፡ አይታጣም ፡ ብዬ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
እንዳደረግኹ ፡ የመንግሥትኽን ፡ ዙፋን ፡ አጸናለኹ ።

19 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ከመከተል ፡ ብትመለሱ ፥ የሰጠ኿ችኹንም ፡ ሥርዐቴንና ፡ ትእዛዜን ፡
ብትተዉ ፥ ኼዳችኹም ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ብታመልኩ ፡ ብትሰግዱላቸውም ፥

20 ፤ ለአባቶቻችኹ ፡ ከሰጠ኿ቸው ፡ ምድር ፡ እነቅላች኿ለኹ ፤ ለስሜም ፡ የቀደስኹትን ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ከፊቴ ፡
እጥለዋለኹ ፥ በአሕዛብም ፡ ዂሉ ፡ መካከል ፡ ምሳሌና ፡ ተረት ፡ አደርገዋለኹ ።

21 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የነበረውንም ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ እያዩ ፡ በዚያ ፡ የሚያልፉ ፡ ሰዎች ፡ ዂሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡
አገርና ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፧ ብለው ፡ ይደነቃሉ ።

22 ፤ መልሰውም ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣቸውን ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ሌላዎችን ፡
አማልክት ፡ ስለ ፡ ተከተሉ ፥ ስለ ፡ ሰገዱላቸውም ፥ ስለ ፡ አመለኳቸውም ፥ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ዂሉ ፡
አመጣባቸው ፡ ይላሉ ።

____________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 8 ።

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሰሎሞን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ የሠራበት ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥

2 ፤ ኪራም ፡ ለሰሎሞን ፡ የሰጠውን ፡ ከተማዎች ፡ ሰሎሞን ፡ ሠራቸው ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ አኖረባቸው ።

3 ፤ ሰሎሞንም ፡ ወደ ፡ ሐማትሱባ ፡ ኼደ ፥ አሸነፋትም ።

4 ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ያለውን ፡ ተድሞርን ፥ በሐማትም ፡ የሠራቸውን ፡ የዕቃ ፡ ቤቱን ፡ ከተማዎች ፡ ዂሉ ፡ ሠራ ።

5 ፤ ደግሞም ፡ ቅጥርና ፡ መዝጊያ ፡ መወርወሪያም ፡ የነበራቸውን ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ ላይኛውን ፡ ቤትሖሮን ፡
ታችኛውንም ፡ ቤትሖሮን ፡ ሠራ ።

6 ፤ ባዕላትንም ፥ ለሰሎሞንም ፡ የነበሩትን ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ ከተማዎች ፡ ዂሉ ፥ የሠረገላውንም ፡ ከተማዎች ፡
ዂሉ ፥ የፈረሰኛዎችንም ፡ ከተማዎች ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በሊባኖስም ፡ በመንግሥቱም ፡ ምድር ፡ ዂሉ ፡ ሰሎሞን ፡ ይሠራ ፡
ዘንድ ፡ የወደደውን ፡ ዂሉ ፡ ሠራ ።

7 ፤ ከኬጢያውያንም ፡ ከአሞራውያንም ፡ ከፌርዜያውያንም ፡ ከዔዊያውያንም ፡ ከኢያቡሳውያንም ፡ የቀሩትን ፡ ከእስራኤል ፡
ወገን ፡ ያልኾኑትን ፡ ሕዝብ ፡ ዂሉ ፥

8 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ያላጠፏቸውን ፥ በኋላቸው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የቀሩትን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሰሎሞን ፡ እስከ ፡
ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ገባሮች ፡ አድርጎ ፡ መለመላቸው ።

9 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለሥራው ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማንንም ፡ ባሪያ ፡ አላደረገም ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡
ሰልፈኛዎች ፥ የሹማምቶችም ፡ አለቃዎች ፥ የሠረገላዎችና ፡ የፈረሰኛዎች ፡ ባልደራሶች ፡ ነበሩ ።



www.ethiopianorthodox.org

10 ፤ እነዚህም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ሠልጥነው ፡ የነበሩ ፡ የንጉሡ ፡ የሰሎሞን ፡ ዐይነተኛዎች ፡ አለቃዎች ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ።

11 ፤ ሰሎሞንም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ የገባበት ፡ ስፍራ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፥ ሚስቴ ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በዳዊት ፡ ቤት ፡ አትቀመጥም ፡ ሲል ፡ የፈርዖንን ፡ ልጅ ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ወደሠራላት ፡ ቤት ፡ አወጣት ።

12 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰሎሞን ፡ በወለሉ ፡ ፊት ፡ በሠራው ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ።

13 ፤ ሙሴም ፡ እንዳዘዘ ፡ እንደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ በየቀኑ ፡ ኹሉ ፥ በየሰንበታቱም ፥ በየመባቻዎቹም ፥ በየተወሰኑትም ፡ በዓላት ፥ በየዓመቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በየቂጣው ፡ በዓልና ፡ በየሰባቱ ፡ ሱባዔ ፡ በዓል ፡ በየዳሱም ፡ በዓል ፡ ቍርባን ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ።

14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ዳዊት ፡ እንዲህ ፡ አዞ ፡ ነበርና ፥ ካህናቱን ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ሥርዐት ፡ በያገልግሎታቸው ፡ ሰሞን ፡ ከፈላቸው ፤ ሌዋውያንም ፡ እንደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፥ በካህናቱም ፡ ፊት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ በየሰሞናቸው ፡ ከፈላቸው ፤ በረኛዎቹንም ፡ ደግሞ ፡ በየበሩ ፡ ኹሉ ፡ በየሰሞናቸው ፡ ከፈላቸው ።

15 ፤ እነርሱም ፡ ንጉሡ ፡ ስለ ፡ ነገሩ ፡ ኹሉና ፡ ስለ ፡ መዝገቡ ፡ ካህናቱንና ፡ ሌዋውያኑን ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አልተላለፉም ።

16 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ መሠረት ፡ ከተጣለ ፡ ዠምሮ ፡ እስከተጨረሰ ፡ ድረስ ፡ የሰሎሞን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነበረ ። የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ተፈጸመ ።

17 ፤ ሰሎሞንም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ወዳሉ ፡ ወደ ፡ ዔጽዮንጋብርና ፡ ወደ ፡ ኤሎት ፡ ኼደ ።

18 ፤ ኪራምም ፡ መርከቦችንና ፡ የባሕርን ፡ ነገር ፡ የሚያውቁትን ፡ መርከበኛዎች ፡ በባሪያዎቹ ፡ እጅ ፡ ሰደደለት ፤ እነርሱም ፡ ከሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኦፊር ፡ መጡ ፥ ከዚያም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ አመጡ ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምዕራፍ ፡ 9 ።

1 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ዝና ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ በግመሎች ፡ ላይ ፡ ሽቱና ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ የከበረም ፡ ዕንቍ ፡ አስጭና ፡ ከታላቅ ፡ ጓዝ ፡ ጋራ ፡ ሰሎሞንን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእንቆቅልሽ ፡ ትፈትነው ፡ ዘንድ ፡ መጣች ፤ ወደ ፡ ሰሎሞንም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ በልቧ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ አጫወተችው ።

2 ፤ ሰሎሞንም ፡ የጠየቀችውን ፡ ኹሉ ፡ ፈታላት ፤ ሰሎሞንም ፡ ያልፈታው ፡ ስውር ፡ ነገር ፡ አልነበረም ።

3 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፥ ሠርቶትም ፡ የነበረውን ፡ ቤት ፥ የማእዱንም ፡ መብል ፥

4 ፤ የብላቴናዎቹንም ፡ አቀማመጥ ፥ የሎሌዎቹንም ፡ አሠራር ፡ አለባበሳቸውንም ፥ ጠጅ ፡ አሳላፊዎቹንም ፡ አለባበሳቸውንም ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የሚያሳርገውን ፡ መሥዋዕት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ አልቀረላትም ።

5 ፤ ንጉሡንም ፡ አለችው ፦ ስለ ፡ ነገርኽና ፡ ስለ ፡ ጥበብኽ ፡ በአገሬ ፡ ሳለኹ ፡ የሰማኹት ፡ ዝና ፡ እውነት ፡ ነው ።

6 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ መጥቼ ፡ በዐይኔ ፡ እስካየኹ ፡ ድረስ ፡ የነገሩኝን ፡ አላመንኹም ፤ እንሆ ፥ የጥበብኽን ፡ ታላቅነት ፡ እኩሌታ ፡ አልነገሩኝም ፤ ከሰማኹት ፡ ዝና ፡ ትበልጣለኽ ።

7 ፤ በፊትኽ ፡ ኹልጊዜ ፡ የሚቆሙ ፡ ጥበብኽንም ፡ የሚሰሙ ፡ ሰዎችኽና ፡ እነዚህ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

8 ፤ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ንጉሥ ፡ እንድትኾን ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ያስቀምጥኽ ፡ ዘንድ ፡ የወደደኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቡሩክ ፡ ይኹን ፤ አምላክኽ ፡ እስራኤልን ፡ ለዘለዓለም ፡ ያጸናቸው ፡ ዘንድ ፡ ወዷቸዋልና ፥ ስለዚህ ፡ ፍርድና ፡ ጽድቅ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ በላያቸው ፡ አነገሠኽ ።

9 ፤ ለንጉሡም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፥ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ሽቱ ፡ የከበረም ፡ ዕንቍ ፡ ሰጠችው ፤ የሳባም ፡



www.ethiopianorthodox.org

ንግሥት ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ሰጠችው ፡ ያለ ፡ ሽቱ ፡ ከቶ ፡ አልነበረም ።

10 ፤ ከኦፊርም ፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ የኪራም ፡ ባሪያዎችና ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ የሰንደል ፡ ዕንጨትና ፡ የከበረ ፡ ዕንቍ ፡ ደግሞ ፡ አመጡ ።

11 ፤ ንጉሡም ፡ ከሰንደሉ ፡ ዕንጨት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ ለንጉሡ ፡ ቤት ፡ ደርብ ፥ ለመዘምራኑም ፡ መሰንቆና ፡ በገና ፡ አደረገ ፤ እንደዚህም ፡ ያለ ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ከቶ ፡ አልታየም ፡ ነበር ።

12 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ካመጣችው ፡ የሚበልጥ ፥ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ የወደደችውን ፡ ኹሉ ፡ ከርሱም ፡ የለመነችውን ፡ ኹሉ ፡ ሰጣት ፤ ርሷም ፡ ተመልሳ ፡ ከባሪያዎቿ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ምድሯ ፡ ኼደች ።

13 ፤ ነጋድራሶችና ፡ ነጋዴዎች ፡ ካመጡለት ፡ ሌላ ፡ በየዓመቱ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ የሚመጣ ፡ የወርቅ ፡ ሚዛን ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

14 ፤ የዐረብም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ የምድሩም ፡ ሹማምት ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ያመጡ ፡ ነበር ።

15 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በጥፍጥፍ ፡ ወርቅ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፤ በአንዱም ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ጥፍጥፍ ፡ ወርቅ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

16 ፤ ከጥፍጥም ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፤ በአንዱም ፡ ጋሻ ፡ የገባው ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ፤ ንጉሡም ፡ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ በተባለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።

17 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ ከዝኆን ፡ ጥርስ ፡ ታላቅ ፡ ዙፋን ፡ አሠራ ፥ በጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ለበጠው ።

18 ፤ ከዙፋኑም ፡ ጋራ ፡ ተጋጥመው ፡ ወደ ፡ ዙፋኑም ፡ የሚያስኼዱ ፡ ስድስት ፡ ዕርከኖች ፡ ነበሩ ፤ የወርቅ ፡ ብርኵማም ፡ ነበረ ፤ በዚህና ፡ በዚያም ፡ በመቀመጫው ፤ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ የክንድ ፡ መደገፊያዎች ፡ ነበሩበት ፥ በመደገፊያዎችም ፡ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ አንበሳዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

19 ፤ በስድስቱም ፡ ዕርከኖች ፡ ላይ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አንበሳዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ በመንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ አልተሠራም ።

20 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የሚጠጣበት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ የወርቅ ፡ ነበረ ፥ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ በተባለውም ፡ ቤቱ ፡ የነበረው ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፤ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ብር ፡ ከቶ ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።

21 ፤ ለንጉሡም ፡ ከኪራም ፡ ባሪያዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ የሚኼዱ ፡ መርከቦች ፡ ነበሩት ፤ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ዓመትም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የዝኆንም ፡ ጥርስ ፡ ዝንጀሮና ፡ ዝጕርጕር ፡ ወፍም ፡ ይዘው ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

22 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በባለጠግነትና ፡ በጥበብ ፡ በለጠ ።

23 ፤ የምድርም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ ያኖረውን ፡ ጥበቡን ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ የሰሎሞንን ፡ ፊት ፡ ሊያዩ ፡ ይመኙ ፡ ነበር ።

24 ፤ እያንዳንዱም ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፥ የወርቅንና ፡ የብርን ፡ ዕቃ ፥ ልብስንና ፡ የጦር ፡
መሣሪያን ፥ ሽቱውንም ፥ ፈረሶችንና ፡ በቅሎዎችን ፡ እየያዘ ፡ በየዓመቱ ፡ ያመጣ ፡ ነበር ።

25 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለፈረሶችና ፡ ለሠረገላዎች ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጋጥ ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕም ፡ ፈረሰኞዎች ፡
ነበሩት ፥ በሠረገላዎችም ፡ ከተማዎች ፥ ከንጉሡም ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ።

26 ፤ ከኤፍራጥስም ፡ ወንዝ ፡ ዠምሮ ፡ እስከፍልስጥኤም ፡ ምድርና ፡ እስከግብጽ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ባሉ ፡ ነገሥታት ፡
ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

27 ፤ ንጉሡም ፡ ብሩን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ እንዲበዛ ፡ አደረገው ፤ የዝግባውንም ፡ ዕንጨት ፡ ብዛት ፡
በቈላ ፡ እንደሚበቅል ፡ ሾላ ፡ አደረገው ።

28 ፤ ለሰሎሞንም ፡ ፈረሶች ፡ ከግብጽና ፡ ከየአገሩ ፡ ኹሉ ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ።

29 ፤ የቀረውም ፡ ፊተኛውና ፡ ኋለኛው ፡ የሰሎሞን ፡ ነገር ፡ በነቢዩ ፡ በናታን ፡ ታሪክ ፥ በሴሎናዊውም ፡ በኦሒያ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ትንቢት ፥ ስለ ፡ ናባጥም ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ባየው ፡ በባለራእዩ ፡ በአዶ ፡ ራእይ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፨

30 ፤ ሰሎሞንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

31 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ሮብዓም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡
ነገሠ ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምዕራፍ ፡ 10 ።

1 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፥ ሮብዓም ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ኼደ ።

2 ፤ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓምም ፡ ከንጉሡ ፡ ከሰሎሞን ፡ ፊት ፡ ሸሽቶ ፡ በግብጽ ፡ ይኖር ፡ ነበርና ፥ ይህን ፡ በሰማ ፡
ጊዜ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ከግብጽ ፡ ተመለሰ ።

3 ፤ ልከውም ፡ ጠሩት ፤ ኢዮርብዓምና ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ መጥተው ፡ ሮብዓምን ፦

4 ፤ አባትኽ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብን ፡ ነበር ፤ አኹንም ፡ አንተ ፡ ጽኑውን ፡ የአባትኽን ፡ አገዛዝ ፥ በላያችንም ፡ የጫነውን ፡
የከበደውን ፡ ቀንበር ፡ አቅልልን ፥ እኛም ፡ እንገዛልኻለን ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

5 ፤ ርሱም ፦ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በዃላ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ኼዱ ።

6 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስለት ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፨ ብሎ ፡ አባቱ ፡
ሰሎሞን ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

7 ፤ እነርሱም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ቸርነት ፡ ብታደርግላቸው ፥ ደስም ፡ ብታሠኛቸው ፥ በገርነትም ፡
ብትናገራቸው ፥ ለዘለዓለም ፡ ባሪያዎች ፡ ይኾኑልኻል ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

8 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከሩትን ፡ ነገር ፡ ትቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካደጉትና ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡
ብላቴናዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

9 ፤ ርሱም ፦ አባትኽ ፡ የጫነብንን ፡ ቀንበር ፡ አቅልልን ፡ ለሚሉኝ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስላቸው ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡
ምንድር ፡ ነው ፨ አላቸው ።

10 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያደጉት ፡ ብላቴናዎች ፦ አባትኽ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብን ፡ ነበር ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አቅልልን ፡
ለሚሉኽ ፡ ሕዝብ ፦ ታናሺቱ ፡ ጣቴ ፡ ከአባቴ ፡ ወገብ ፡ ትወፍራለች ፤

11 ፤ አኹንም ፡ አባቴ ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ጭኖባችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በቀንበራችኹ ፡ ላይ ፡ እጨምራለኹ ፤ አባቴ ፡
በዐለንጋ ፡ ገርፏችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኋለኹ ፡ በላቸው ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

12 ፤ ንጉሡም ፦ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ኢዮርብዓምና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡
በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ መጡ ።

13 ፤ ንጉሡም ፡ ጽኑ ፡ ምላሽ ፡ መለሰላቸው ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ የሽማግሌዎቹን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፦

14 ፤ አባቴ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶባችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ እጨምርበታለኹ ፤ አባቴ ፡ በዐለንጋ ፡ ገርፏችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡
ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኋለኹ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ብላቴናዎቹ ፡ ምክር ፡ ተናገራቸው ።

15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሴሎናዊው ፡ በአኪያ ፡ አድርጎ ፡ ለናባጥ ፡ ልጅ ፡ ለኢዮርብዓም ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡
እንዲያጸና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተወስኖ ፡ ነበርና ፥ ንጉሡ ፡ ሕዝቡን ፡ አልሰማም ።

16 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ንጉሡ ፡ እንዳልሰማቸው ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፦ በዳዊት ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ክፍል ፡
አለን ፨ በእሴይም ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ ርስት ፡ የለንም ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ እየድንኳኖቻችኹ ፡ ተመለሱ ፤ ዳዊት ፡
ሆይ ፥ አኹን ፡ ቤትኽን ፡ ተመልከት ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ መለሱለት ። እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እየድንኳኖቻቸው ፡
ኼዱ ።

17 ፤ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ በተቀመጡት ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሮብዓም ፡ ነገሠባቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

18 ፲ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ አስገባሪውን ፡ አዶራምን ፡ ሰደደ ፲ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በድንጋይ ፡
ወገሩት ፥ ሞተም ፲ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሸሸ ።

19 ፲ እስራኤልም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ሸፈተ ።

__________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 11 ።

1 ፲ ሮብዓምም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤልን ፡ ወግተው ፡ መንግሥቱን ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ ይመልሱ ፡
ዘንድ ፡ ከይሁዳና ፡ ከብንያም ፡ ቤት ፡ የተመረጡትን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ ሰልፈኞዎች ፡ ሰዎች ፡ ሰበሰበ ።

2 ፲ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደሸማያ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

3 ፲ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ለሮብዓም ፥ በይሁዳና ፡ በብንያምም ፡ ላሉት ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፦

4 ፲ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፥ አትውጡ ፥ ወንድሞቻችኹንም ፡
አትውጉ ፲ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ። የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡
ሰሙ ፥ በኢዮርብዓምም ፡ ላይ ፡ ከመኼድ ፡ ተመለሱ ።

5 ፲ ሮብዓምም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጠ ፥ በይሁዳም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ ሠራ ።

6 ፲ በይሁዳና ፡ በብንያም ፡ ያሉትንም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፥ ቤተ ፡ ልሔም ፥ ኤጣምን ፥ ቴቁሔን ፥

7 ፲ 8 ፲ ቤትጹርን ፥ ሦኮን ፥ ዓዶላምን ፥ ጌትን ፥ መሪሳን ፥

9 ፲ ዚፍን ፥ አዶራይምን ፥ ለኪሶን ፥ ዓዜቃን ፥

10 ፲ ጾርዓን ፥ ኤሎንን ፥ ኬብሮንን ፥ ሠራ ።

11 ፲ ምሽጎቹንም ፡ አጠነከረ ፥ አለቃዎችንም ፡ አኖረባቸው ፥ ምግቡንም ፡ ዘይቱንም ፡ የወይን ፡ ጠጁንም ፡ አከማቸባቸው ።

12 ፲ በከተማዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ጋሻና ፡ ጦርን ፡ አኖረ ። ከተማዎቹንም ፡ እጅግ ፡ አጠነከራቸው ፲ ይሁዳና ፡ ብንያምም ፡ የርሱ ፡
ወገን ፡ ነበሩ ።

13 ፲ በእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የነበሩ ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ ከየአገራቸው ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ።

14 ፲ የእግዚአብሔርም ፡ ካህናት ፡ እንዳይኾኑ ፡ ኢዮርብዓምና ፡ ልጆቹ ፡ አስለቅቀዋቸው ፡ ነበርና ፥ ሌዋውያን ፡
መሰመሪያቸውንና ፡ ቦታቸውን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ይሁዳና ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

15 ፲ ርሱ ፡ ግን ፡ ለኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ለአጋንንቱም ፡ ለሠራቸውም ፡ እንቦሶች ፡ ካህናትን ፡ አቆመ ።

16 ፲ ደግሞም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዉ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤልን ፡
አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመፈለግ ፡ ልባቸውን ፡ የሰጡ ፡ ኹሉ ፡ እነርሱን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

17 ፲ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በዳዊትና ፡ በሰሎሞን ፡ መንገድ ፡ ይኼዱ ፡ ነበርና ፥ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የይሁዳን ፡ መንግሥት ፡
አበረቱ ፥ የሰሎሞንንም ፡ ልጅ ፡ ሮብዓምን ፡ አጸኑ ።

18 ፲ ሮብዓምም ፡ መሐላትን ፡ አገባ ፲ አባቷ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ኢያሪሙት ፡ ነበረ ፲ እናቷም ፡ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ የኤልያብ ፡
ልጅ ፡ አቢካኢል ፡ ነበረች ።

19 ፲ ርሷም ፡ የዑስን ፥ ሰማራያን ፥ ዘሃምን ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ወለደችለት ።

20 ፲ ከርሷም ፡ በኋላ ፡ የአቤሴሎምን ፡ ልጅ ፡ መዓካን ፡ አገባ ፲ ርሷም ፡ አብያን ፥ ዐታይን ፥ ዚዛን ፥ ሰሎሚትን ፡
ወለደችለት ።

21 ፲ ሮብዓምም ፡ ከሚስቶቹና ፡ ከቁባቶቹ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የአቤሴሎምን ፡ ልጅ ፡ መዓካን ፡ ወደደ ፲ ዐሥራ ፡ ስምንትም ፡
ሚስቶችና ፡ ስድሳ ፡ ቁባቶች ፡ ነበሩት ፥ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ወንዶችና ፡ ስድሳ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወለደ ።

22 ፲ ሮብዓምም ፡ ንጉሥ ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ዐስቢልና ፥ የመዓካን ፡ ልጅ ፡ አብያን ፡ በወንድሞቹ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡



www.ethiopianorthodox.org

አድርጎ ፡ ሾመው ።

23 ፤ ተጠበበም ፥ ልጆቹንም ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳና ፡ በብንያም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በምሽጉ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ከፋፈላቸው ፤ ብዙም ፡ ምግብ ፡ ሰጣቸው ፤ ብዙም ፡ ሚስቶች ፡ ፈለገላቸው ።

______________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 12 ።

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የሮብዓም ፡ መንግሥት ፡ በጸናች ፡ ጊዜ ፥ ርሱም ፡ በበረታ ፡ ጊዜ ፥ ርሱና ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ተዉ ።

2 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በድለዋልና ፥ ሮብዓም ፡ በነገሠ ፡ በዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ሺሻቅ ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሠረገላዎችና ፡ ስድሳ ፡ ሺሕ ፡ ፈረሰኛዎች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣ ።

3 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ከግብጽ ፡ ለመጣው ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥር ፡ አልነበረውም ፤ እነርሱም ፡ የልብያ ፡ ሰዎች ፥ ሱካውያን ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎችም ፡ ነበሩ ።

4 ፤ ለይሁዳም ፡ የነበሩትን ፡ ምሽጎች ፡ ከተማዎች ፡ ወሰደ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጣ ።

5 ፤ ነቢዩም ፡ ሸማያ ፡ ወደ ፡ ሮብዓምና ፡ ከሺሻቅ ፡ ሸሽተው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወደተሰበሰቡባት ፡ ወደይሁዳ ፡ መሳፍንት ፡ መጥቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተ ፡ ተዋችኹኝ ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በሺሻቅ ፡ እጅ ፡ ተውኋችኹ ።

6 ፤ የእስራኤልም ፡ መሳፍንትና ፡ ንጉሡ ። እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሰውነታቸውን ፡ አዋረዱ ።

7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰውነታቸውን ፡ እንዳዋረዱ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ። ሰውነታቸውን ፡ አዋርደዋል ፤ አላጠፋቸውም ፤ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ አድናቸዋለኹ ፥ ቍጣዬም ፡ በሺሻቅ ፡ እጅ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አይፈስም ፤

8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለእኔ ፡ መገዛትንና ፡ ለምድር ፡ ነገሥታት ፡ መገዛትን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገዙለታል ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ ሸማያ ፡ መጣ ።

9 ፤ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ሺሻቅም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ መዛግብትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ ወሰደ ፤ ኹሉንም ፡ ወሰደ ፤ ደግሞም ፡ ሰሎሞን ፡ የሠራቸውን ፡ የወርቁን ፡ ጋሻዎች ፡ ወሰደ ።

10 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ በእነርሱ ፡ ፋንታ ፡ የናስ ፡ ጋሻዎችን ፡ ሠራ ፥ የንጉሡንም ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ በሚጠብቁ ፡ በዘበኛዎች ፡ አለቃ ፡ እጅ ፡ አኖራቸው ።

11 ፤ ንጉሡም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ ቍጥር ፡ ዘበኛዎች ፡ መጥተው ፡ ይሸከሟቸው ፡ ነበር ፥ መልሰውም ፡ በዘበኛዎች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያኖሯቸው ፡ ነበር ።

12 ፤ ሰውነቱንም ፡ ባዋረደ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳያጠፋው ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሰ ፤ በይሁዳም ፡ ደግሞ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ተገኘ ።

13 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በረታ ፡ ንጉሥም ፡ ኾነ ፤ ሮብዓምም ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ የአርባ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስሙን ፡ ያኖርባት ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በመረጣት ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የዐሞን ፡ ሴት ፡ ናዕማ ፡ ነበረች ።

14 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ አላዘጋጀም ፡ ነበርና ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

15 ፤ የሮብዓምም ፡ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ ነገር ፡ በነቢዩ ፡ ሸማያና ፡ በባለራእዩ ፡ በአዶ ፡ የትውልድ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧ በሮብዓምና ፡ በኢዮርብዓም ፡ መካከልም ፡ በዘመናቸው ፡ ኹሉ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።

16 ፤ ሮብዓምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ አብያ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

______________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። ______________



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 13 ።

1 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮርብዓም ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ አብያ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ኾነ ።

2 ፤ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነገሠ ፤ የእናቱም ፡ ስም ፡ ሚካያ ፡ ነበረ ፥ የገብዓ ፡ ሰው ፡ የኡርኤል ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

3 ፤ በአብያና ፡ በኢዮርብዓም ፡ መካከልም ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ። አብያም ፡ የተመረጡትን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ኀያላን ፡
ሰልፈኛዎች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ወጣ ፤ ኢዮርብዓምም ፡ የተመረጡትን ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡
ሰዎች ፡ ይዞ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተሰለፈ ።

4 ፤ አብያም ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በጽማራይም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡
አለ ፡— ኢዮርብዓምና ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤

5 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መንግሥትን ፡ ለዳዊትና ፡ ለልጆቹ ፡ በጨው ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በእውኑ ፡ አታውቁምን ፧

6 ፤ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያ ፡ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ግን ፡ ተነሥቶ ፡ በጌታው ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ።

7 ፤ ክፉዎች ፡ ሰዎችና ፡ ምናምንቴዎችም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተሰበሰቡ ፤ ሮብዓም ፡ ሕፃንና ፡ ለጋ ፡ በነበረበት ፡
ጊዜ ፥ ሊቋቋሟቸውም ፡ ባልቻለበት ፡ ጊዜ ፥ በሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ በሮብዓም ፡ ላይ ፡ በረቱበት ።

8 ፤ አኹንም ፡ በዳዊት ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ የሚኾነውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ልትቋቋሙ ፡
ታስባላችኹ ። እናንተም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ናችኹ ፥ ኢዮርብዓምም ፡ አማልክት ፡ አድርጎ ፡ የሠራላችኹ ፡
የወርቅ ፡ እንቦሶች ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ።

9 ፤ የአሮንን ፡ ልጆች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ አላሳደዳችኹምን ፧ እንደ ፡ ሌላዎችም ፡ አሕዛብ ፡
ልማድ ፡ ካህናትን ፡ አላደረጋችኹምን ፧ አንድ ፡ ወይፈንና ፡ ሰባት ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ይዞ ፡ ይቀድስ ፡ ዘንድ ፡ የሚመጣ ፡
ኹሉ ፡ አማልክት ፡ ላልኾኑት ፡ ለእነዚያ ፡ ካህን ፡ ይኾናል ።

10 ፤ ለእኛ ፡ ግን ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ አልተውነውም ፤ የእግዚአብሔርም ፡ አገልጋዮች ፡ የአሮን ፡
ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ ሌዋውያኑም ፡ በሥራቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ።

11 ፤ በየጧቱና ፡ በየማታውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ ጣፋጩን ፡ ዕጣን ፡
ያሳርጋሉ ፤ የገጹንም ፡ ኅብስት ፡ በንጹሕ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፥ የወርቁን ፡ መቅረዝና ፡ ቀንዲሎቹንም ፡ ማታ ፡ ማታ ፡
እንዲያበሩ ፡ ያዘጋጃሉ ፤ እኛም ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ እንጠብቃለን ፥ እናንተ ፡ ግን ፡
ትታችኹታል ።

12 ፤ እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ነው ፥ መለከቱንም ፡ የሚነፉ ፡ ካህናቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡
ናቸው ፥ በእናንተም ፡ ላይ ፡ ይጮኻሉ ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ አይበጃችኹምና ፡ ከአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አትዋጉ ።

13 ፤ ኢዮርብዓም ፡ ግን ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ በስተኋላቸው ፡ አዞረ ፤ እነርሱ ፡ በይሁዳ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፡ ድብቅ ፡ ጦሩ ፡
በስተኋላቸው ፡ ነበረ ።

14 ፤ ይሁዳም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ሰልፉ ፡ በፊቱና ፡ በኋላው ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡
ጮኹ ፥ ካህናቱም ፡ መለከቱን ፡ ነፉ ።

15 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ጮኹ ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢዮርብዓምንና ፡ እስራኤልን ፡
ኹሉ ፡ በአብያና ፡ በይሁዳ ፡ ፊት ፡ መታቸው ።

16 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከይሁዳ ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

17 ፤ አብያና ፡ ሕዝቡ ፡ ታላቅ ፡ አመታት ፡ መቷቸው ፤ ከእስራኤልም ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡
ተገድለው ፡ ወደቁ ።

18 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተዋረዱ ፥ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ በአባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

ታምነው ፡ ነበርና ፥ አሸነፉ ።

19 ፤ አብያም ፡ ኢዮርብዓምን ፡ አሳደደው ፥ ከርሱም ፡ ከተማዎቹን ፥ ቤቴልንና ፡ መንደሮቿን ፥ ይሻናንና ፡
መንደሮቿን ፥ ዔፍሮንንና ፡ መንደሮቿን ፡ ወሰደ ።

20 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በአብያ ፡ ዘመን ፡ አልበረታም ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቀሠፈው ፥ ሞተም ።

21 ፤ አብያም ፡ ጸና ፥ ዐሥራ ፡ አራትም ፡ ሚስቶች ፡ አገባ ፥ ኻያ ፡ ኹለትም ፡ ወንዶች ፡ ልጆችንና ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡
ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ወለደ ።

22 ፤ የአብያም ፡ የቀረው ፡ ነገርና ፡ አካኼዱ ፡ የተናገራቸውም ፡ ቃሎች ፡ በነቢዩ ፡ በአዶ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፈዋል ።

____________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 14 ።

1 ፤ አብያም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ አሣ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡
ነገሠ ። በርሱም ፡ ዘመን ፡ ምድሪቱ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ዐረፈች ።

2 ፤ አሣም ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካምና ፡ ቀን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤

3 ፤ የእንግዳዎቹንም ፡ አማልክት ፡ መሠዊያ ፡ የኰረብታውንም ፡ መስገጃዎች ፡ አፈረሰ ፥ ሐውልቶቹንም ፡
ሰበረ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንም ፡ ቈረጠ ፤

4 ፤ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፥ ሕጉንና ፡ ትእዛዙንም ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳን ፡ አዘዘ ።

5 ፤ ከይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎችና ፡ የፀሓይ ፡ ምስሎችን ፡ አስወገደ ፤ መንግሥቱም ፡
በርሱ ፡ ሥር ፡ በሰላም ፡ ተቀመጠች ።

6 ፤ በይሁዳም ፡ ምሽጎች ፡ ከተማዎችን ፡ ሠራ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዕረፍት ፡ ስለ ፡ ሰጠው ፡ ምድሪቱ ፡ ጸጥ ፡ ብላ ፡
ነበር ፥ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ሰልፍ ፡ አልነበረም ።

7 ፤ ይሁዳንም ፦ እነዚህን ፡ ከተማዎች ፡ እንሥራ ፥ ቅጥርም ፡ ግንብም ፡ መዝጊያም ፡ መወርወሪያም ፡
እናድርግባቸው ፤ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ፈለግነው ፡ ምድሪቱ ፡ ገና ፡ በፊታችን ፡ ናት ፤ እኛ ፡
ፈልገነዋል ፥ ርሱም ፡ በዙሪያችን ፡ ዕረፍት ፡ ሰጥቶናል ፡ አለ ። እነርሱም ፡ ሠሩ ፡ አከናወኑም ።

8 ፤ ለአሣም ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ የሚሸከሙ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ የይሁዳ ፡ ሰራዊት ፥ ጋሻም ፡
የሚሸከሙ ፡ ቀስትም ፡ የሚገትሩ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ የብንያም ፡ ሰዎች ፡ ነበሩት ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡
ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

9 ፤ ኢትዮጵያዊውም ፡ ዝሪ ፡ አንድ ፡ ሚልዮን ፡ ሰዎችና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠረገላዎች ፡ ይዞ ፡ ወጣባቸው ፤ ወደ ፡
መሪሳም ፡ መጣ ።

10 ፤ አሣም ፡ ሊጋጠመው ፡ ወጣ ፥ በመሪሳም ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በጽፋታ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ተሰለፉ ።

11 ፤ አሣም ፦ አቤቱ ፥ በብዙም ፡ ኾነ ፡ በጥቂቱ ፡ ማዳን ፡ አይሳንኽም ፤ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡
ታምነናልና ፥ በስምኽም ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ መጥተናልና ፥ ርዳን ፤ አቤቱ ፥ አምላካችን ፡ አንተ ፡
ነኽ ፤ ሰውም ፡ አያሸንፍኽ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ።

12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በአሣና ፡ በይሁዳ ፡ ፊት ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ መታ ፤ ኢትዮጵያውያንም ፡ ሸሹ ።

13 ፤ አሣም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ እስከ ፡ ጌራራ ፡ ድረስ ፡ አሳደዷቸው ፤ ኢትዮጵያውያንም ፡ ፈጽመው ፡
እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ወደቁ ፥ በእግዚአብሔርና ፡ በሰራዊቱ ፡ ፊት ፡ ተሰባብረዋልና ፤ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ ወሰዱ ።

14 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ስለ ፡ ወደቀባቸው ፡ በጌራራ ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩትን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡
መቱ ፤ በከተማዎቹም ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ ብዝበዛ ፡ ነበረና ፡ ከተማዎቹን ፡ ኹሉ ፡ በዘበዙ ።

15 ፤ የከብቶቹንም ፡ በረት ፡ አፈረሱ ፤ እጅግም ፡ ብዙ ፡ በጎችንና ፡ ግመሎችንም ፡ ማረኩ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡



www.ethiopianorthodox.org

ተመለሱ ።

__________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 15 ።

1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በዖዴድ ፡ ልጅ ፡ በዐዛርያስ ፡ ላይ ፡ ኾነ ፤

2 ፤ አሳንም ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ አሳ ፡ ይሁዳና ፡ ብንያም ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ እናንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ስትኾኑ ፡ ርሱ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ ብትፈልጉትም ፡ ይገኝላችኋል ፤ ብትተዉት ፡ ግን ፡ ይተዋችኋል ።

3 ፤ እስራኤልም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ያለእውነተኛ ፡ አምላክ ፥ ያለአስተማሪም ፡ ካህን ፥ ያለሕግም ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

4 ፤ በመከራቸውም ፡ ወደእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሰው ፡ በፈለጉት ፡ ጊዜ ፡ አገኙት ።

5 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ለሚወጣውና ፡ ለሚገባው ፡ ሰላም ፡ አልነበረም ፥ በምድርም ፡ በሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ነበረ ።

6 ፤ እግዚአብሔር ፡ በመከራው ፡ ኹሉ ፡ ያስጨንቃቸው ፡ ነበርና ፥ ወገን ፡ ከወገን ፡ ጋራ ፥ ከተማም ፡ ከከተማ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ።

7 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ለሥራችኹ ፡ ብድራት ፡ ይኾንላችኋልና ፥ በርቱ ፥ እጃችኹም ፡ አይላላ ።

8 ፤ አሳም ፡ ይህን ፡ ቃልና ፡ የነቢዩን ፡ የዖዴድን ፡ ትንቢት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ጸና ፥ ከይሁዳና ፡ ከቢንያምም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ከያዛቸው ፡ ከተማዎች ፡ ጸያፉን ፡ ነገር ፡ አስወገደ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መሠዊያ ፡ ዐደሰ ።

9 ፤ አምላኩም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተጠግተው ፡ ነበርና ፥ ርሱ ፡ ይሁዳንና ፡ ብንያምን ፡ ኹሉ ፥ ከኤፍሬምና ፡ ከምናሴም ፡ ከስምዖንም ፡ መጥተው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የተቀመጡትን ፡ ሰበሰበ ።

10 ፤ አሳም ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተሰበሰቡ ።

11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ካመጡት ፡ ምርኮ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ በሬዎችና ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሠዉ ።

12 ፤ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ ፤

13 ፤ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማይፈልግ ፥ ታናሽ ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፥ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ቢኾን ፥ ይገደል ፡ ዘንድ ፡ ማሉ ።

14 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅና ፡ በእልልታ ፥ በእንቢልታና ፡ በቀንደ ፡ መለከት ፡ ማሉ ።

15 ፤ በፍጹምም ፡ ልባቸው ፡ ምለዋልና ፥ በፍጹምም ፡ ኀሊናቸው ፡ ፈልገውታልና ፥ ርሱም ፡ ተገኝቶላቸዋልና ፥ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ በመሐላው ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዙሪያቸው ፡ ዕረፍት ፡ ሰጣቸው ።

16 ፤ ንጉሡም ፡ አሳ ፡ እናቱን ፡ መዓካን ፡ በማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ጣዖት ፡ ስላደረገች ፡ ከእቴጌነቷ ፡ አዋረዳት ፤ አሳም ፡ ምስሏን ፡ ቈርጦ ፡ ቀጠቀጠው ፥ በቄድሮንም ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ አቃጠለው ።

17 ፤ በኰረብታ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ መስገጃዎች ፡ ግን ፡ ከእስራኤል ፡ አላራቀም ፤ ይኹን ፡ እንጂ ፡ የአሳ ፡ ልብ ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹም ፡ ነበረ ።

18 ፤ አባቱም ፡ የቀደሰውን ፥ ርሱም ፡ የቀደሰውን ፡ ወርቁንና ፡ ብሩን ፥ ልዩ ፡ ልዩውንም ፡ ዕቃ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገባ ።

19 ፤ አሳም ፡ እስከነገሠበት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ሰልፍ ፡ አልነበረም ።

__________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። __________________



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 16 ።

1 ፤ አሣ ፡ በነገሠ ፡ በሠላሳ ፡ ስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ባኦስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ ወደይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሣ ፡ ማንም ፡ መውጣትና ፡ መግባት ፡ እንዳይችል ፡ ራማን ፡ ሠራ ።

2 ፤ አሣም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ ከንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ወስዶ ፦

3 ፤ በአባቴና ፡ በአባትኽ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በእኔና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ ይኹናል ፤ እንሆ ፥ ብርና ፡
ወርቅ ፡ ሰድጄልኻለኊ ፤ ርሱ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንዲርቅ ፡ ኼደኽ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከባኦስ ፡ ጋራ ፡ ያለኽን ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ አፍርስ ፡ ብሎ ፡ በደማስቆ ፡ ወደተቀመጠው ፡ ወደሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ሰደደ ።

4 ፤ ወልደ ፡ አዴር ፡ ንጉሡን ፡ አሣን ፡ ዕሺ ፡ አለው ፥ የሰራዊቱም ፡ አለቃዎች ፡ በእስራኤል ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡
ሰደደ ፤ እነርሱም ፡ ዒዮንንና ፡ ዳንን ፡ አቤልማይምንና ፡ የንፍታሌምን ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ ከተማዎች ፡ ዥሉ ፡ መቱ ።

5 ፤ ባኦስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ራማን ፡ መሥራት ፡ ተወ ፥ ሥራውንም ፡ አቋረጠ ።

6 ፤ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ የይሁዳን ፡ ሰዎች ፡ ዥሉ ፡ ሰበሰበ ፤ ባኦስ ፡ ይሠራበት ፡ የነበረውን ፡ የራማን ፡ ድንጋይና ፡ ዕንጨት ፡
አስወገዱ ፥ ርሱም ፡ ጌባንና ፡ ምጽጳን ፡ ሠራበት ።

7 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ባለራእዩ ፡ ዐናኒ ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሣ ፡ መጥቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ በሶርያ ፡ ንጉሥ ፡
ታምነኻልና ፥ በአምላክኽም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አልታመንኽምና ፡ ስለዚህ ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ጭፍራ ፡ ከእጅኽ ፡
አምልጧል ።

8 ፤ ኢትዮጵያውያንና ፡ የልብያ ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሠረገላዎችና ፡ ፈረሰኛዎች ፡ የነበሯቸው ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡
ጭፍራ ፡ አልነበሩምን ፦ በእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ታመንኽ ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥

9 ፤ እግዚአብሔር ፥ ልቡ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ፍጹም ፡ የኾነውን ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፥ ዐይኖቹ ፡ በምድር ፡ ዥሉ ፡
ይመለከታሉና ፦ አኹንም ፡ስንፍና ፡ አድርገኻል ። ስለዚህም ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ ሰልፍ ፡ ይኾንብኻል ።

10 ፤ አሣም ፡ በባለራእዩ ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ተቈጥቷልና ፥ በግዞት ፡ አኖረው ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ አሣ ፡
ከሕዝቡ ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎችን ፡ አስጨነቀ ።

11 ፤ የአሣም ፡ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

12 ፤ በነገሠም ፡ በሠላሳ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ አሣ ፡ እግሩን ፡ ታመመ ፤ ደዌውም ፡ ጸናበት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በታመመ ፡
ጊዜ ፡ ባለመድኀኒቶችን ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አልፈለገም ።

13 ፤ አሣም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በነገሠም ፡ በአርባ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ሞተ ።

14 ፤ ለርሱም ፡ ለራሱ ፡ በሠራው ፡ መቃብር ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ቀበሩት ፤ በቀማሚ ፡ ብልኀት ፡ የተሰናዳ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
መልካም ፡ ሽቱ ፡ በተሞላ ፡ ዐልጋ ፡ ላይም ፡ አኖሩት ፤ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ የመቃብር ፡ ወግ ፡ አደረጉለት ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ምዕራፍ ፡ 17 ።

1 ፤ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ነገሠ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ጠነከረ ።

2 ፤ በተመሸጉትም ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ዥሉ ፡ ወታደሮችን ፡ አኖረ ፥ በይሁዳም ፡ አገር ፡ አባቱም ፡ አሣ ፡
በወሰዳቸው ፡ በኤፍሬም ፡ ከተማዎች ፡ ዘበኛዎችን ፡ አስቀመጠ ።

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከኢዮሳፍጥ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ በፊተኛዪቱ ፡ በአባቱ ፡ በዳዊት ፡ መንገድ ፡ ኼዷልና ፥ በዓሊምንም ፡
አልፈለገምና ፤

4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአባቱን ፡ አምላክ ፡ ፈለገ ፥ በትእዛዙም ፡ ኼደ ፥ የእስራኤልንም ፡ ሥራ ፡ አልሠራም ።

5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መንግሥቱን ፡ በእጁ ፡ አጸና ፤ ይሁዳም ፡ ዥሉ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ለኢዮሳፍጥ ፡ አመጣ ፤ እጅግም ፡
ብዙ ፡ ብልጥግናና ፡ ክብር ፡ ኾነለት ።



www.ethiopianorthodox.org

6 ፤ ልቡም ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎችና ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዱንም ፡ ከይሁዳ ፡ አስወገደ ።

7 ፤ በነገሠም ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ መሳፍንቱን ፥ ቤንኀይልን ፥ ዐብድያስን ፥ ዘካርያስን ፥ ናትናኤልን ፥ ሚክያስን ፥ ሰደደ ።

8 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌዋውያንን ፡ ሸማያን ፥ ነታንያን ፥ ዝባድያን ፥ ዐሳሄልን ፥ ሰሚራሞትን ፥ ዮናታንን ፥ አዶንያስን ፥ ጦብያን ፥ ጦባዶንያን ፡ ሰደደ ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ካህናቱን ፡ ኤሊሳማንና ፡ ኢዮራምን ፡ ሰደደ ።

9 ፤ እነርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የሕጉን ፡ መጽሐፍ ፡ ይዘው ፡ በይሁዳ ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ፤ ወደይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ዅሉ ፡ ኼደው ፡ ሕዝቡን ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ።

10 ፤ በይሁዳም ፡ ዙሪያ ፡ በነበሩ ፡ መንግሥታት ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ድንጋጤ ፡ ኾነ ፥ ከኢዮሳፍጥም ፡ ጋራ ፡ አልተዋጉም ።

11 ፤ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ለኢዮሳፍጥ ፡ እጅ ፡ መንሻና ፡ የብር ፡ ግብር ፡ ያመጡ ፡ ነበር ፤ ዐረባውያንም ፡ ደግሞ ፡ ከመንጋዎቻቸው ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አውራ ፡ በጎችና ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ።

12 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ እየበረታና ፡ እጅግም ፡ እየከበረ ፡ ኼደ ፤ በይሁዳም ፡ ግንቦችንና ፡ የጐተራ ፡ ከተማዎችን ፡ ሠራ ።

13 ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰልፈኛዎች ፡ ነበሩት ።

14 ፤ ቍጥራቸውም ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ከይሁዳ ፡ ሻለቃዎች ፡ አለቃው ፡ ዓድና ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤

15 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ አለቃው ፡ ይሆሐናን ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ዅለት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤

16 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ በፈቃዱ ፡ ራሱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የቀደሰ ፡ የዝክሪ ፡ ልጅ ፡ ዓማስያ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ዅለት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

17 ፤ ከብንያምም ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ የነበረው ፡ ኤሊዳሄ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ቀስትና ፡ ጋሻ ፡ የሚይዙ ፡ ዅለት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤

18 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የዛባት ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ለሰልፍ ፡ የተዘጋጁ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

19 ፤ ንጉሡ ፡ በተመሸጉ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ዅሉ ፡ ካኖራቸውም ፡ ሌላ ፡ እነዚህ ፡ ንጉሡን ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ።

____________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 18 ።

1 ፤ ለኢዮሳፍጥም ፡ ብዙ ፡ ብልጥግናና ፡ ክብር ፡ ነበረው ፤ ለአክአብም ፡ ጋብቻ ፡ ኾነ ።

2 ፤ ከጥቂት ፡ ዓመት ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ አክአብ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ወረደ ። አክአብም ፡ ለርሱና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ለነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ብዙ ፡ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፡ ዐረደ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ አባበለው ።

3 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ አክአብ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ትኼዳለኽን ፧ አለው ። ርሱም ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ነኝ ፥ ሕዝቤም ፡ እንደ ፡ ሕዝብኽ ፡ ናቸው ፤ በሰልፍም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንኾናለን ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

4 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አስቀድመኽ ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

5 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ነቢያቱን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ሰብስቦ ፦ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡ ልኺድን ፧ ወይስ ፡ ልቅር ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፥ ውጣ ፡ አሉት ።



www.ethiopianorthodox.org

6 ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ ግን ፦ እንጠይቀው ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነቢይ ፡ የኾነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ አይገኝምን ፧ አለ ።

7 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ እግዚአብሔርን ፡ የምንጠይቅበት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹል ፡
ጊዜ ፡ ክፉ ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ መልካም ፡ ትንቢት ፡ አይነግርልኝምና ፡ እጠላዋለኹ ፤ ርሱም ፡ የይምላ ፡ ልጅ ፡ ሚክያስ ፡ ነው ፡
አለው ። ኢዮሳፍጥም ፦ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ አይበል ፡ አለው ።

8 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ አንድ ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ጠርቶ ፦ የይምላን ፡ ልጅ ፡ ሚክያስን ፡ ፈጥነኽ ፡ አምጣው ፡ አለው ።

9 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሰው ፡ በሰማርያ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡
አጠገብ ፡ በአደባባይ ፡ በዙፋኖቻቸው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ ነቢያትም ፡ ኹሉ ፡ በፊታቸው ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡
ነበር ።

10 ፤ የክንዓና ፡ ልጅ ፡ ሰዴቅያስም ፡ የብረት ፡ ቀንዶች ፡ ሠርቶ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሶርያውያንን ፡
እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በእነዚህ ፡ ትወጋለኽ ፡ አለ ።

11 ፤ ነቢያትም ፡ ኹሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ኺድና ፡
ተከናወን ፡ እያሉ ፡ እንዲሁ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

12 ፤ ሚክያስንም ፡ ሊጠራ ፡ የኼደ ፡ መልእክተኛ ፦ እንሆ ፥ ነቢያት ፡ ባንድ ፡ አፍ ፡ ኾነው ፡ ለንጉሡ ፡ መልካም ፡
ይናገራሉ ፤ ቃልኽም ፡ እንደ ፡ ቃላቸው ፡ እንዲኾን ፡ መልካም ፡ እንድትናገር ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

13 ፤ ሚክያስም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! አምላኬ ፡ የሚለውን ፡ ርሱን ፡ እናገራለኹ ፡ አለ ።

14 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፦ ሚክያስ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡
እንኺድን ፧ ወይስ ፡ እንቅር ፧ አለው ። ርሱም ፦ ውጣ ፥ ተከናወን ፤ በእጅኽም ፡ ዐልፈው ፡ ይሰጣሉ ፡ አለ ።

15 ፤ ንጉሡም ፦ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከእውነት ፡ በቀር ፡ እንዳትነግረኝ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ አምልኻለኹ ፧ አለው ።

16 ፤ ርሱም ፦ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ጠባቂ ፡ እንደሌላቸው ፡ በጎች ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተበትነው ፡
አየኹ ፤ እግዚአብሔርም ፦ ለእነዚህ ፡ ጌታ ፡ የላቸውም ፥ እያንዳንዱም ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡
ተናገረ ።

17 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ክፉ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ትንቢት ፡ አይናገርልኝም ፡
አላልኹኽምን ፧ አለው ።

18 ፤ ሚክያስም ፡ አለ ፦ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ እግዚአብሔር ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፥ የሰማይም ፡
ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ በቀኙና ፡ በግራው ፡ ቆመው ፡ አየኹ ።

19 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ወጥቶ ፡ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ይወድቅ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ አክአብን ፡ የሚያታልል ፡
ማን ፡ ነው ፧ አለ ። አንዱም ፡ እንደዚህ ፥ ሌላውም ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ።

20 ፤ መንፈስም ፡ መጣ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፦ እኔ ፡ አታልለዋለኹ ፡
አለ ። እግዚአብሔርም ፦ በምን ፧ አለው ።

21 ፤ ርሱም ፦ ወጥቼ ፡ በነቢያቱ ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስ ፡ እኾናለኹ ፡
አለ ። እግዚአብሔርም ፦ ታታልለዋለኽ ፤ ይቀናኻል ፤ ውጣ ፥ እንዲህም ፡ አድርግ ፡ አለ ።

22 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእነዚህ ፡ በነቢያትኽ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስን ፡
አድርጓል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ተናግሮብኻል ።

23 ፤ የክንዓናም ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ቀረበ ፥ ሚክያስንም ፡ በጥፊ ፡ መታውና ፦ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ከአንተ ፡
ጋራ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ በምን ፡ መንገድ ፡ ከእኔ ፡ ዐለፈ ፧ አለ ።

24 ፤ ሚክያስም ፦ እንሆ ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ልትሸሸግ ፡ ወደ ፡ ዕልፍኝኽ ፡ ስትኼድ ፡ ታያለኽ ፡ አለ ።

25 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ። ሚክያስን ፡ ውሰዱ ፥ ወደከተማዪቱም ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ዐሞን ፥ ወደንጉሡም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡
ኢዮአስ ፡ መልሳችኹ ።



www.ethiopianorthodox.org

26 ፤ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በደኅና ፡ እስክመለስ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ በግዞት ፡ አኑሩት ፥ የመከራም ፡ እንጀራ ፡ መግቡት ፥ የመከራም ፡ ውሃ ፡ አጠጡት ፡ በሉ ፡ አለ ።

27 ፤ ሚክያስም ፦ በደኅና ፡ ብትመለስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኔ ፡ የተናገረ ፡ አይደለም ፡ አለ ። ደግሞም ፦ እናንተ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ ስሙኝ ፡ አለ ።

28 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ወጡ ።

29 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥም ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ልብሴን ፡ ለውጬ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እገባለኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ልብስኽን ፡ ልበስ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ልብሱን ፡ ለወጠ ፥ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ ገቡ ።

30 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ የሠረገላዎቹን ፡ አለቃዎች ፦ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በቀር ፡ ትንሽ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ትልቅ ፡ ከማናቸውም ፡ ጋራ ፡ አትጋጠሙ ፡ ብሎ ፡ አዞ ፡ ነበር ።

31 ፤ የሠረገላዎችም ፡ አለቃዎች ፡ ኢዮሳፍጥን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ አሉ ፥ ሊጋጠሙትም ፡ ከበቡት ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ ግን ፡ ጮኽ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ረዳው ፥ አምላኩም ፡ ከርሱ ፡ መለሳቸው ።

32 ፤ የሠረገላዎቹም ፡ አለቃዎች ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እንዳልኾነ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ርሱን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመለሱ ።

33 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ ቀስቱን ፡ በድንገት ፡ ገትሮ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ በጥሩሩ ፡ መጋጠሚያ ፡ በኩል ፡ ሳምባውን ፡ ወጋው ። ሠረገላኛውንም ፦ ተወግቻለኹና ፡ እጅኽን ፡ ግታ ፥ ከሰልፍም ፡ ውስጥ ፡ አውጣኝ ፡ አለው ።

34 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፍ ፡ በረታ ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በሶርያውያን ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ራሱን ፡ ይደግፍ ፡ ነበር ፤ ፀሓይም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ።

___________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ። _________________

ምዕራፍ ፡ 19 ።

1 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደኅና ፡ ተመለሰ ።

2 ፤ ባለራእዩ ፡ የዐናኒ ፡ ልጅ ፡ ኢዩ ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ፥ ንጉሡንም ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ከሓዲውን ፡ ታግዛለኽን ፧ ወይስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚጠሉትን ፡ ትወዳለኽን ፧ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ቍጣ ፡ ኾኖብኻል ።

3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹን ፡ ከምድር ፡ አስወግደኻልና ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ትፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ልብኽን ፡ አዘጋጅተኻልና ፥ መልካም ፡ ነገር ፡ ተገኝቶብኻል ፡ አለው ።

4 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጠ ፤ ደግሞም ፡ ከቤርሳቤሕ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ተራራማው ፡ እስከኤፍሬም ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ወጥቶ ፡ ወዳባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መለሳቸው ።

5 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ በተመሸጉት ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ በያንዳንዱ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ፈራጆች ፡ አኖረ ።

6 ፤ ፈራጆቹንም ፦ ለእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ አትፈርዱምና ፥ ርሱም ፡ በፍርድ ፡ ነገር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ የምታደርጉትን ፡ ተመልከቱ ።

7 ፤ አኹንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ በአምላካችንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በደልና ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ ማድላት ፡ መማለጃም ፡ መውሰድ ፡ የለምና ፡ ኹሉን ፡ ተጠንቅቃችኹ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ።

8 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ከሌዋውያንና ፡ ከካህናት ፡ ከእስራኤልም ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፥ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ፍርድን ፡ እንዲፈርዱ ፡ ክርክርንም ፡ እንዲቈርጡ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሾመ ። እነርሱም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ።

9 ፤ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፦ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ በቅንነትም ፡ በፍጹምም ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

10 ፤ በከተማዎቻቸውም ፡ ከተቀመጡት ፡ ከወንድሞቻችኹ ፡ በደምና ፡ በደም ፡ መካከል ፡ በሕግና ፡ በትእዛዝ ፡ በሥርዐትና ፡ በፍርድም ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ቢመጣ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳይበድሉ ፥ ቍጣም ፡ በእናንተና ፡ በወንድሞቻችኹ ፡ ላይ ፡ እንዳይመጣ ፡ አስጠንቅቋቸው ፤ እንዲህም ፡ ብታደርጉ ፡ በደለኛዎች ፡ አትኾኑም ።



www.ethiopianorthodox.org

11 ፤ እንሆም ፥ ለእግዚአብሔር ፡ በሚኾነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ አማርያ ፥ በንጉሡም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የይስማኤል ፡ ልጅ ፡ ዝባድያ ፡ በላያችኹ ፡ ተሾመዋል ፤ ሌዋውያኑም ፡ ደግሞ ፡ በፊታችኹ ፡ አለቃዎች ፡ ይኾናሉ ፤ በርትታችኹም ፡ አድርጉ ፥ እግዚአብሔርም ፡ መልካም ፡ ከሚያደርግ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ምዕራፍ ፡ 20 ።

1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሞዐብና ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ምዑናውያን ፡ ኢዮሳፍጥን ፡ ሊወጉ ፡ መጡ ።

2 ፤ ወሬኛዎችም ፡ መጥተው ፦ ከባሕሩ ፡ ማዶ ፡ ከሶርያ ፡ ታላቅ ፡ ሰራዊት ፡ መጥቶብኻል ፤ እንሆም ፥ ዐይንጋዲ ፡ በተባለች ፡ በሐሴሶን ፡ ታማር ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ለኢዮሳፍጥ ፡ ነገሩት ።

3 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ፈራ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ሊፈልግ ፡ ፊቱን ፡ አቀና ፤ በይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ ጾም ፡ ዐወጀ ።

4 ፤ ይሁዳም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ተከማቸ ፤ ከይሁዳ ፡ ከተማዎችም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ መጡ ።

5 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ጉባኤ ፡ መካከል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በዐዲሱ ፡ አደባባይ ፡ ፊት ፡ ቆመ ፤

6 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ አቤቱ ፡ የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በሰማይ ፡ ያለኽ ፡ አምላክ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧ የአሕዛብንስ ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧ ኀይልና ፡ ችሎታ ፡ በእጅኽ ፡ ነው ፥ ሊቋቋምኽም ፡ የሚችል ፡ የለም ።

7 ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ምድር ፡ የነበሩትን ፡ አሕዛብ ፡ ከሕዝብኽ ፡ ከእስራኤል ፡ ፊት ፡ ያሳደድኽ ፥ ለወዳጅኽም ፡ ለአብርሃም ፡ ዘር ፡ ለዘለዓለም ፡ የሰጠኻት ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧

8 ፤ እነርሱም ፡ የተቀመጡባት ፥ ለስምኽም ፡ መቅደስን ፡ ሠርተውባት ።

9 ፤ ክፉ ፡ ነገር ፥ የፍርድ ፡ ሰይፍ ፡ ወይም ፡ ቸነፈር ፡ ወይም ፡ ራብ ፥ ቢመጣብን ፡ ስምኽ ፡ ባለበት ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ ፊትና ፡ በፊትኽ ፡ ቆመን ፡ በመከራችን ፡ ወዳንተ ፡ እንጮኻለን ፥ አንተም ፡ ሰምተኽ ፡ ታድነናለኽ ፡ አሉ ።

10 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ያልፉባቸው ፡ ዘንድ ፡ ያልፈቀድኽላቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ፈቀቅ ፡ ብለው ፡ ያላጠፏቸው ፥ የዐሞንና ፡ የሞዐብ ፡ ልጆች ፡ የሴይርም ፡ ተራራ ፡ ሰዎች ፥

11 ፤ እንሆ ፥ ለወሮታችን ፡ ክፋት ፡ ይመልሱልናል ፤ ከሰጠኸንም ፡ ርስት ፡ ያወጡን ፡ ዘንድ ፡ መጥተዋል ።

12 ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ አትፈርድባቸውምን ፧ ይህን ፡ የመጣብንን ፡ ታላቅ ፡ ወገን ፡ እንቃወም ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ፤ የምናደርገውንም ፡ አናውቅም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐይኖቻችን ፡ ወዳንተ ፡ ናቸው ።

13 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከሕፃናታቸውና ፡ ከሚስቶቻቸው ፡ ከልጆቻቸውም ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ከአሣፍ ፡ ወገን ፡ በነበረው ፡ በሌዋዊው ፡ በማታንያ ፡ ልጅ ፡ በይዒኤል ፡ ልጅ ፡ በበናያስ ፡ ልጅ ፡ በዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ በየሕዚኤል ፡ ላይ ፡ በጉባኤው ፡ መካከል ፡ መጣ ፤

15 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የምትኖሩ ፥ አንተም ፡ ንጉሡ ፡ ኢዮሳፍጥ ፥ ስሙ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላችኋል ። ሰልፉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእናንተ ፡ አይደለምና ፡ ከዚህ ፡ ታላቅ ፡ ወገን ፡ የተነሣ ፡ አትፍሩ ፥ አትደንግጡም ።

16 ፤ ነገ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ውረዱ ፤ እንሆ ፥ በጺጽ ፡ ዐቀበት ፡ ይወጣሉ ፤ በሸለቆውም ፡ መጨረሻ ፡ በይሩኤል ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ታገኟቸዋላችኹ ።

17 ፤ እናንተ ፡ በዚህ ፡ ሰልፍ ፡ የምትዋጉ ፡ አይደላችኹም ፤ ይሁዳና ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ተሰለፉ ፥ ዝም ፡ ብላችኹ ፡ ቁሙ ፥ የሚኾነውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መድኀኒት ፡ እዩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ነውና ፥ አትፍሩ ፥ አትደንግጡም ፥ ነገም ፡ ውጡባቸው ።

18 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፋ ፡ ይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደቁ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ሰገዱ ።

19 ፤ ሌዋውያንም ፥ የቀአት ፡ ልጆችና ፡ የቆሬ ፡ ልጆች ፥ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በእጅግ ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ ቆሙ ።

20 ፤ ማልደውም ፡ ተነሡ ፥ ወደቴቁሔም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጡ ፤ ሲወጡም ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ቆመና ፦ ይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ፥ ትጸኑማላችኹ ፤ በነቢያቱም ፡ እመኑ ፥ ነገሩም ፡ ይሰላላችኋል ፡ አለ ።

21 ፤ ከሕዝቡም ፡ ጋራ ፡ ተማክሮ ፡ በሰራዊቱ ፡ ፊት ፡ የሚኼዱትን ፦ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ የሚሉትንም ፥ ጌጠኛ ፡ ልብስም ፡ ለብሰው ፡ የሚያመሰግኑትን ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የሚዘምሩትን ፡ መዘምራን ፡ አቆመ ።

22 ፤ ዝማሬውንና ፡ ምስጋናውንም ፡ በዠመሩ ፡ ጊዜ ፡ ይሁዳን ፡ ሊወጉ ፡ በመጡት ፡ በዐሞንና ፡ በሞዐብ ፡ ልጆች ፡ በሴይርም ፡ ተራራ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድብቅ ፡ ጦርን ፡ አመጣባቸው ፤ እነርሱም ፡ ተመቱ ።

23 ፤ የዐሞንና ፡ የሞዐብ ፡ ልጆችም ፡ በሴይር ፡ ተራራ ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ ፈጽመው ፡ ይገድሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ያጠፏቸውም ፡ ዘንድ ፡ ተነሥተውባቸው ፡ ነበር ፤ በሴይርም ፡ የሚኖሩትን ፡ ካጠፉ ፡ በኋላ ፡ እያንዳንዱ ፡ ባልንጀራውን ፡ ለማጥፋት ፡ ተረዳዳ ።

24 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ወደምድረ ፡ በዳ ፡ ግንብ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ አዩ ፤ እንሆም ፥ በምድሩ ፡ ኹሉ ፡ ሬሳ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር ፥ ያመለጠም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

25 ፤ ኢዮሳፍጥና ፡ ሕዝቡም ፡ ምርኮ ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ ፡ መጡ ፡ ብዙ ፡ ከብትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃም ፥ ልብስም ፥ እጅግም ፡ ያማረ ፡ ዕቃ ፡ አገኙ ፥ በዘበዙትም ፥ ኹሉንም ፡ ይሸከሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፤ ከምርኮውም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ይበዘብዙ ፡ ነበር ።

26 ፤ በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ በበረከት ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ተሰበሰቡ ፥ በዚያም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባረኩ ፤ ስለዚህም ፡ ያ ፡ ስፍራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የበረከት ፡ ሸለቆ ፡ ተባለ ።

27 ፤ የይሁዳና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፥ በፊታቸውም ፡ ኢዮሳፍጥ ፥ እግዚአብሔር ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ አሠኝቷቸዋልና ፥ በደስታ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሱ ።

28 ፤ በበገናም ፡ በመሰንቆም ፡ በመለከትም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ገቡ ።

29 ፤ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤልን ፡ ጠላቶች ፡ እንደ ፡ ወጋ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍርሀት ፡ ኾነ ።

30 ፤ የኢዮሳፍጥም ፡ መንግሥት ፡ ጸጥ ፡ አለች ፥ አምላኩም ፡ በዙሪያው ፡ ካሉ ፡ አሳረፈው ።

31 ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፤ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜም ፡ የሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የሺልሒ ፡ ልጅ ፡ ዓዙባ ፡ ነበረች ።

32 ፤ በአባቱም ፡ በአሣ ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፥ ከርሱም ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ አደረገ ።

33 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ ልባቸውን ፡ ወዳባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ አላዘጋጁም ፡ ነበር ።

34 ፤ የቀረውም ፡ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ በዐናኒ ፡ ልጅ ፡ በኢዩ ፡ ታሪክ ፡ ተጽፏል ።

35 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ሥራው ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ከኾነ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከአካዝያስ ፡ ጋራ ፡ ተባበረ ።



www.ethiopianorthodox.org

36 ፤ ወደ ፡ ተርሴስም ፡ የሚኼዱትን ፡ መርከቦች ፡ ያሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ኾኑ ፤ መርከቦቹንም ፡ በዔጽዮንጋብር ፡ አሠሩ ።

37 ፤ የመሪሳም ፡ ሰው ፡ የዶዳያ ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፦ ከአካዝያስ ፡ ጋራ ፡ ተባብረኻልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ሥራኽን ፡ አፍርሶታል ፡ ብሎ ፡ በኢዮሳፍጥ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ። መርከቦቹም ፡ ተሰበሩ ፥ ወደ ፡ ተርሴስም ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

______________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 21 ።

1 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ኢዮራም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

2 ፤ ለርሱም ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ልጆች ፡ ዐዛርያስ ፥ ይሒኤል ፥ ዘካርያስ ፥ ዔዛርያስ ፥ ሚካኤል ፥ ሰፋጥያስ ፡ የሚባሉ ፡ ወንድሞች ፡ ነበሩት ፤ እነዚህ ፡ ዅሉ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

3 ፤ አባታቸውም ፡ ብዙ ፡ ስጦታ ፥ ብርና ፡ ወርቅ ፥ የከበረም ፡ ዕቃ ፥ በይሁዳም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጣቸው ፤ መንግሥቱን ፡ ግን ፡ በኵር ፡ ልጁ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለኢዮራም ፡ ሰጠ ።

4 ፤ ኢዮራምም ፡ በአባቱ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፡ ወንድሞቹን ፡ ዅሉ ፡ ሌላዎችንም ፡ የእስራኤልን ፡ መሳፍንት ፡ በሰይፍ ፡ ገደለ ።

5 ፤ ኢዮራምም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

6 ፤ የአክአብንም ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ነበርና ፥ የአክአብ ፡ ቤት ፡ እንዳደረገ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ስላደረገው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፥ ለርሱና ፡ ለልጆቹም ፡ በዘመናት ፡ ዅሉ ፡ መብራት ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ስለሰጠው ፡ ተስፋ ፥ እግዚአብሔር ፡ የዳዊትን ፡ ቤት ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ።

8 ፤ በርሱም ፡ ዘመን ፡ ኤዶምያስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ፥ ለራሱም ፡ ንጉሥ ፡ አነገሠ ።

9 ፤ ኢዮራምም ፡ ከአለቃዎቹና ፡ ከሠረገላዎቹ ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፡ ተሻገረ ፤ በሌሊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ርሱንና ፡ የሠረገላዎቹን ፡ አለቃዎች ፡ ከበው ፡ የነበሩትን ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰዎች ፡ መታ ።

10 ፤ ኤዶምያስ ፡ ግን ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ዐመፀ ፥ በዚያንም ፡ ዘመን ፡ ልብና ፡ ደግሞ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ፥ የአባቶቹን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትቶ ፡ ነበርና ።

11 ፤ ደግሞም ፡ በይሁዳ ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ መስገጃዎችን ፡ ሠራ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የተቀመጡትን ፡ እንዲያመነዝሩ ፡ አደረጋቸው ፥ ይሁዳንም ፡ አሳተው ።

12 ፤ ከነቢዩም ፡ ከኤልያስ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ መጣባት ፦ የአባትኽ ፡ የዳዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በአባትኽ ፡ በኢዮሳፍጥ ፡ መንገድ ፡ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ መንገድ ፡ አልኼድኽምና ፥

13 ፤ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ ኼደኻልና ፥ የአክአብም ፡ ቤት ፡ እንዳደረገ ፡ ይሁዳንና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ እንዲያመነዝሩ ፡ አድርገኻልና ፥ ከአንተም ፡ የሚሻሉትን ፡ የአባትኽን ፡ ቤት ፡ ወንድሞችኽን ፡ ገድለኻልና ፥

14 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕዝብኽንና ፡ ልጆችኽን ፡ ሚስቶችኽንም ፡ ያለኽንም ፡ ዅሉ ፡ በታላቅ ፡ መቅሠፍት ፡ ይቀሥፋል ።

15 ፤ አንተም ፡ ከደዌው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ አንዠትኽ ፡ በየዕለቱ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ በክፉ ፡ የአንዠት ፡ ደዌ ፡ ትታመማለኽ ።

16 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የፍልስጥኤማውያንና ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ አጠገብ ፡ የሚኖሩትን ፡ የዐረባውያንን ፡ መንፈስ ፡ በኢዮራም ፡ ላይ ፡ አስነሣ ።



www.ethiopianorthodox.org

17 ፤ ወደ ፡ ይሁዳም ፡ ወጡ ፥ አፈረሷትም ፥ የንጉሡንም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፥ ወንዶች ፡ ልጆቹንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹንም ፡ ማረኩ ፤ ከታናሹም ፡ ልጅ ፡ ከአካዝያስ ፡ በቀር ፡ ልጅ ፡ አልቀረለትም ።

18 ፤ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ በማይፈወስ ፡ ደዌ ፡ አንጀቱን ፡ ቀሠፈው ።

19 ፤ ከቀንም ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ከኹለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከደዌው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ አንጀቱ ፡ ወጣ ፥ በክፉም ፡ ደዌ ፡ ሞተ ። ሕዝቡም ፡ ለአባቶቹ ፡ ያደርገው ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ለርሱ ፡ የመቃብር ፡ ወግ ፡ አላደረገም ።

20 ፤ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ ማንም ፡ ሳያዝንለት ፡ ኼደ ፤ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ እንጂ ፡ በነገሥታት ፡ መቃብር ፡ አልቀበሩትም ።

__________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 22 ።

1 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩትም ፡ ታናሹን ፡ ልጁን ፡ አካዝያስን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡት ። የመጣባቸው ፡ የዐረብና ፡ የአሊማዞን ፡ የሽፍቶች ፡ ጭፍራ ፡ የርሱን ፡ ታላቆች ፡ ገድለዋቸው ፡ ነበርና ። የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ ነገሠ ።

2 ፤ አካዝያስም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜው ፡ አርባ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ጎቶሊያ ፡ የተባለች ፡ የዘንበሪ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

3 ፤ እናቱም ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ ትመክረው ፡ ነበርና ፥ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በአክአብ ፡ ቤት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ።

4 ፤ አባቱም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የአክአብ ፡ ቤት ፡ እንዳደረገ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ መካሪዎች ፡ ነበሩትና ።

5 ፤ በምክራቸውም ፡ ኼደ ፥ ከእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ከአክአብ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮራም ፡ ጋራ ፡ የሶርያን ፡ ንጉሥ ፡ አዛሄልን ፡ በሬማት ፡ ዘገለአድ ፡ ሊዋጋ ፡ ኼደ ፤ ሶርያውያንም ፡ ኢዮራምን ፡ አቈሰሉት ።

6 ፤ ከሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ከአዛሄል ፡ ጋራ ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ሶርያውያን ፡ በሬማት ፡ ያቈሰሉትን ፡ ቊስል ፡ ይታከም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ተመለሰ ፤ ታሞም ፡ ነበርና ፥ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ የአክአብን ፡ ልጅ ፡ ኢዮራምን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ወረደ ።

7 ፤ አካዝያስም ፡ ወደ ፡ ኢዮራም ፡ በመምጣቱ ፡ ይጠፋ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነበረ ፤ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ ከኢዮራም ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአክአብን ፡ ቤት ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወደቀባው ፡ ወደናሜሲ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዩ ፡ ወጣ ።

8 ፤ ኢዩም ፡ በአክአብ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ ሲፈጽም ፡ የይሁዳን ፡ መሳፍንትና ፡ አካዝያስን ፡ ያገለግሉ ፡ የነበሩትን ፡ የአካዝያስን ፡ ወንድሞች ፡ ልጆች ፡ አግኝቶ ፡ ገደላቸው ።

9 ፤ አካዝያስንም ፡ ፈለገው ፥ በሰማርያ ፡ ተሸሽጎ ፡ ሳለ ፡ አገኙት ፤ ወደ ፡ ኢዩም ፡ አምጥተው ፡ ገደሉትና ፦ በፍጹም ፡ ልብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የፈለገው ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቀበሩት ። ከአካዝያስም ፡ ቤት ፡ ማንም ፡ መንግሥትን ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ አልነበረም ።

10 ፤ የአካዝያስም ፡ እናት ፡ ጎቶሊያ ፡ ልጇ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተነሥታ ፡ የይሁዳን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ አጠፋች ።

11 ፤ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ዮሳቤት ፡ ግን ፡ ከተገደሉት ፡ ከንጉሡ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ የአካዝያስን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአስን ፡ ሰርቃ ፡ ወሰደች ፤ ርሱንና ፡ ሞግዚቱን ፡ በዕልፍኝ ፡ ውስጥ ፡ አኖረቻቸው ፤ ጎቶሊያ ፡ እንዳታስገድለው ፡ የንጉሡ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ የአካዛያስ ፡ እኅት ፡ የካህኑ ፡ የዮዳዔ ፡ ሚስት ፡ ዮሳቤት ፡ እንዲሁ ፡ ሸሸገችው ።

12 ፤ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ተሸሽጎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ተቀመጠ ፤ ጎቶልያም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነገሠች ።

__________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ። __________________



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 23 ።

1 ፤ በሰባተኛውም ፡ ዓመት ፡ ዮዳዔ ፡ በረታ ፥ የመቶ ፡ አለቃዎቹንም ፥ የይሮሐምን ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስን ፥ የይሆሐናንንም ፡
ልጅ ፡ ይስማኤልን ፥ የዖቤድንም ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስን ፥ የዓዳያንም ፡ ልጅ ፡ መዕሴያን ፥ የዝክሪንም ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፉጥን ፡
ወስዶ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

2 ፤ ይሁዳንም ፡ ዞሩ ፥ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ሌዋውያንንና ፡ የእስራኤልን ፡ አባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡
ሰብስበው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

3 ፤ ጉባኤውም ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ። ዮዳዔም ፡
አላቸው ፡— እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለዳዊት ፡ ልጆች ፡ አንደ ፡ ተናገረ ፡ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ይነግሣል ።

4 ፤ የምታደርጉት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ከምትገቡት ፡ ከእናንተ ፡ ከካህናትና ፡ ከሌዋዊውያን ፡ ከሦስት ፡ አንድ ፡
እጅ ፡ በመግቢያ ፡ በሮች ፡ በረኛዎች ፡ ኹኑ ፤

5 ፤ ከሦስት ፡ አንድ ፡ እጅም ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ ኹኑ ፤ አንድ ፡ እጅም ፡ በመካከለኛው ፡ በር ፡ ኹኑ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ይኹኑ ።

6 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ከካህናትና ፡ ከአገልጋዮቹ ፡ ሌዋውያን ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አይግባ ፤ እነርሱ ፡ ቅዱሳን ፡
ናቸውና ፥ ይግቡ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ይጠብቅ ።

7 ፤ ሌዋውያንም ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ንጉሡን ፡ በዙሪያው ፡ ይክበቡት ፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡
የሚገባ ፡ ይገደል ፡ ንጉሡም ፡ ሲገባና ፡ ሲወጣ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኹኑ ።

8 ፤ ሌዋውያንና ፡ ይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ ካህኑ ፡ ዮዳዔ ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ አደረጉ ፤ ካህኑም ፡ ዮዳዔ ፡ ሰሞነኛዎቹን ፡
አላሰናበተም ፡ ነበርና ፥ እያንዳንዱ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ይገቡ ፡ የነበሩትን ፡ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ይወጡ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡
ወሰደ ።

9 ፤ ካህኑም ፡ ዮዳዔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ የንጉሡን ፡ የዳዊትን ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ አላባሽ ፡ አግሬውንም ፡
ጋሻ ፡ ለመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ሰጣቸው ።

10 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ በእጁ ፡ እየያዘ ፡ በንጉሡ ፡ ዙሪያ ፡ ከቤቱ ፡ ቀኝ ፡ እስከቤቱ ፡
ግራ ፡ ድረስ ፡ በመሠዊያውና ፡ በቤቱ ፡ አጠገብ ፡ እንዲቆም ፡ አደረገ ።

11 ፤ የንጉሡንም ፡ ልጅ ፡ አውጥተው ፡ ዘውዱን ፡ ጫኑበት ፥ ምስክሩንም ፡ ሰጡት ፥ አነገሡትም ፤ ዮዳዔና ፡
ልጆቹም ፡— ንጉሡ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ እያሉ ፡ ቀቡት ።

12 ፤ ጎቶሊያም ፡ የሚሮጡትንና ፡ ንጉሡን ፡ የሚያመሰግኑትን ፡ የሕዝቡን ፡ ድምፅ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡
ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መጣች ።

13 ፤ እንሆም ፥ ንጉሡ ፡ በመግቢያው ፡ በዐምዱ ፡ አጠገብ ፡ ኾኖ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ አለቃዎችና ፡ መለከተኛዎች ፡
ቆመው ፡ አየች ። የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ መለከቱን ፡ ይነፉ ፡ ነበር ፤ መዘምራንም ፡ በዜማ ፡ ዕቃ ፡
እያዜሙ ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ፡ ይዘምሩ ፡ ነበር ። ጎቶሊያም ፡ ልብሷን ፡ ቀዳ ፡— ዐመፅ ፡ ነው ፥ ዐመፅ ፡ ነው ፡ ብላ ፡
ጮኸች ።

14 ፤ ካህኑም ፡ ዮዳዔ ፡ በጭፍራው ፡ ላይ ፡ የተሾሙትን ፡ የመቶ ፡ አለቃዎች ፡— ወደ ፡ ሰልፉ ፡ መካከል ፡
አውጧት ፤ የሚከተላትም ፡ በሰይፍ ፡ ይገደል ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ካህኑም ፡— በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡
አትግደሏት ፡ አለ ።

15 ፤ ገለልም ፡ ብለው ፡ አሳለፏት ፤ ርሷም ፡ ወደፈረሱ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ኼደች ፥ በዚያም ፡ ገደሏት ።

16 ፤ ዮዳዔም ፡ በርሱና ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በንጉሡም ፡ መካከል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ አደረገ ።

17 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደበዓል ፡ ቤት ፡ ኼደው ፡ አፈረሱት ፥ መሠዊያዎቹንና ፡ ምስሎቹንም ፡ አደቀቁ ፥ የበዓልንም ፡
ካህን ፡ ማታንን ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ ገደሉት ።



www.ethiopianorthodox.org

18 ፤ ዮዳዔም ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ እንደተጻፈው ፥ እንደ ፡ ዳዊትም ፡ ትእዛዝ ፥ በደስታና ፡ በመዝሙር ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የከፈላቸውን ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ ሾመ ።

19 ፤ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ እንዳይገባ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በር ፡ በረኛዎችን ፡ አኖረ ።

20 ፤ የመቶ ፡ አለቃዎችንም ፥ ከበርቴዎቹንም ፥ የሕዝቡንም ፡ አለቃዎች ፥ የአገሩንም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡
ወሰደ ፥ ንጉሡንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አወረደ ፤ በላይኛውም ፡ በር ፡ በኩል ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡
መጡ ፥ ንጉሡንም ፡ በመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ አኖሩት ።

21 ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፥ ከተማዪቱም ፡ ጸጥ ፡ አለች ፤ ጎቶሊያንም ፡ በሰይፍ ፡ ገደሏት ። ች ፡

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ምዕራፍ ፡ 24 ።

1 ፤ ኢዮአስም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡
ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ሳብያ ፡ የተባለች ፡ የቤርሳቤሕ ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

2 ፤ በካህኑም ፡ በዮዳዔ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ኢዮአስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

3 ፤ ዮዳዔም ፡ ኹለት ፡ ሚስቶች ፡ አጋባው ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንም ፡ ወለደ ።

4 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢዮአስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ይጠግን ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ።

5 ፤ ካህናትንና ፡ ሌዋውያንንም ፡ ሰብስቦ ፦ ወደይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ውጡ ፥ የአምላካችኹንም ፡ ቤት ፡ በየዓመቱ ፡
ለማደስ ፡ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ገንዘብን ፡ ሰብስቡ ፤ ነገሩንም ፡ ፈጥናችኹ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ። ሌዋውያን ፡ ግን ፡ ቸል ፡
አሉ ።

6 ፤ ንጉሡም ፡ አለቃውን ፡ ዮዳዔን ፡ ጠርቶ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ስለምስክሩ ፡ ድንኳን ፡ የእስራኤል ፡
ጉባኤ ፡ እንዲያዋጣ ፡ ያዘዘውን ፡ ግብር ፡ ከይሁዳና ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ሌዋውያንን ፡
አላተጋኻቸውም ፡ አለው ።

7 ፤ ጎቶሊያ ፡ ከሓዲት ፡ ነበረችና ፡ ልጆቿም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አፍርሰዋልና ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡
ተቀድሶ ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ ለበዓሊም ፡ ሰጥተዋልና ።

8 ፤ ንጉሡም ፡ አዘዘ ፥ ሣጥንም ፡ ሠርተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ በስተውጭ ፡ አኖሩት ።

9 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ያዘዘውን ፡ ግብር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያመጡ ፡
ዘንድ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ።

10 ፤ አለቃዎቹና ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ አቀረቡት ፥ እስኪሞላም ፡ ድረስ ፡ በሣጥኑ ፡ ውስጥ ፡ ጣሉት ።

11 ፤ ሣጥኑም ፡ በሌዋውያን ፡ እጅ ፡ ወደንጉሡ ፡ ሹማምት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥ ብዙ ፡ ገንዘብም ፡ እንዳለበት ፡ ባየ ፡
ጊዜ ፥ የንጉሡ ፡ ጸሓፊና ፡ የዋነኛው ፡ ካህን ፡ ሹም ፡ እየመጡ ፡ ብሩን ፡ ከሣጥን ፡ ያወጡ ፡ ነበር ፥ ሣጥኑንም ፡ ደግሞ ፡
ወደ ፡ ስፍራው ፡ ይመልሱት ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ በየቀኑ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፥ ብዙም ፡ ገንዘብ ፡ አከማቹ ።

12 ፤ ንጉሡና ፡ ዮዳዔም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለተሾሙት ፡ ሰጧቸው ፤ እነርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቤት ፡ የሚጠግኑትን ፡ ጠራቢዎችንና ፡ ዐናጢዎችን ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ የሚያድሱትን ፡ የብረትና ፡ የናስ ፡
ሠራተኛዎችን ፡ ይገዙበት ፡ ነበር ።

13 ፤ ሠራተኛዎችም ፡ ሠሩ ፥ የፈረሰውም ፡ በእጃቸው ፡ ተጠገነ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሥራ ፡
መለሱ ፥ አጽንተውም ፡ አቆሙት ።

14 ፤ በጨረሱም ፡ ጊዜ ፡ የተረፈውን ፡ ገንዘብ ፡ በንጉሡና ፡ በዮዳዔ ፡ ፊት ፡ አመጡ ፤ እነርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
ዕቃ ፥ ለአገልግሎትና ፡ ለቍርባን ፡ ዕቃ ፥ ለጭልፋዎችም ፥ ለወርቅና ፡ ለብርም ፡ ዕቃ ፡ አደረጉት ። በዮዳዔም ፡ ዘመን ፡
ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ኹልጊዜ ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

15 ፤ ዮዳዔም ፡ ሸመገለ ፥ ዕድሜም ፡ ጠግቦ ፡ ሞተ ፤ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜው ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

16 ፤ ከእስራኤልም ፡ ጋራ ፥ ከእግዚአብሔርና ፡ ከቤቱም ፡ ጋራ ፡ ቸርነትን ፡ ሠርቷልና ፥ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከነገሥታቱ ፡ ጋራ ፡ ቀበሩት ።

17 ፤ ዮዳዔም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የይሁዳ ፡ አለቃዎች ፡ ገብተው ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሡ ፤ ንጉሡም ፡ ዕሺ ፡ አላቸው ።

18 ፤ የአባቶቻቸውንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችንና ፡ ጣዖታትን ፡ አመለኩ ፤ በዚህ ፡ በደላቸውም ፡ ምክንያት ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ ወረደ ።

19 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመልሷቸው ፡ ዘንድ ፡ ነቢያትን ፡ ይሰድላቸው ፡ ነበር ፤ መሰከሩባቸውም ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ አላደመጡም ።

20 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በካህኑ ፡ በዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በዘካርያስ ፡ ላይ ፡ መጣ ፤ ርሱም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ቆመና ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ለምን ፡ ትተላለፉላችኹ ፧ መልካምም ፡ አይኾንላችኹም ፤ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ተዋችኹ ፡ ርሱ ፡ ትቷችኋል ፡ አላቸው ።

21 ፤ ተማማሉበትም ፡ በንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ውስጥ ፡ በድንጋይ ፡ ወገሩት ።

22 ፤ እንዲሁም ፡ ንጉሡ ፡ ኢዮአስ ፡ ዮዳዔ ፡ ያደረገለትን ፡ ቸርነት ፡ አላሰበም ፥ ልጁንም ፡ ዘካርያስን ፡ አስገደለው ፤ ርሱም ፡ ሲሞት ። እግዚአብሔር ፡ ይየው ፥ ይፈልገውም ፡ አለ ።

23 ፤ ዓመቱም ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የሶርያውያን ፡ ሰራዊት ፡ መጡበት ፤ ወደ ፡ ይሁዳና ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጥተው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ የሕዝቡን ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ አጠፉ ፥ ምርኳቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ላኩ ።

24 ፤ የሶርያውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ቍጥር ፡ ጥቂት ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታላቅን ፡ ሰራዊት ፡ አሳልፎ ፡ በእጃቸው ፡ ሰጣቸው ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ። እነርሱም ፡ በኢዮአስ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ፈረዱበት ።

25 ፤ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ዐልፈው ፡ ከኼዱ ፡ በኋላ ፡ እጅግ ፡ ታሞ ፡ ነበር ፤ የገዛ ፡ ባሪያዎቹም ፡ ስለ ፡ ካህኑ ፡ ስለዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ ተበቅለው ፡ ተማማሉበት ፥ በዐልጋውም ፡ ላይ ፡ ገደሉት ፥ ሞተም ፤ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ እንጂ ፡ በነገሥታት ፡ መቃብር ፡ አልቀበሩትም ።

26 ፤ የተማማሉበትም ፡ የአሞናዊቱ ፡ የሰምዓት ፡ ልጅ ፡ ዛባድ ፥ የሞዐባዊቱም ፡ የሰማሪት ፡ ልጅ ፡ ዮዛባት ፡ ነበሩ ።

27 ፤ የልጆቹና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ነገር ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ማደሱ ፥ እንሆ ፥ በነገሥታቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ። ልጁም ፡ አሜስያስ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

______________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 25 ።

1 ፤ አሜስያስም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱ ፡ ዮዓዳን ፡ የተባለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በፍጹም ፡ ልብ ፡ አይደለም ።

3 ፤ መንግሥትም ፡ በጸናለት ፡ ጊዜ ፡ አባቱን ፡ የገደሉትን ፡ ባሪያዎች ፡ ገደለ ።

4 ፤ በሙሴም ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ እግዚአብሔርም ፦ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በገዛ ፡ ኀጢአቱ ፡ ይሙት ፡ እንጂ ፡ አባቶች ፡ በልጆች ፡ ፋንታ ፡ አይሙቱ ፥ ልጆችም ፡ በአባቶች ፡ ፋንታ ፡ አይሙቱ ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዘ ፡ የነፍሰ ፡ ገዳዮችን ፡ ልጆች ፡ አልገደለም ።

5 ፤ አሜስያስም ፡ ይሁዳን ፡ ሰበሰበ ፥ በያባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ ከሺሕ ፡ አለቃዎችና ፡ ከመቶ ፡ አለቃዎች ፡ እጅ ፡ በታች ፡ አቆማቸው ፤ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉትን ፡ ይሁዳንና ፡ ብንያምን ፡ ኹሉ ፡ ቈጠረ ፥ ለሰልፍም ፡ የሚወጡ ፥ ጋሻና ፡ ጦርም ፡ የሚይዙ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ አገኘ ።



www.ethiopianorthodox.org

6 ፤ ደግሞም ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ በመቶ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ቀጠረ ።

7 ፤ አንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥቶ ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤልና ፡
ከኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ አይደለምና ፡ የእስራኤል ፡ ጭፍራ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አይውጣ ።

8 ፤ ብትኼድ ፡ ግን ፥ በእነርሱም ፡ ማሸነፍን ፡ ብታስብ ፥ የመርዳትና ፡ የመጣል ፡ ኀይል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ነውና ፥ እግዚአብሔር ፡ በጠላቶችኽ ፡ ፊት ፡ ይጥልኻል ፡ አለው ።

9 ፤ አሜስያስም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፦ ለእስራኤል ፡ ጭፍራ ፡ የሰጠኹት ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ ምን ፡
ይኹን ፧ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፦ ከዚህ ፡ አብልጦ ፡ ይሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡
መለሰለት ።

10 ፤ አሜስያስም ፡ ከኤፍሬም ፡ የመጡት ፡ ጭፍራዎች ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ለይቶ ፡
አሰናበታቸው ፤ ስለዚህም ፡ ቍጣቸው ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ጸና ፥ ወደ ፡ አገራቸውም ፡ በጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ተመለሱ ።

11 ፤ አሜስያስም ፡ በረታ ፥ ሕዝቡንም ፡ አውጥቶ ፡ ወደጨው ፡ ሸለቆ ፡ ኼደ ፥ ከሴይርም ፡ ልጆች ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ገደለ ።

12 ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ደግሞ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሰዎችን ፡ በሕይወታቸው ፡ ማረኩ ፥ ወደአለቱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡
አመጧቸው ፤ ከአለቱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጣሏቸው ፥ ኹሉም ፡ ተፈጠፈጡ ።

13 ፤ አሜስያስ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እንዳይኼዱ ፡ ያሰናበታቸው ፡ ጭፍራዎች ፡ ከሰማርያ ፡ ዠምረው ፡
እስከ ፡ ቤትሖሮን ፡ ድረስ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ፥ ከነርሱም ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ገደሉ ፥ ብዙ ፡
ምርኮም ፡ ማረኩ ።

14 ፤ አሜስያስም ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰዎች ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ የሴይርን ፡ ልጆች ፡ አማልክት ፡ አመጣ ፥ የርሱም ፡
አማልክት ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ አቆማቸው ፥ ይሰግድላቸውም ፡ ያጥንላቸውም ፡ ነበር ።

15 ፤ ስለዚህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በአሜስያስ ፡ ላይ ፡ ነደደና ፦ ሕዝባቸውን ፡ ከአንተ ፡ እጅ ፡ ያላዳኑትን ፡
የአሕዛብን ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ፈለግኻቸው ፧ የሚል ፡ ነቢይ ፡ ሰደደበት ።

16 ፤ ርሱም ፡ ሲናገር ፡ ንጉሡ ፦ በእውኑ ፡ አንተ ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪ ፡ ልትኾን ፡ ሾመንኻልን ፧ ተው ፤ ቅጣትን ፡ ስለ ፡
ምን ፡ ትሻለኽ ፧ አለው ። ነቢዩም ፦ ይህን ፡ አድርገኻልና ፥ ምክሬንም ፡ አልሰማኽምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊያጠፋኽ ፡
እንዳሰበ ፡ ዐወቅኹ ፡ ብሎ ፡ ተወ ።

17 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አሜስያስ ፡ ምክር ፡ አደረገና ፦ ና ፥ ርስ ፡ በርሳችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንተያይ ፡ ብሎ ፡
ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወደኢዩ ፡ ልጅ ፡ ወደኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዮአስ ፡ ላከ ።

18 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮስያስ ፦ የሊባኖስ ፡ ኵርንችት ፦ ልጅኽን ፡ ለልጄ ፡ ሚስት ፡ አድርገኽ ፡ስጠው ፡ ብሎ ፡
ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ላከ ፤ የሊባኖስም ፡ አውሬ ፡ ዐልፎ ፡ ኵርንችቱን ፡ ረገጠ ።

19 ፤ አንተም ፦ እንሆ ፥ ኤዶምያስን ፡ መትቻለኹ ፡ ብለኽ ፡ ኰርተኻል ፤ በቤትኽ ፡ ተቀመጥ ፤ አንተ ፡ ከይሁዳ ፡ ጋራ ፡
ትወድቅ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ መከራን ፡ ትሻለኽ ፧ ብሎ ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሜስያስ ፡ ላከ ።

20 ፤ የኤዶምያስንም ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ፈለጉ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ፈቃድ ፡ ነበረና ፡ አሜስያስ ፡ አልሰማም ።

21 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአስ ፡ ወጣ ፤ ርሱና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ አሜስያስም ፡ በይሁዳ ፡ ባለች ፡ በቤትሳሚስ ፡
ላይ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተያዩ ።

22 ፤ ይሁዳም ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ ተመታ ፥ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሸ ።

23 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአስ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የአካዝያስን ፡ ልጅ ፡ የኢዮአስን ፡ ልጅ ፡ አሜስያስን ፡
በቤትሳሚስ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አመጣው ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ ከኤፍሬም ፡ በር ፡ ዠምሮ ፡ እስከማእዘኑ ፡
በር ፡ ድረስ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አፈረሰ ።

24 ፤ ወርቁንና ፡ ብሩን ፡ ኹሉ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ከዖቤድኤዶም ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ዕቃዎች ፡



www.ethiopianorthodox.org

ኹሉ ፥ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፥ በመያዣ ፡ የተያዙትንም ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ተመለሰ ።

25 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ አሜስያስ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮአስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ።

26 ፤ የቀረውም ፡ የፊተኛውና ፡ የኋላኛው ፡ የአሜስያስ ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፨

27 ፤ አሜስያስም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ከራቀ ፡ በኋላ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የዐመፅ ፡ መሐላ ፡ አደረጉበት ፥ ወደ ፡ ለኪሶም ፡ ኰበለለ ፤ በስተኋላውም ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ላኩ ፥ በዚያም ፡ ገደሉት ።

28 ፤ በፈረስም ፡ ጭነው ፡ አመጡት ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ቀበሩት ።

____________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 26 ።

1 ፤ የይሁዳም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ የነበረውን ፡ ዖዝያንን ፡ ወስደው ፡ በአባቱ ፡ በአሜስያስ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡት ።

2 ፤ ንጉሡም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ካንቀላፋ ፡ በኋላ ፡ ዖዝያን ፡ ኤላትን ፡ ሠራ ፥ ወደ ፡ ይሁዳም ፡ መለሳት ።

3 ፤ ዖዝያንም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ይኮልያ ፡ የተባለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

4 ፤ አባቱም ፡ አሜስያስ ፡ እንዳደረገው ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

5 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ መፍራት ፡ ባስተማረ ፡ በዘካርያስ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ልብ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነገሩን ፡ አከናወነለት ።

6 ፤ ወጥቶም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፥ የጌትንና ፡ የየብናን ፡ የአዞጦንንም ፡ ቅጥር ፡ አፈረሰ ፤ በአዛጦንና ፡ በፍልስጥኤማውያንም ፡ አገር ፡ ከተማዎችን ፡ ሠራ ።

7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በፍልስጥኤማውያንና ፡ በጕርበዓል ፡ በሚኖሩ ፡ ዐረባውያን ፡ በምዑናውያንም ፡ ላይ ፡ ረዳው ።

8 ፤ አሞናውያንም ፡ ለዖዝያን ፡ ገበሩ ፤ እጅግም ፡ በርትቶ ፡ ነበርና ፥ ዝናው ፡ እስከግብጽ ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ተሰማ ።

9 ፤ ዖዝያንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በማእዘኑ ፡ በርና ፡ በሸለቆው ፡ በር ፡ ቅጥሩም ፡ በዞረበት ፡ ማእዘን ፡ አጠገብ ፡ ግንቦችን ፡ ሠርቶ ፡ መሸጋቸው ።

10 ፤ ብዙም ፡ እንስሳዎች ፡ ነበሩበትና ፡ በምድረ ፡ በዳና ፡ በቈላው ፡ በደጋውም ፡ ግንብ ፡ ሠራ ፥ ብዙ ፡ ጕድጓድም ፡ ማሰ ፤ ደግሞም ፡ ዕርሻ ፡ ይወድ ፡ ነበርና ፥ በተራራማውና ፡ በፍሬያማው ፡ ስፍራ ፡ ዐራሾችና ፡ አትክልተኛዎች ፡ ነበሩት ።

11 ፤ ደግሞም ፡ ለዖዝያን ፡ በሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ሰልፈኛዎች ፡ ነበሩት ፤ በንጉሡ ፡ አለቃ ፡ በሐናንያ ፡ ትእዛዝ ፡ በአለቃው ፡ በመዕሴያና ፡ በጸሓፊው ፡ በይዒኤል ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተቈጠሩ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ በየቍጥራቸው ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።

12 ፤ የአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ የጽኑዓን ፡ ኀያላኑ ፡ ቍጥር ፡ ኹሉ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበረ ።

13 ፤ ንጉሡንም ፡ በጠላቱ ፡ ላይ ፡ ያግዝ ፡ ዘንድ ፥ በታላቅ ፡ ኀይል ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጣ ፥ ከእጃቸው ፡ በታች ፡ የነበረ ፡ ሰራዊት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበረ ።

14 ፤ ዖዝያንም ፡ ለጭፍራው ፡ ኹሉ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፥ ራስ ፡ ቍርና ፡ ጥሩር ፥ ቀስትና ፡ የሚወነጭፉትን ፡ ድንጋይ ፡ አዘጋጀላቸው ።

15 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ በብልኀተኛዎች ፡ እጅ ፡ የተሠሩትን ፥ በግንብና ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ የሚኖሩትን ፥ ፍላጻና ፡ መርግ ፡ የሚወረወርባቸውን ፡ መሣሪያዎች ፡ አደረገ ፤ እስኪበረታም ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በድንቅ ፡ ረድቶታልና ፥ ዝናው ፡ እስከ ፡ ሩቅ ፡ ድረስ ፡ ተሰማ ።

16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በበረታ ፡ ጊዜ ፡ ለጥፋት ፡ ልቡ ፡ ታበየ ፥ አምላኩንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በደለ ፤ ወደ ፡ መቅደስ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ገብቶ ፡ በዕጣን ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ዐጠነ ።

17 ፤ ካህኑም ፡ ዐዛርያስ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ጽኑዓን ፡ የነበሩ ፡ ሰማንያ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡ ተከትለው ፡ ገቡ ።

18 ፤ ንጉሡንም ፡ ዖዝያንን ፡ እየተቃወሙ ፡— ዖዝያን ፡ ሆይ ፥ ዕጣን ፡ ማጠን ፡ የተቀደሱት ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ የካህናቱ ፡
ሹመት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታጥን ፡ ዘንድ ፡ ለአንተ ፡ አይገባኽም ፤ በድለኻልና ፥ ከመቅደሱ ፡
ውጣ ፤ ከአምላክኽም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ክብር ፡ አይኾንልኽም ፡ አሉት ።

19 ፤ ዖዝያንም ፡ ተቈጣ ፤ የሚያጥንበትም ፡ ጥና ፡ በእጁ ፡ ነበረ ፤ ካህናቱንም ፡ በተቈጣ ፡ ጊዜ ፡ በካህናቱ ፡ ፊት ፡
በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በዕጣኑ ፡ መሠዊያ ፡ አጠገብ ፡ ሳለ ፡ በግንባሩ ፡ ላይ ፡ ለምጽ ፡ ታየ ።

20 ፤ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ዐዛርያስ ፡ ካህናቱም ፡ ኹሉ ፡ ተመለከቱት ፥ እንሆም ፥ በግንባሩ ፡ ላይ ፡ ለምጽ ፡
ነበረ ፤ ፈጥነውም ፡ አባረሩት ፥ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀሥፎት ፡ ነበርና ፥ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ቸኰለ ።

21 ፤ ንጉሡም ፡ ዖዝያን ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ለምጻም ፡ ነበረ ፤ ለምጻምም ፡ ኾኖ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡
ተቈርጧልና ፥ በተለየ ፡ ቤት ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ ልጁም ፡ ኢዮአታም ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ኾኖ ፡ በምድሩ ፡ ሕዝብ ፡
ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ።

22 ፤ የቀረውንም ፡ የፊተኛውንና ፡ የኋለኛውን ፡ የዖዝያንን ፡ ነገር ፡ ነቢዩ ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ጽፎታል ።

23 ፤ ዖዝያንም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ ለምጻም ፡ ነው ፡ ብለውም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ በነገሥታቱ ፡ መቃብር ፡
ዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ ኢዮአታም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ምዕራፍ ፡ 27 ።

1 ፤ ኢዮአታምም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡
ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ ኢየሩሳ ፡ ትባል ፡ ነበር ።

2 ፤ አባቱም ፡ ዖዝያን ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡
ግን ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ አልገባም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ ይበድል ፡ ነበር ።

3 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ የላይኛውን ፡ በር ፡ ሠራ ፥ በዖፌልም ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ሠራ ።

4 ፤ በተራራማውም ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ከተማዎችን ፡ ሠራ ፥ በዱር ፡ ሰፍራዎችም ፡ ዐምባዎችንና ፡ ግንቦችን ፡ ሠራ ።

5 ፤ ከዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፡ አሸነፋቸውም ። በዚያም ፡ ዓመት ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡
ብር ፥ ዐሥር ፡ ሺሕም ፡ የቈሬስ ፡ መስፈሪያ ፡ ስንዴ ፥ ዐሥር ፡ ሺሕም ፡ የቈሬስ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡
ሰጡት ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ በኹለተኛውና ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ሰጡት ።

6 ፤ ኢዮአታምም ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መንገዱን ፡ አቅንቷልና ፥ በረታ ።

7 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮአታም ፡ ነገር ፥ ሰልፉም ፡ ኹሉ ፥ ሥራውም ፥ እንሆ ፥ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡
መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

8 ፤ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡
ዓመት ፡ ነገሠ ።

9 ፤ ኢዮአታምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ አካዝ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ምዕራፍ ፡ 28 ።

1 ፤ አካዝ ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡
ነገሠ ፤ እንደ ፡ አባቱም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አላደረገም ።

2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፥ ደግሞም ፡ ለበዓሊም ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎችን ፡


www.ethiopianorthodox.org

ሠራ ።

3 ፤ ደግሞም ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ዐጠነ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንዳሳደዳቸው ፡
እንደ ፡ አሕዛብም ፡ ክፉ ፡ ልማድ ፡ ልጆቹን ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

4 ፤ በኰረብታው ፡ መስገጃዎችና ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ በለመለመውም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

5 ፤ ስለዚህ ፥ አምላኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ፤ ሶርያውያንም ፡ መቱት ፥ ከርሱም ፡
ብዙ ፡ ምርኮኞዎች ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ አመጡ ። ደግሞም ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡
ሰጠው ፤ ርሱም ፡ በታላቅ ፡ አመታት ፡ መታው ።

6 ፤ የአባቶቻቸውንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ነበርና ፥ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ከይሁዳ ፡
መቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ገደለ ፤ ኹሉም ፡ ጽኑዓን ፡ ነበሩ ።

7 ፤ ከኤፍሬምም ፡ ወገን ፡ የነበረው ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ዝክሪ ፡ የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ መዕሴያንና ፡ የቤቱን ፡ አዛዥ ፡
ዐዝሪቃምን ፥ ለንጉሡም ፡ በማዕርግ ፡ ኹለተኛ ፡ የኾነውን ፡ ሕልቃናን ፡ ገደለ ።

8 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሴቶችን ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንም ፡
ማረኩ ፥ እጅግም ፡ ምርኮ ፡ ከነርሱ ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ አገቡ ።

9 ፤ በዚያም ፡ ዖዴድ ፡ የተባለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ የሚመጣውን ፡ ጭፍራ ፡ ሊገናኘው ፡
ወጣ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ እንሆ ፥ የአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሁዳን ፡ ስለ ፡ ተቈጣ ፡ በእጃችኹ ፡
አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥ እናንተም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በሚደርስ ፡ ቍጣ ፡ ገደላችኋቸው ።

10 ፤ አኹንም ፡ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጆች ፡ ባሪያዎች ፡ ኾነው ፡ ይገዙላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ታስባላችኹ ፤ ነገር ፡
ግን ፥ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የበደላችኹት ፡ በደል ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የለምን ፧

11 ፤ አኹንም ፡ ስሙኝ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በላያችኹ ፡ ነዷልና ፥ ከወንድሞቻችኹ ፡ የወሰዳችኋቸውን ፡
ምርኮኞዎች ፡ መልሱ ።

12 ፤ ደግሞም ፡ ከኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ የዮሐናን ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፥ የምሺሌሞትም ፡ ልጅ ፡
በራክያ ፥ የሰሎምም ፡ ልጅ ፡ ይሒዝቅያ ፥ የሐድላይም ፡ ልጅ ፡ ዓሜሳይ ፡ ከሰልፍ ፡ በተመለሱት ፡ ላይ ፡ ተቃወሟቸው ።

13 ፤ ደግሞም ፦ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ በደል ፡ ታመጡብናላችኹና ፥ ኀጢአታችንንና ፡ በደላችንን ፡
ታበዙብናላችኹና ፡ የተማረኩትን ፡ ወደዚህ ፡ አታግቡ ፤ በደላችን ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ የመቅሠፍቱም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡
ላይ ፡ ነውና ፥ አሏቸው ።

14 ፤ ሰልፈኛዎቹም ፡ ምርኮኛዎቹንና ፡ ምርኮውን ፡ በአለቃዎችና ፡ በጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ተዉ ።

15 ፤ በስማቸውም ፡ የተጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ ምርኮኛዎቹን ፡ ወሰዱ ፥ በመካከላቸውም ፡ ዕራቍታቸውን ፡ ለነበሩት ፡
ኹሉ ፡ ከምርኮው ፡ አለበሷቸው ፥ አጐናጸፏቸውም ፥ ጫማም ፡ በእግራቸው ፡
አደረጉላቸው ፥ መገቧቸውም ፥ አጠጧቸውም ፥ ቀቧቸውም ፤ ደካማዎቹንም ፡ ኹሉ ፡ በአህያዎች ፡ ላይ ፡
አስቀመጧቸው ፥ ዘንባባም ፡ ወዳለበት ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ወደ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ አመጧቸው ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡
ተመለሱ ።

16 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ አካዝ ፡ ርዳታ ፡ ፈልጎ ፡ ወደአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ላከ ፤

17 ፤ የኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ ዳግመኛ ፡ መጥተው ፥ ይሁዳንም ፡ መትተው ፡ ብዙ ፡ ምርኮኛ ፡ ወስደው ፡ ነበርና ።

18 ፤ ደግሞም ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ በቈላውና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ባሉት ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡
ነበር ፤ ቤትሳሚስንና ፡ ኤሎንን ፥ ግዴሮትንም ፥ ሦኮንና ፡ መንደሮቿን ፥ ተምናንና ፡ መንደሮቿን ፥ ጊምዞንና ፡
መንደሮቿን ፡ ወስደው ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

19 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ክዷልና ፥ ከርሱም ፡ እጅግ ፡ ርቋልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡
ይሁዳን ፡ አዋረደው ።



www.ethiopianorthodox.org

20 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ቴልጌልቴልፌልሶር ፡ መጥቶ ፡ አስጨነቀው ፡ እንጂ ፡ አልረዳውም ።

21 ፤ አካዝም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከንጉሡና ፡ ከአለቃዎቹም ፡ ቤት ፡ እኩሌታውን ፡ ገፈፈ ፥ ለአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ሰጠ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንዳች ፡ አልተጠቀመበትም ።

22 ፤ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝ ፡ በተጨነቀ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መበደል ፡ አበዛ ።

23 ፤ ለመቱትም ፡ ለደማስቆ ፡ አማልክት ፦ የሶርያን ፡ ነገሥታት ፡ አማልክት ፡ ረድተዋቸዋልና ፥ እኔን ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ፡ እሠዋላቸዋለኹ ፡ ብሎ ፡ ሠዋላቸው ። ነገር ፡ ግን ፥ ለርሱና ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ እንቅፋት ፡ ኾኑ ።

24 ፤ አካዝም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ወስዶ ፡ ሰባበራቸው ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ ቈለፈ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ማእዘን ፡ ኹሉ ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ።

25 ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ያጥን ፡ ዘንድ ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃዎች ፡ አሠራ ፤ የአባቶቹንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቈጣ ።

26 ፤ የቀረውም ፡ ነገርና ፡ ሥራው ፡ ኹሉ ፥ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፥ እንሆ ፥ በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

27 ፤ አካዝም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በከተማዪቱም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቀበሩት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መቃብር ፡ አላገቡትም ፤ ልጁም ፡ ሕዝቅያስ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ምዕራፍ ፡ 29 ።

1 ፤ ሕዝቅያስም ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ መንገሥ ፡ ዠመረ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ አቡ ፡ ትባል ፡ ነበር ።

2 ፤ አባቱም ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

3 ፤ በነገሠም ፡ በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፡ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ደጆች ፡ ከፈተ ፥ ዐደሳቸውም ።

4 ፤ ካህናቱንና ፡ ሌዋውያኑንም ፡ አስመጣ ፥ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ አደባባይም ፡ ሰበሰባቸው ፥

5 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ሌዋውያን ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ ተቀደሱ ፥ የአባቶቻችኹንም ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ቀድሱ ፤ ርኩሱን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከመቅደሱ ፡ አስወግዱ ።

6 ፤ አባቶቻችን ፡ ተላልፈዋል ፥ በአምላካችንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አድርገዋል ፤ ርሱንም ፡ ትተዋል ፥ ፊታቸውንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መኖሪያ ፡ መልሰዋል ፥

7 ፤ ወደ ፡ ርሷም ፡ ዠርባቸውን ፡ አዙረዋል ፤ ደግሞም ፡ የወለሉን ፡ ደጆች ፡ ቈልፈዋል ፥ መብራቶቹንም ፡ አጥፍተዋል ፥ በመቅደሱም ፡ ውስጥ ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አላጠኑም ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አላቀረቡም ።

8 ፤ ስለዚህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ኾነ ፥ በዐይናችኹም ፡ እንደምታዩ ፡ ለድንጋጤና ፡ ለመደነቂያ ፡ ለመዘበቻም ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

9 ፤ እንሆም ፥ ስለዚህ ፡ አባቶቻችን ፡ በሰይፍ ፡ ወደቁ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችንም ፡ ሚስቶቻችንም ፡ ተማረኩ ።

10 ፤ አኹንም ፡ የቍጣው ፡ ጽናት ፡ ከእኛ ፡ እንዲመለስ ፡ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላደርግ ፡ ዘንድ ፡ በልቤ ፡ ዐስቤያለኹ ።

11 ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ በፊቱ ፡ ትቆሙና ፡ ታገለግሉት ፡ ዘንድ ፥ አገልጋዮቹም ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፥ ታጥኑለትም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መርጧችኋልና ፥ ቸል ፡ አትበሉ ።

12 ፤ ሌዋውያኑም ፥ ከቀአት ፡ ልጆች ፡ የዐማሲ ፡ ልጅ ፡ መሐትና ፡ የዐዛርያስ ፡ ልጅ ፡ ኢዮኤል ፥ ከሜራሪም ፡ ልጆች ፡ የዐብዲ ፡ ልጅ ፡ ቂስና ፡ የይሃሌልኤል ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፥ ከጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ የዛማት ፡ ልጅ ፡ ዮአክና ፡ የዮአክ ፡ ልጅ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ዔዴን ፥

13 ፤ 14 ፤ ከኤሊጸፋንም ፡ ልጆች ፡ ሺምሪና ፡ ይዒኤል ፥ ከአሣፍም ፡ ልጆች ፡ ዘካርያስና ፡ መታንያ ፥ ከኤማንም ፡ ልጆች ፡ ይሒኤልና ፡ ሰሜኢ ፥ ከኤዶታምም ፡ ልጆች ፡ ሸማያና ፡ ዑዝኤል ፡ ተነሡ ።

15 ፤ ወንድሞቻቸውንም ፡ ሰብስበው ፡ ተቀደሱ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደመጣው ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ያነጹ ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ።

16 ፤ ካህናቱም ፡ ያነጹት ፡ ዘንድ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ውስጡ ፡ ገቡ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ መቅደስ ፡ ያገኙትን ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ አወጡት ። ሌዋውያንም ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወደ ፡ ቄድሮን ፡ ወንዝ ፡ ጣሉት ።

17 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ይቀደሱ ፡ ዠመር ፥ በዚያውም ፡ ወር ፡ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወለል ፡ ደረሱ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ቀደሱ ፥ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ፈጸሙ ።

18 ፤ ወደ ፡ ውስጥም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ገብተው ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፥ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ መሠዊያና ፡ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፥ የገጹንም ፡ ኅብስት ፡ ገበታና ፡ ዕቃውን ፡ ኹሉ ፡ አንጽተናል ፤

19 ፤ ንጉሡም ፡ አካዝ ፡ ነግሦ ፡ ሳለ ፡ በመተላለፍ ፡ ያረከሰውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ አዘጋጅተናል ፡ ቀድሰናልም ፤ እንሆም ፥ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ኾነዋል ፡ አሉት ።

20 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፡ የከተማዪቱንም ፡ አለቃዎች ፡ ሰበሰበ ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ወጣ ።

21 ፤ ስለ ፡ መንግሥቱና ፡ ስለ ፡ መቅደሱም ፡ ስለ ፡ ይሁዳም ፡ ሰባት ፡ ወይፈኖች ፥ ሰባትም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ሰባትም ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥ ሰባትም ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አመጡ ። የአሮንንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱን ፦ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ አሳርጓቸው ፡ አላቸው ።

22 ፤ ወይፈኖቹንም ፡ ዐረዱ ፥ ካህናቱም ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ረጩት ፤ አውራ ፡ በጎቹንም ፡ ዐረዱ ፥ ደሙንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ረጩት ፤ ጠቦቶቹንም ፡ ዐረዱ ፡ ደሙንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ረጩት ።

23 ፤ የኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾኑትን ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ በንጉሡና ፡ በጉባኤው ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ፥ እጃቸውንም ፡ ጫኑባቸው ፥ ካህናቱም ፡ አረዷቸው ፤

24 ፤ ንጉሡም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ እንዲደረግ ፡ አዞ ፡ ነበርና ፥ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ማስተስረያ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቀረቡ ።

25 ፤ ይህንም ፡ ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢያቱ ፡ እጅ ፡ አዟልና ፥ እንደ ፡ ዳዊትና ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ባለራእይ ፡ እንደ ፡ ጋድ ፥ እንደ ፡ ነቢዩም ፡ እንደ ፡ ናታን ፡ ትእዛዝ ፥ ጸናጽልና ፡ በገና ፡ መሰንቆም ፡ አስይዞ ፡ ሌዋውያንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አቆመ ።

26 ፤ ሌዋውያንም ፡ የዳዊትን ፡ የዜማ ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፥ ካህናቱም ፡ መለከቱን ፡ ይዘው ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

27 ፤ ሕዝቅያስም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያሳርጉ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ የሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ ማረግ ፡ በተዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መዝሙር ፡ ደግሞ ፡ ተዠመረ ፥ መለከቱም ፡ ተነፋ ፥ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የዳዊት ፡ ዜማ ፡ ዕቃ ፡ ተመታ ።

28 ፤ ጉባኤውም ፡ ኹሉ ፡ ሰገዱ ፥ መዘምራኑም ፡ ዘመሩ ፥ መለከተኛዎችም ፡ ነፉ ፤ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ኾነ ።

29 ፤ ማቅረቡንም ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፡ አጐነበሱ ፡ ሰገዱም ።

30 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቅያስና ፡ አለቃዎቹ ፡ ሌዋውያንን ፡ በዳዊትና ፡ በባለራእዩ ፡ በአሣፍ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ አዘዙ ። በደስታም ፡ አመሰገኑ ፥ አጐነበሱም ፡ ሰገዱም ።



www.ethiopianorthodox.org

31 ፤ ሕዝቅያስም ፡— አኹን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀድሳችኋል ፤ ቅረቡ ፥ መሥዋዕቱንና ፡ የምስጋናውን ፡ መሥዋዕት ፡
ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ጉባኤውም ፡ መሥዋዕቱንና ፡ የምስጋናውን ፡ መሥዋዕት ፡
አመጡ ፤ ልባቸውም ፡ የፈቀደ ፡ ዅሉ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አመጡ ።

32 ፤ ጉባኤውም ፡ ያመጡት ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ቍጥር ፡ ሰባ ፡ ወይፈን ፥ መቶም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ኹለት ፡
መቶም ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ ይህ ፡ ዅሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነበረ ።

33 ፤ የተቀደሱትም ፡ ቍጥር ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ በሬዎች ፡ ሦስት ፡ ሺሕም ፡ በጎች ፡ ነበረ ።

34 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ካህናቱ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ለመግፈፍ ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ፤ ስለዚህም ፡ ሌዋውያን ፡ በቅን ፡
ልብ ፡ ከካህናት ፡ ይልቅ ፡ ይቀደሱ ፡ ነበርና ፥ ሥራው ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፥ ካህናቱም ፡ እስኪቀደሱ ፡ ድረስ ፡
ወንድሞቻቸው ፡ ሌዋውያን ፡ ያግዟቸው ፡ ነበር ።

35 ፤ የሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ የደኅንነቱም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፥ ከሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፡
የሚቀርበው ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባን ፥ ብዙ ፡ ነበረ ። እንዲሁም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ተዘጋጀ ።

36 ፤ ሕዝቅያስና ፡ ሕዝቡም ፡ ዅሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፡ ስላዘጋጀው ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ይህም ፡ ነገር ፡
በድንገት ፡ ተደረገ ።

__________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 30 ።

1 ፤ ለእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
እንዲመጡ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ወደ ፡ እስራኤልና ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ዅሉ ፡ ላከ ፥ ደግሞም ፡ ወደ ፡ ኤፍሬምና ፡ ወደ ፡ ምናሴ ፡
ደብዳቤ ፡ ጻፈ ።

2 ፤ 3 ፤ ካህናቱም ፡ በሚበቃ ፡ ቍጥር ፡ ስላልተቀደሱ ፥ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስላልተሰበሰቡ ፡ በጊዜው ፡
ያደርጉት ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉምና ፡ ንጉሡና ፡ አለቃዎቹ ፡ የኢየሩሳሌምም ፡ ጉባኤ ፡ ዅሉ ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ ፋሲካውን ፡
ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ተመካክረው ፡ ነበር ።

4 ፤ ነገሩም ፡ ለንጉሡና ፡ ለጉባኤው ፡ ዅሉ ፡ ዐይን ፡ መልካም ፡ ነበረ ።

5 ፤ እንደ ፡ ተጻፈም ፡ በብዙ ፡ ቍጥር ፡ አላደረጉም ፡ ነበርና ፥ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፋሲካ ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲመጡ ፡ ከቤርሳቤሕ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ ለእስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ዐዋጅ ፡
እንዲነገር ፡ ወሰኑ ።

6 ፤ እንደ ፡ ንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ መልክተኛዎቹ ፡ እንዲህ ፡ የሚለውን ፡ የንጉሡንና ፡ የአለቃዎቹን ፡ ደብዳቤ ፡ ይዘው ፡
ወደ ፡ እስራኤልና ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ዅሉ ፡ ኼዱ ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከአሶር ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡
ወዳመለጠ ፡ ቅሬታችኹ ፡ እንዲመለስ ፡ ወደአብርሃምና ፡ ወደይሥሐቅ ፡ ወደእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ተመለሱ ።

7 ፤ እናንተም ፡ እንደምታዩ ፡ የተፈቱ ፡ እስኪያደርጋቸው ፡ ድረስ ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡
በደሉ ፡ እንደ ፡ አባቶቻችኹና ፡ እንደ ፡ ወንድሞቻችኹ ፡ አትኹኑ ።

8 ፤ አባቶቻችኹም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ አትኹኑ ፤ እጃችኹንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስጡ ፥ ለዘለዓለም ፡
ወደተቀደሰው ፡ ወደ ፡ መቅደሱም ፡ ግቡ ፥ ጽኑ ፡ ቍጣውም ፡ ከእናንተ ፡ እንዲመለስ ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡
አምልኩ ።

9 ፤ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸርና ፡ መሓሪ ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ብትመለሱ ፡ ፊቱን ፡ ከእናንተ ፡ አያዞርምና ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብትመለሱ ፡ ወንድሞቻችኹና ፡ ልጆቻችኹ ፡ በማረኳቸው ፡ ፊት ፡ ምሕረትን ፡
ያገኛሉ ፥ ደግሞም ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ።

10 ፤ መልእክተኛዎቹም ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በኤፍሬምና ፡ በምናሴ ፡ አገር ፡ እስከ ፡ ዛብሎን ፡ ኼዱ ፤ እነዚያ ፡
ግን ፡ በንቀት ፡ ሣቁባቸው ፥ አፌዘባቸውም ።

11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከአሴርና ፡ ከምናሴ ፡ ከዛብሎንም ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነታቸውን ፡ አዋረዱ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡



www.ethiopianorthodox.org

መጡ ።

12 ፤ ደግሞም ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ የኾነውን ፡ የንጉሡንና ፡ የአለቃዎቹን ፡
ትእዛዝ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ኾነ ።

13 ፤ በኹለተኛውም ፡ ወር ፡ የቂጣውን ፡ በዓል ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ የኾነ ፡ ሕዝብ ፡ በኢየሩሳሌም ፡
ተከማቸ ።

14 ፤ ተነሥተውም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩትን ፡ መሠዊያዎችና ፡ ለጣዖታት ፡ የሚያጥኑበትን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡
አስወገዱ ፥ በቄድሮንም ፡ ወንዝ ፡ ጣሉት ።

15 ፤ በኹለተኛውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ፋሲካውን ፡ ዐረዱ ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፡
ዐፈሩ ፥ ተቀደሱም ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አመጡ ።

16 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ሕግ ፡ በሥርዐታቸው ፡ ቆሙ ፤ ካህናቱም ፡ ከሌዋውያን ፡ እጅ ፡
የተቀበሉትን ፡ ደም ፡ ይረጩ ፡ ነበር ።

17 ፤ በጉባኤውም ፡ ያልተቀደሱ ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ስለዚህም ፡ ሌዋውያን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይቀድሷቸው ፡ ዘንድ ፡
ንጹሓን ፡ ላልኾኑት ፡ ኹሉ ፡ ፋሲካውን ፡ ያርዱላቸው ፡ ነበር ።

18 ፤ እንደ ፡ ትእዛዙም ፡ ሳይኾን ፡ ከኤፍሬምና ፡ ከምናሴ ፡ ከይሳኮርና ፡ ከዛብሎንም ፡ ወገን ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ሳይነጹ ፡
ፋሲካውን ፡ በሉ ።

19 ፤ ሕዝቅያስም ፦ ምንም ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ማንጻት ፡ ባይነጻ ፡ የአባቶቹን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመፈለግ ፡
ልቡን ፡ የሚያቀናውን ፡ ኹሉ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበለው ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ጸለየ ።

20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሕዝቅያስን ፡ ሰማው ፥ ሕዝቡንም ፡ ፈወሰ ።

21 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ተገኝተው ፡ የነበሩ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የቂጣውን ፡ በዓል ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡
አደረጉ ፤ ሌዋውያኑና ፡ ካህናቱም ፡ በዜማ ፡ ዕቃ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እየዘመሩ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እግዚአብሔርን ፡
ያመሰግኑ ፡ ነበር ።

22 ፤ ሕዝቅያስም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አገልግሎት ፡ አስተዋዮች ፡ የነበሩትን ፡ ሌዋውያንን ፡ ኹሉ ፡ ያጽናና ፡
ነበር ። የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ እያቀረቡ ፥ የአባቶቻቸውንም ፡ አምላክ ፡ እያመሰገኑ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አደረጉ ።

23 ፤ 24 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ ሺሕ ፡ ወይፈኖችና ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ ለጉባኤው ፡
ሰጥቶ ፡ ነበርና ፥ አለቃዎቹም ፡ ሺሕ ፡ ወይፈኖችና ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ ለጉባኤው ፡ ሰጥተው ፡ ነበርና ፥ ከካህናቱም ፡
እጅግ ፡ ብዙ ፡ ተቀድሰው ፡ ነበርና ፥ ጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡
ተማከሩ ፤ በደስታም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አደረጉ ።

25 ፤ የይሁዳም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፥ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፥ ከእስራኤልም ፡ የመጡ ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፥ ከእስራኤልም ፡ አገር ፡
የመጡትና ፡ በይሁዳ ፡ የኖሩት ፡ እንግዳዎች ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

26 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ኾነ ፤ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከዳዊት ፡ ልጅ ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡
እንደዚህ ፡ ያለ ፡ በዓል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አልተደረገም ፡ ነበር ።

27 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፡ ተነሥተው ፡ ሕዝቡን ፡ ባረኩ ፤ ድምፃቸውም ፡ ተሰማ ፥ ጸሎታቸውም ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡
መኖሪያው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ።

## መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ምዕራፍ ፡ 31 ፤

1 ፤ ይህም ፡ ኹሉ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ የተገኙ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ወደይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ወጥተው ፡ ኹሉን ፡
ፈጽመው ፡ እስኪጠፉቸው ፡ ድረስ ፡ ሐውልቶቹን ፡ ሰባበሩ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንም ፡ ቈረጡ ፥ በይሁዳና ፡
በብንያምም ፡ ኹሉ ፡ ደግሞም ፡ በኤፍሬምና ፡ በምናሴ ፡ የነበሩትን ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃዎችና ፡ መሠዊያዎች ፡



www.ethiopianorthodox.org

አፈረሱ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርስታቸውና ፡ ወደ ፡ ከተማዎቻቸው ፡ ተመለሱ ።

2 ፤ ሕዝቅያስም ፡ የካህናትንና ፡ የሌዋውያንን ፡ ሰሞን ፡ በየክፍላቸውና ፡ በያገልግሎታቸው ፡ አቆመ ፤ በእግዚአብሔር ፡
ቤት ፡ አደባባይ ፡ በሮች ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፥ ያገለግሉም ፡
ዘንድ ፥ ያመሰግኑም ፡ ያከብሩም ፡ ዘንድ ፡ ካህናቱንና ፡ ሌዋውያኑን ፡ አቆመ ።

3 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በጧትና ፡ በማታ ፥ በሰንበታቱም ፥ በመባቻዎቹም ፥ በበዓላትም ፡
ለሚቀርበው ፡ ለሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ንጉሡ ፡ ከገንዘቡ ፡ የሚከፍለውን ፡ ወሰነ ።

4 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ለአገልግሎት ፡ እንዲጸኑ ፡ ለካህናቱና ፡ ለሌዋውያን ፡ ክፍላቸውን ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡
በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ ሕዝብ ፡ አዘዘ ።

5 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ እንዳዘዘ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የእኽሉንና ፡ የወይኑን ፡ ጠጅ ፡ የዘይቱንና ፡
የማሩንም ፥ የዕርሻውንም ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ በኵራት ፡ ሰጡ ፤ የኹሉንም ፡ ዓሥራት ፡ አብዝተው ፡ አቀረቡ ።

6 ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ የሚኖሩ ፡ የእስራኤልና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ የበሬውንና ፡ የበጉን ፡
ዓሥራት ፥ ለአምላካቸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰውን ፡ ዓሥራት ፡ አመጡ ፥ ከምረውም ፡ አኖሩት ።

7 ፤ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ መከመር ፡ ዠመሩ ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ጨረሱ ።

8 ፤ ሕዝቅያስና ፡ አለቃዎቹም ፡ መጥተው ፡ ክምሩን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ሕዝቡን ፡ እስራኤልን ፡ ባረኩ ።

9 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ካህናቱንና ፡ ሌዋውያኑን ፡ ስለ ፡ ክምሩ ፡ ጠየቀ ።

10 ፤ ከሳዶቅም ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ ዋነኛው ፡ ካህን ፡ ዓዛሪያስ ፦ ሕዝቡ ፡ ቍርባኑን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡
ከዠመረ ፡ ወዲህ ፡ በልተናል ፥ ጠግበናልም ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ባርኳልና ፥ ብዙ ፡ ተርፏል ፤ የተረፈውም ፡ ይህ ፡
ክምር ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

11 ፤ ሕዝቅያስም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ጐተራ ፡ ያዘጋጁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ እነርሱም ፡ አዘጋጁ ።

12 ፤ ቍርባኑና ፡ ዓሥራቱን ፡ የተቀደሱትንም ፡ በእምነት ፡ ወደዚያ ፡ አገቡት ። ሌዋዊውም ፡ ኮናንያ ፡
ተሾመባቸው ፥ ወንድሙም ፡ ሰሜኢ ፡ በማዕርግ ፡ ኹለተኛ ፡ ነበረ ፤

13 ፤ በንጉሡም ፡ በሕዝቅያስና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ በዐዛርያስ ፡ ትእዛዝ ፡
ይሒዒል ፥ ዓዛዝያ ፥ ናሖት ፥ ዐሳሄል ፥ ይሬሞት ፥ ዮዛባት ፥ ኤሊኤል ፥ ሰማክያ ፥ መሐት ፥ በናያስ ፥ ከኮናንያና ፡
ከወንድሙ ፡ ከሰሜኢ ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ ነበሩ ።

14 ፤ የሌዋዊውም ፡ የይምና ፡ ልጅ ፡ የምሥራቁ ፡ ደጅ ፡ በረኛ ፡ ቆሬ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መባና ፡ የተቀደሱትን ፡ ነገሮች ፡
እንዲያካፍል ፡ ሕዝቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፈቃድ ፡ ባቀረቡት ፡ ላይ ፡ ተሾመ ።

15 ፤ በካህናቱም ፡ ከተማዎች ፡ ለታላላቆችና ፡ ለታናናሾች ፡ ወንድሞቻቸው ፡ በየሰሞናቸው ፡ ክፍላቸውን ፡ በእምነት ፡
ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ ዔዴን ፥ ሚንያሚን ፥ ኢያሱ ፥ ሸማያ ፥ አማርያ ፥ ሴኬንያ ፡ ከእጁ ፡ በታች ፡ ነበሩ ።

16 ፤ ከሦስትም ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ በየሰሞናቸው ፡ ለሥራቸውና ፡ ለአገልግሎታቸው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡
ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ለሚገቡ ፡ ወንዶች ፡ ኹሉ ፤

17 ፤ በያባቶቻቸውም ፡ ቤት ፡ ለተቈጠሩ ፡ ካህናት ፥ ከኻያ ፡ ዓመትም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ በየሥርዐታቸውና ፡
በየሰሞናቸው ፡ ለተቈጠሩ ፡ ሌዋውያን ፥

18 ፤ በማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ በየትውልዳቸው ፡ ለተቈጠሩ ፡ ለሕፃናታቸውና ፡ ለሚስቶቻቸው ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡
ልጆቻቸውም ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፤ በእምነት ፡ ተቀድሰዋልና ።

19 ፤ በየከተማዪቱም ፡ ኹሉ ፡ በከተማቸው ፡ መሰምሪያዎቹ ፡ ላሉ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ለካህናቱ ፥ ከካህናቱም ፡ ወገን ፡
ላሉ ፡ ወንዶች ፡ ኹሉ ፥ በትውልዳቸውም ፡ ለተቈጠሩ ፡ ሌዋውያን ፡ ኹሉ ፡ ክፍላቸውን ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ በስማቸው ፡
የተጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

20 ፤ ሕዝቅያስም ፡ በይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፤ በአምላኩም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካምንና ፡ ቅንን ፡


www.ethiopianorthodox.org

ነገር ፡ እውነትንም ፡ አደረገ ።

21 ፤ ስለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ በገመረው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ በሕጉና ፡ በትእዛዙም ፥ አምላኩን ፡
ለመፈለግ ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ አደረገው ፥ ተከናወነለትም ።

______________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ። ______________

ምዕራፍ ፡ 32 ።

1 ፤ ከዚህም ፡ ነገርና ፡ ከዚህ ፡ እምነት ፡ በኋላ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡
ገባ ፥ በተመሸጉትም ፡ ከተማዎች ፡ ፊት ፡ ሰፈረ ፥ ሊወስዳቸውም ፡ ዐሰበ ።

2 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ሰናክሬም ፡ እንደ ፡ መጣ ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ ሊወጋ ፡ ፊቱን ፡ እንዳቀና ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥

3 ፤ ከከተማዪቱ ፡ በስተውጭ ፡ ያለውን ፡ የውሃውን ፡ ምንጭ ፡ ይደፍኑ ፡ ዘንድ ፡ ከአለቃዎቹና ፡ ከኀያላኑ ፡ ጋራ ፡
ተማከረ ፤ እነርሱም ፡ ረዱት ።

4 ፤ እጅግም ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፦ የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ መጥተው ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያገኛሉ ፡ ብለው ፡
ምንጩን ፡ ኹሉ ፥ በምድርም ፡ መካከል ፡ ይንዶለዶል ፡ የነበረውን ፡ ወንዝ ፡ ደፈኑ ።

5 ፤ ሰውነቱንም ፡ አጸናና ፥ የፈረሰውንም ፡ ቅጥር ፡ ኹሉ ፡ ጠገነ ፥ በላዩም ፡ ግንብ ፡ ሠራበት ፥ ከርሱም ፡ በስተውጭ ፡
ሌላ ፡ ቅጥር ፡ ሠራ ፤ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ያለችውን ፡ ሚሎን ፡ አጠነከረ ፤ ብዙም ፡ መሣሪያና ፡ ጋሻ ፡ ሠራ ።

6 ፤ የጦር ፡ አለቃዎቹንም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ሾሞ ፥ ኹሉንም ፡ በከተማዪቱ ፡ በር ፡ ወዳለው ፡ አደባባይ ፡ ሰብስቦ ።

7 ፤ ጽኑ ፥ አይዟችኹ ፤ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካለው ፡ ይበልጣልና ፥ ከአሶር ፡ ንጉሥና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡
ካለው ፡ ጭፍራ ፡ ኹሉ ፡ አትፍሩ ፥ አትደንግጡም ።

8 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሥጋ ፡ ክንድ ፡ ነው ፤ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ግን ፡ የሚረዳንና ፡ የሚዋጋልን ፡ አምላካችን ፡
እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አጸናናቸው ። ሕዝቡም ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ቃል ፡ ተጽናና ።

9 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ከሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በለኪሶ ፡ ፊት ፡ ሳለ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ወደ ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወደነበሩ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ላከ ።

10 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተ ፡ በማን ፡ ተማምናችኹ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ምሽግ ፡
ትቀመጣላችኹ ፧

11 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ያድነናል ፡ እያለ ፡ በራብና ፡ በጥም ፡ እንድትሞቱ ፡ አሳልፎ ፡
ይሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፡ የሚያባብላችኹ ፡ ሕዝቅያስ ፡ አይደለምን ፧

12 ፤ ባንድ ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ስገዱ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ ዕጠኑ ፡ እያለ ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ አዞ ፥ የኰረብታው ፡
መስገጃዎቹና ፡ መሠዊያዎቹን ፡ ያፈረሰ ፡ ይህ ፡ ሕዝቅያስ ፡ አይደለምን ፧

13 ፤ እኔና ፡ አባቶቼ ፡ በምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ያደረግነውን ፡ አላወቃችኹምን ፧ የምድርስ ፡ ኹሉ ፡ አሕዛብ ፡
አማልክት ፡ አገራቸውን ፡ ከእጄ ፡ ያድኑ ፡ ዘንድ ፡ በእውኑ ፡ ተቻላቸውን ፧

14 ፤ አምላካችኹስ ፡ ከእጄ ፡ እናንተን ፡ ለማዳን ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ አባቶቼ ፡ ካጠፏቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡
ሕዝቡን ፡ ከእጄ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ የቻለ ፡ ማን ፡ ነው ፧

15 ፤ አኹንም ፡ ሕዝቅያስ ፡ አያስታችኹ ፥ እንዲህም ፡ አያባብላችኹ ፥ አትመኑትም ፤ ከአሕዛብና ፡ ከመንግሥታት ፡
አማልክት ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡን ፡ ከእጄና ፡ ከአባቶቼ ፡ እጅ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ አልቻለም ፤ ይልቁንስ ፡
አምላካችኹ ፡ ከእጄ ፡ ያድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧

16 ፤ ባሪያዎቹም ፡ ደግሞ ፡ በአምላክ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በባሪያው ፡ በሕዝቅያስ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተናገሩ ።

17 ፤ ደግሞም ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመስደብ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ ለመናገር ። የምድር ፡ አሕዛብ ፡
አማልክት ፡ ሕዝባቸውን ፡ ከእጄ ፡ ያድኑ ፡ ዘንድ ፡ እንዳልቻሉ ፥ እንዲሁ ፡ የሕዝቅያስ ፡ አምላክ ፡ ሕዝቡን ፡ ከእጄ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ያድን ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ።

18 ፤ ከተማዪቱንም ፡ እንዲወስዱ ፥ በቅጥር ፡ ላይ ፡ የተቀመጡትን ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሕዝብ ፡ ያስፈሩና ፡ ያስደነግጡ ፡
ዘንድ ፥ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ይጮኹባቸው ፡ ነበር ።

19 ፤ በሰውም ፡ እጅ ፡ በተሠሩ ፡ በምድር ፡ አሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ላይ ፡ እንደሚናገሩ ፡ መጠን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አምላክ ፡
ላይ ፡ ተናገሩ ።

20 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቅያስና ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለዚህ ፡ ጸለዩ ፥ ወደ ፡ ሰማይም ፡ ጮኹ ።

21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላኑንና ፡ መሳፍንቱን ፡ አለቃዎቹንም ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰፈር ፡ እንዲያጠፉ ፡
መልአኩን ፡ሰደደ ። የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ዐፍሮ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ። ወደአምላኩም ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ከወገቡ ፡
የወጡት ፡ ልጆቹ ፡ በዚያ ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉት ።

22 ፤ እንዲሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቅያስንና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ከሰናክሬም ፡ እጅ ፡
ከኹሉም ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ፤ በዙሪያቸውም ፡ ካለው ፡ ኹሉ ፡ አሳረፋቸው ።

23 ፤ ብዙዎቹም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መባ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይመጡ ፡ ነበር ፥ ለይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡
ለሕዝቅያስ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።

24 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሕዝቅያስ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ታመመ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጸለየ ፤ ርሱም ፡
ተናገረው ፥ ምልክትም ፡ ሰጠው ።

25 ፤ ሕዝቅያስ ፡ ግን ፡ እንደተቀበለው ፡ ቸርነት ፡ መጠን ፡ አላደረገም ፥ ልቡም ፡ ኰራ ፤ ስለዚህም ፡ በርሱና ፡ በይሁዳ ፡
በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ ኾነ ።

26 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ስለልቡ ፡ ኵራት ፡ ሰውነቱን ፡ አዋረደ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡
በሕዝቅያስ ፡ ዘመን ፡ አልመጣባቸውም ።

27 ፤ ለሕዝቅያስም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሀብትና ፡ ክብር ፡ ነበረው ፤ ለብርና ፡ ለወርቅም ፥ ለከበረው ፡ ዕንቍና ፡
ለሽቱው ፥ ለጋሻውና ፡ ለከበረው ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ ሠራ ።

28 ፤ ለእኽልና ፡ ለወይን ፡ ጠጅም ፡ ለዘይትም ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፥ ለልዩ ፡ ልዩም ፡ እንስሳ ፡ ጋጥ ፥ ለመንጋዎችም ፡ በረት ፡
ሠራ ።

29 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ጥሪት ፡ ሰጥቶት ፡ ነበርና ፥ ከተማዎችን ፡ ሠራ ፥ ብዙም ፡ የበግና ፡ የላም ፡ መንጋ ፡
ሰበሰበ ።

30 ፤ ይህም ፡ ሕዝቅያስ ፡ የላይኛውን ፡ የግዮንን ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ ደፈነ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡
አቅንቶ ፡ አወረደው ። የሕዝቅያስም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተከናወነ ።

31 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የባቢሎን ፡ መሳፍንት ፡ መልእክተኛዎች ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ ስለተደረገው ፡ ተኣምራት ፡ ይጠይቁት ፡
ዘንድ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በተላኩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈትነውና ፡ በልቡ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ተወው ።

32 ፤ የሕዝቅያስም ፡ የቀረው ፡ ነገር ፥ ቸርነቱም ፥ እንሆ ፥ በዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ ራእይ ፡ በይሁዳና ፡
በእስራኤልም ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

33 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ልጆች ፡ መቃብር ፡ በላይኛው ፡ ክፍል ፡ ቀበሩት ፤ በይሁዳና ፡
በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ በሞቱ ፡ አከበሩት ። ልጁም ፡ ምናሴ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

__________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 33 ።

1 ፤ ምናሴም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐምሳ ፡ ዐምስት ፡
ዓመት ፡ ነገሠ ።

2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንዳወጣቸው ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ያለ ፡ ርኵሰት ፡ በእግዚአብሔር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

3 ፤ አባቱም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ያፈረሳቸውን ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ መልሶ ፡ ሠራ ፤ ለበዓሊምም ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችንም ፡ ተከለ ፥ ለሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ሰገደ ፥ አመለካቸውም ።

4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ስሜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ ባለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መሠዊያዎችን ፡ ሠራ ።

5 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በኹለቱ ፡ አደባባዮች ፡ ላይ ፡ ለሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ መሠዊያዎችን ፡ ሠራ ።

6 ፤ በሄኖምም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ልጆቹን ፡ በእሳት ፡ አሳለፈ ፤ሞራ ፡ ገላጭም ፡ ኾነ ፥ አስማትም ፡ አደረገ ፥ መተተኛም ፡ ነበረ ፥ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችንም ፡ ሰበሰበ ፤ ያስቈጣውም ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

7 ፤ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለዳዊትና ፡ ለልጁ ፡ ለሰሎሞን ፦ በዚህ ፡ ቤት ፡ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ በመረጥኋት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስሜን ፡ ለዘለዓለም ፡ አኖራለኹ ፤ ያዘዝኋቸውንም ፡ ኹሉ ፥ በሙሴ ፡ የተሰጠውን ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ ፍርድንም ፡ ኹሉ ፡ ቢያደርጉ ፡ ቢጠብቁም ፥ ለአባቶቻችኹ ፡ ከሰጠኋት ፡ ምድር ፡ የእስራኤልን ፡ እግር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አላርቅም ፡ ባለበት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሠራውን ፡ የጣዖት ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ አቆመ ።

9 ፤ ምናሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ካጠፋቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ አሳተ ።

10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምናሴንና ፡ ሕዝቡን ፡ ተናገራቸው ፤ ግን ፡ አልሰሙትም ።

11 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ አለቃዎች ፡ አመጣባቸው ፤ ምናሴንም ፡ በዛንጅር ፡ ያዙት ፥ በሰንሰለትም ፡ አስረው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዱት ።

12 ፤ በተጨነቀም ፡ ጊዜ ፡ አምላኩን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈለገ ፥ በአባቶቹም ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ ሰውነቱን ፡ እጅግ ፡ አዋረደ ፥

13 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ጸለየ ፤ ርሱም ፡ ተለመነው ፥ ጸሎቱንም ፡ ሰማው ፥ ወደ ፡ መንግሥቱም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መለሰው ፤ ምናሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቀ ።

14 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ በስተውጭው ፡ ከግዮን ፡ ምዕራብ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ እስከዓሳ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ቅጥር ፡ ሠራ ። በዖፌልም ፡ አዞረበት ፥ እጅግም ፡ ከፍ ፡ አደረገው ፤ በተመሸጉትም ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችን ፡ አኖረ ።

15 ፤ እንግዳዎችንም ፡ አማልክትና ፡ ጣዖቱንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አራቀ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ባለበት ፡ ተራራ ፡ ላይና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሠራቸውን ፡ መሠዊያዎች ፡ ኹሉ ፡ ወስዶ ፡ ከከተማዪቱ ፡ በስተውጭ ፡ ጣላቸው ።

16 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ መሠዊያ ፡ ደግሞ ፡ ዐደሰ ፥ የደኅንነትና ፡ የምስጋናም ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋበት ፤ ይሁዳም ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲያመልኩ ፡ አዘዘ ።

17 ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ገና ፡ በኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋ ፡ ነበር ፤ ቢኾንም ፡ ለአምላኩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

18 ፤ የምናሴም ፡ የቀረው ፡ ነገር ፥ ወደ ፡ አምላኩም ፡ የጸለየው ፡ ጸሎት ፥ በእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የነገሩት ፡ የነቢያት ፡ ቃል ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

19 ፤ ደግሞም ፡ ጸሎቱ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደተለመነው ፥ ኀጢአቱና ፡ መተላለፉ ፡ ኹሉ ፥ ራሱንም ፡ ሳያዋርድ ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃዎችን ፡ የሠራበት ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዱንና ፡ የተቀረጹትንም ፡ ምስሎች ፡ የተከለበት ፡ ስፍራ ፥ እንሆ ፥ በባለራእዩ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

20 ፤ ምናሴም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በቤቱም ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ ዓሞጽ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

21 ፤ ዓሞጽ ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡



www.ethiopianorthodox.org

ነገሠ ።

22 ፤ አባቱም ፡ ምናሴ ፡ እንዳደረገ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ ዓሞጽም ፡ አባቱ ፡ ምናሴ ፡ ለሠራቸው ፡ ለተቀረጹት ፡ ምስሎች ፡ ኹሉ ፡ ሠዋ ፥ አመለካቸውም ።

23 ፤ አባቱም ፡ ምናሴ ፡ ሰውነቱን ፡ እንዳዋረደ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አንዳላዋረደ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ሰውነቱን ፡ አላዋረደም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዓሞጽ ፡ መተላለፉን ፡ እጅግ ፡ አበዛ ።

24 ፤ ባሪያዎቹም ፡ ተማምለው ፡ በቤቱ ፡ ገደሉት ።

25 ፤ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ በንጉሡ ፡ በዓሞጽ ፡ ላይ ፡ የተማማሉትን ፡ ኹሉ ፡ ገደሉ ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ልጁን ፡ ኢዮስያስን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡ ።

______________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 34 ።

1 ፤ ኢዮስያስም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የስምንት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፤ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አላለም ።

3 ፤ በነገሠም ፡ በስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ሳለ ፡ የአባቱን ፡ የዳዊትን ፡ አምላክ ፡ ይፈልግ ፡ ዠመር ፤ በዐሥራ ፡ ኹለተኛውም ፡ ዓመት ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከኰረብታው ፡ መስገጃዎችና ፡ ከማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹ ፥ ከተቀረጹትና ፡ ቀልጠው ፡ ከተሠሩት ፡ ምስሎች ፡ ያነጻ ፡ ዠመር ።

4 ፤ የበዓሊምንም ፡ መሠዊያዎች ፡ በፊቱ ፡ አፈረሱ ፤ በላዩም ፡ የነበሩትን ፡ የፀሓዩን ፡ ምስሎች ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንም ፡ ቈረጠ ፤ የተቀረጹትንና ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎች ፡ ሰባበረ ፥ አደቀቃቸውም ፥ ይሠዉላቸው ፡ በነበሩት ፡ ሰዎች ፡ መቃብርም ፡ ላይ ፡ በተናቸው ።

5 ፤ የካህናታቸውንም ፡ ዐጥንት ፡ በመሠዊያቸው ፡ ላይ ፡ አቃጠለ ፤ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ አነጻ ።

6 ፤ የምናሴንና ፡ የኤፍሬምንም ፡ የስምዖንና ፡ የንፍታሌምንም ፡ ከተማዎች ፥ በዙሪያቸውም ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ እንዲሁ ፡ አነጻ ።

7 ፤ መሠዊያዎቹንም ፡ አፈረሰ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንና ፡ የተቀረጹትን ፡ ምስሎች ፡ አደቀቀ ፥ በእስራኤልም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ የፀሓይን ፡ ምስሎች ፡ ኹሉ ፡ ቈራረጠ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ተመለሰ ።

8 ፤ በነገሠም ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ምድሪቱንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ካነጻ ፡ በ፡ኋላ ፥ የኤዜልያስ ፡ ልጅ ፡ ሳፋን ፥ የከተማዪቱም ፡ አለቃ ፡ መዕሴያ ፥ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የአምላኩን ፡ ቤት ፡ ይጠግኑ ፡ ዘንድ ፡ ሰደዳቸው ።

9 ፤ ወደ ፡ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ወደ ፡ ኬልቅያስ ፡ መጡ ፤ ሌዋውያኑም ፡ በረኞች ፡ ከምናሴና ፡ ከኤፍሬም ፡ ከቀረውም ፡ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፥ ከይሁዳና ፡ ከብንያም ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ከሚኖሩት ፡ የሰበሰቡትን ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የቀረበውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰጡት ።

10 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ በሚሠሩት ፡ ላይ ፡ ለተሾሙት ፡ ሰጡ ፤ እነርሱም ፡ ይጠግኑና ፡ ያድሱ ፡ ዘንድ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለሚሠሩ ፡ ሠራተኛዎች ፡ ሰጡ ።

11 ፤ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ላፈረሱት ፡ ቤት ፡ ሠረገላዎች ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፥ ለማጋጠሚያም ፡ ዕንጨት ፡ የተጠረበውንም ፡ ድንጋይ ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ ለዐናጢዎችና ፡ ለጠራቢዎች ፡ ሰጡ ።

12 ፤ ሰዎቹም ፡ ሥራውን ፡ በመታመን ፡ አደረጉ ፤ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ የተሾሙት ፥ ሥራውንም ፡ የሚያሠሩት ፡ ሌዋውያን ፡ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ኢኤትና ፡ ዐብድዩ ፥ ከቀአትም ፡ ልጆች ፡ ዘካርያስና ፡ ሜሱላም ፡ ነበሩ ። ከሌዋውያንም ፡ ወገን ፡ በዜማ ፡ ዕቃ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፡



www.ethiopianorthodox.org

13 ፤ በተሸካሚዎችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩ ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡ ነበር ፤ ጸሓፊዎቹና ፡ አለቃዎቹም ፡ በረኞዎቹም ፡
ከሌዋውያን ፡ ወገን ፡ ነበሩ ።

14 ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የቀረበውን ፡ ገንዘብ ፡ ባመጡ ፡ ጊዜ ፡ ካህኑ ፡ ኬልቅያስም ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡
የተሰጠውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ አገኘ ።

15 ፤ ኬልቅያስም ፡ ጸሓፊውን ፡ ሳፋንን ፦ የሕጉን ፡ መጽሐፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አግኝቻለኹ ፡ ብሎ ፡
ተናገረው ። ኬልቅያስም ፡ መጽሐፉን ፡ ለሳፋን ፡ ሰጠው ።

16 ፤ ሳፋንም ፡ መጽሐፉን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አመጣ ፤ ለንጉሡም ። ባሪያዎችኽ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡
ያደርጋሉ ፤

17 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ አፈሰሱ ፥ በሥራውም ፡ ላይ ፡ ለተሾሙትና ፡ ለሠራተኞዎቹ ፡ ሰጡ ፡
ብሎ ፡ አወራለት ።

18 ፤ ጸሓፊውም ፡ ሳፋን ፡ ለንጉሡ ፦ ካህኑ ፡ ኬልቅያስ ፡ መጽሐፍ ፡ ሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ሳፋንም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡
አነበበው ።

19 ፤ ንጉሡም ፡ የሕጉን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ።

20 ፤ ንጉሡም ፡ ኬልቅያስን ፥ የሳፋንንም ፡ ልጅ ፡ አኪቃምን ፥ የሚክያስንም ፡ ልጅ ፡ ዐብዶንን ፥ ጸሓፊውንም ፡
ሳፋንን ፥ የንጉሡንም ፡ ብላቴና ፡ ዐሳያን ፦

21 ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ ኹሉ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አባቶቻችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስላልጠበቁ ፥ በላያችን ፡ የነደደ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ እጅግ ፡ ነውና ፥ ኼዳችኹ ፡ ስለተገኘው ፡ የመጽሐፍ ፡ ቃል ፡
ለእኔ ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳም ፡ ለቀሩት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠይቁ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

22 ፤ ኬልቅያስና ፡ እነዚያ ፡ ንጉሥ ፡ ያዘዛቸው ፡ ወደልብስ ፡ ጠባቂው ፡ ወደሐስራ ፡ ልጅ ፡ ወደቲቁዋ ፡ ልጅ ፡ ወደሴሌም ፡
ሚስት ፡ ወደ ፡ ነቢዪቱ ፡ ወደ ፡ ሕልዳና ፡ ኼዱ ፤ ርሷም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በከተማዪቱ ፡ በኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ ተቀምጣ ፡
ነበር ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ ነገሯት ።

23 ፤ ርሷም ፡ አለቻቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ለላካችኹ ፡ ሰው ፡
እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦

24 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ በተነበበው ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፉትን ፡ ቃላት ፡
ኹሉ ፥ ማለት ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፥ በዚህ ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ።

25 ፤ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ሊያስቈጡኝ ፡ ትተውኛልና ፥ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ ዐጥነዋልና ፥ ቍጣዬ ፡ በዚህ ፡
ስፍራ ፡ ይነዷል ፥ አይጠፋምም ።

26 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ለላካችኹ ፡ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለሰማኸው ፡ ቃል ፡ ልብኽ ፡ ገር ፡ ኾኗልና ፥

27 ፤ በፊቴም ፡ ራስኽን ፡ አዋርደኻልና ፥ በዚህም ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ ቃሌን ፡ በሰማኽ ፡ ጊዜ ፡ ራስኽን ፡
አዋርደኻልና ፥ ልብስኽንም ፡ ቀደኽ ፡ በፊቴ ፡ አልቅሰኻልና ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ሰምቻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

28 ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ አባቶችኽ ፡ እሰበስብኻለኹ ፥ በሰላምም ፡ ወደ ፡ መቃብርኽ ፡ ትሰበሰባለኽ ፤ በዚህም ፡ ስፍራና ፡
በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ የማመጣውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ዐይኖችኽ ፡ አያዩም ። ይህንም ፡ ለንጉሥ ፡ አወሩለት ።

29 ፤ ንጉሡም ፡ ላከ ፥ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ።

30 ፤ ንጉሡም ፡ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩና ፡ ካህናቱ ፥ ሌዋውያኑም ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡
ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጡ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡
የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በጆሯቸው ፡ አነበበ ።

31 ፤ ንጉሡም ፡ በስፍራው ፡ ቆሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተከትሎ ፡ እንዲኼድ ፥ ትእዛዙንና ፡ ምስክሩን ፡ ሥርዐቱንም ፡



www.ethiopianorthodox.org

በፍጹም ፡ ልቡና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሱ ፡ እንዲጠብቅ ፥ በዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡
እንዲያደርግ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

32 ፤ በኢየሩሳሌምና ፡ በብንያምም ፡ የተገኙትን ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አማለ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩት ፡
የአባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዳዘዘ ፡ አደረጉ ።

33 ፤ ኢዮስያስም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ርኩሱን ፡ ኹሉ ፡ አስወገደ ፥ በእስራኤልም ፡ የተገኙትን ፡ ኹሉ ፡
አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲያመልኩ ፡ አደረገ ። በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ከመከተል ፡ አልራቁም ።

_________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ። _________________

ምዕራፍ ፡ 35 ።

1 ፤ ኢዮስያስም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ፋሲካ ፡ አደረገ ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡
ቀን ፡ ፋሲካውን ፡ ዐረዱ ።

2 ፤ ካህናቱንም ፡ በየሥርዐታቸውም ፡ አቆመ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ አጸናቸው ።

3 ፤ እስራኤልንም ፡ ኹሉ ፡ ያስተምሩ ፡ ለነበሩት ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ለተቀደሱት ፡ ሌዋውያን ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ቅዱሱን ፡
ታቦት ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሰሎሞን ፡ በሠራው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኑሩት ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡
በትከሻችኹ ፡ ላይ ፡ ሸክም ፡ አይኾንባችኹም ፤ አኹንም ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ሕዝቡን ፡ እስራኤልን ፡
አገልግሉ ፤

4 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ ልጁም ፡ ሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ በየሰሞናችኹና ፡ በያባቶቻችኹ ፡
ቤቶች ፡ ተዘጋጁ ፤

5 ፤ እንደ ፡ ሕዝቡም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ወንድሞቻችኹ ፡ በያባቶች ፡ ቤቶች ፡ ኰናችኹ ፡ በመቅደሱ ፡
ቁሙ ፤ የሌዋውያንም ፡ ነገድ ፡ በየወገናቸው ፡ እንደ ፡ ተከፈሉ ፡ እናንተ ፡ ተከፈሉ ፤ ፋሲካውንም ፡ ዕረዱ ፥

6 ፤ እናንተም ፡ ተቀደሱ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለወንድሞቻችኹ ፡
አዘጋጁ ።

7 ፤ ኢዮስያስም ፡ ለፋሲካው ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲኾን ፡ በዚያ ፡ ለነበሩት ፡ ለሕዝቡ ፡ ልጆች ፡ ከመንጋው ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡
የበግና ፡ የፍየል ፡ ጠቦቶች ፥ ሦስት ፡ ሺሕም ፡ ወይፈኖች ፡ ሰጣቸው ፤ እነዚህም ፡ ከንጉሡ ፡ ሀብት ፡ ነበሩ ።

8 ፤ መሳፍንቱም ፡ ለሕዝቡና ፡ ለካህናቱ ፡ ለሌዋውያኑም ፡ በፈቃዳቸው ፡ ሰጡ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡
አለቃዎች ፥ ኬልቅያስ ፥ ዘካርያስ ፥ ይሒኤል ፥ ለፋሲካው ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲኾን ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡
በጎችና ፡ ፍየሎች ፥ ሦስት ፡ መቶም ፡ በሬዎች ፡ ለካህናቱ ፡ ሰጡ ።

9 ፤ የሌዋውያኑም ፡ አለቃዎች ፡ ኮናንያ ፥ ወንድሞቹም ፡ ሸማያና ፡ ናትናኤል ፥ ሐሸቢያ ፥ ይዒኤል ፥ ዮዛባት ፡ ለፋሲካው ፡
መሥዋዕት ፡ እንዲኾን ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ በጎችና ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ መቶም ፡ በሬዎች ፡ ለሌዋውያን ፡ ሰጡ ።

10 ፤ አገልግሎቱም ፡ ተዘጋጀ ፥ ካህናቱም ፡ በስፍራቸው ፥ ሌዋውያኑም ፡ በየክፍላቸው ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ትእዛዝ ፡
ቆሙ ።

11 ፤ ፋሲካውንም ፡ ዐረዱ ፥ ሌዋውያኑም ፡ ቍርበቱን ፡ ገፈፉ ፥ ካህናቱም ፡ ከእጃቸው ፡ የተቀበሉትን ፡ ደም ፡ ረጩ ።

12 ፤ በሙሴም ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ለሕዝቡ ፡
ልጆች ፡ እንዲሰጡ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ለዩ ። እንዲሁም ፡ በበሬዎቹ ፡ አደረጉ ።

13 ፤ ፋሲካውንም ፡ እንደ ፡ ሥርዐቱ ፡ በእሳት ፡ ጠበሱ ፤ የተቀደሰውንም ፡ ቍርባን ፡ በምንቸትና ፡ በሰታቴ ፡ በድስትም ፡
ቀቀሉ ፥ ለሕዝቡም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ በፍጥነት ፡ አደረሱ ።

14 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለራሳቸውና ፡ ለካህናቱ ፡ አዘጋጁ ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡
ስቡን ፡ ለማቅረብ ፡ እስከ ፡ ሌሊት ፡ ድረስ ፡ ይሠሩ ፡ ነበርና ፥ ስለዚህ ፡ ሌዋውያን ፡ ለራሳቸውና ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡



www.ethiopianorthodox.org

ለካህናቱ ፡ አዘጋጁ ።

15 ፤ የአሣፍም ፡ ልጆች ፡ መዘምራን ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፥ እንደ ፡ አሣፍም ፡ እንደ ፡ ኤማንም ፡ የንጉሡም ፡ ባለራእይ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንደ ፡ ኤዶታም ፡ ትእዛዝ ፡ በየስፍራቸው ፡ ነበሩ ፤ በረኞዎቹም ፡ በሮቹን ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ ሌዋውያን ፡ ያዘጋጁላቸው ፡ ነበርና ፥ ከአገልግሎታቸው ፡ ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ አያስፈልጋቸውም ፡ ነበር ።

16 ፤ እንደ ፡ ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ኢዮስያስ ፡ ትእዛዝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፥ ፋሲካውንም ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልግሎት ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ተዘጋጀ ።

17 ፤ የተገኙትም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ፋሲካውን ፥ ሰባት ፡ ቀንም ፡ የቂጣ ፡ በዓልን ፡ አደረጉ ።

18 ፤ ከነቢዩ ፡ ከሳሙኤል ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ፋሲካ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ አልተደረገም ፤ ከእስራኤልም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ኢዮስያስና ፡ ካህናቱ ፥ ሌዋውያኑም ፥ በዚያም ፡ የተገኙ ፡ የይሁዳና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩት ፡ እንዳደረጉት ፡ ያለ ፡ ፋሲካ ፡ ያደረገ ፡ የለም ።

19 ፤ ይህም ፡ ፋሲካ ፡ ኢዮስያስ ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ተደረገ ።

20 ፤ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ በኋላ ፥ ኢዮስያስም ፡ ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ ካሰናዳ ፡ በኋላ ፥ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ኒካዑ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በከርከሚሽ ፡ ላይ ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፤ ኢዮስያስም ፡ ሊጋጠመው ፡ ወጣ ።

21 ፤ ርሱም ፦ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፤ በምዋጋበት ፡ በሌላ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ አልመጣኹም ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንድቸኵል ፡ አዞኛል ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳያጠፋኽ ፡ ይህን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ከማድረግ ፡ ተመለስ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኛዎችን ፡ ላከበት ።

22 ፤ ኢዮስያስ ፡ ግን ፡ ይዋጋው ፡ ዘንድ ፡ ተጸናና ፡ እንጂ ፡ ፊቱን ፡ ከርሱ ፡ አልመለሰም ፤ በእግዚአብሔርም ፡ አፍ ፡ የተነገረውን ፡ የኒካዑን ፡ ቃል ፡ አልሰማም ፥ በመጊዶም ፡ ሸለቆ ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ መጣ ።

23 ፤ ቀስተኛዎችም ፡ ንጉሡን ፡ ኢዮስያስን ፡ ወጉት ፤ ንጉሡም ፡ ብላቴናዎቹን ፦ አጥብቄ ፡ ቈስያለኹና ፡ ከሰልፉ ፡ ውስጥ ፡ አውጡኝ ፡ አላቸው ።

24 ፤ ብላቴናዎቹም ፡ ከሠረገላው ፡ አውርደው ፡ ለርሱ ፡ በነበረው ፡ በኹለተኛው ፡ ሠረገላ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጡት ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ አመጡት ፤ ርሱም ፡ ሞተ ፥ በአባቶቹም ፡ መቃብር ፡ ተቀበረ ፤ ይሁዳና ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ኹሉ ፡ ለኢዮስያስ ፡ አለቀሱ ።

25 ፤ ኤርምያስም ፡ ለኢዮስያስ ፡ የልቅሶ ፡ ግጥም ፡ ገጠመለት ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ መዘምራን ፡ ኹሉ ፡ በልቅሶ ፡ ግጥማቸው ፡ ስለ ፡ ኢዮስያስ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ወግ ፡ ኾኖ ፡ በልቅሶ ፡ ግጥም ፡ ተጽፏል ።

26 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮስያስ ፡ ነገር ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ አንደ ፡ ተጻፈ ፡ ያደረገው ፡ ቸርነት ፥

27 ፤ የፊተኛውና ፡ የኋለኛውም ፡ ነገሩ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

____________________መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ። ____________________

ምዕራፍ ፡ 36 ።

1 ፤ የአገሩም ፡ ሰዎች ፡ የኢዮስያስን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአክስን ፡ ወስደው ፡ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አነገሡት ።

2 ፤ ኢዮአክስም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ።

3 ፤ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከመንግሥቱ ፡ አወጣው ፥ መቶም ፡ መክሊት ፡ ብርና ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ዕዳ ፡ ጣለበት ።

4 ፤ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ወንድሙን ፡ ኤልያቄምን ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አነገሠ ፥ ስሙንም ፡ ኢዮአቄም ፡ ብሎ ፡ ለወጠ ፤ ኒካዑም ፡ ወንድሙን ፡ ኢዮአክስን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወሰደው ።



www.ethiopianorthodox.org

5 ፤ ኢዮአቄምም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡
አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ በአምላኩም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

6 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ይወስደው ፡ ዘንድ ፡ በሰንሰለት ፡
አሰረው ።

7 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ዐያሌውን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ አፈለሰ ፥ በባቢሎንም ፡ በመቅደሱ ፡
ውስጥ ፡ አኖረው ።

8 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮአቄም ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ርኵሰት ፥ በርሱም ፡ የተገኘው ፡ ኹሉ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤልና ፡
በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ፤ ልጁም ፡ ዮአኪን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

9 ፤ ዮአኪንም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡
ወርና ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ነገሠ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

10 ፤ ዓመቱ ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ልኮ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰደው ፥ የከበረውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቤት ፡ ዕቃ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አስወሰደ ፤ ወንድሙንም ፡ ሴዴቅያስን ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አነገሠ ።

11 ፤ ሴዴቅያስ ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡
ዓመት ፡ ነገሠ ።

12 ፤ በአምላኩም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ አፍ ፡ በተናገረው ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡
ፊት ፡ ራሱን ፡ አላወረደም ።

13 ፤ ደግሞም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምሎት ፡ በነበረው ፡ በንጉሡ ፡ በናቡከደነጾር ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ፤ ወደእስራኤልም ፡
አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይመለስ ፡ ዐንገቱን ፡ አደነደነ ፡ ልቡንም ፡ አጠነከረ ።

14 ፤ ደግሞም ፡ የካህናቱ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡም ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ያለ ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ መተላለፍን ፡
አበዙ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የቀደሰውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አረከሱ ።

15 ፤ የአባቶቻቸውም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡና ፡ ለማደሪያው ፡ ስላዘነ ፡ ማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡ በመልእክተኛዎቹ ፡
እጅ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ይልክ ፡ ነበር ።

16 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፥ ፈውስም ፡ እስከማይገኝላቸው ፡
ድረስ ፥ በእግዚአብሔር ፡ መልእክተኛዎች ፡ ይሣለቁ ፥ ቃሉንም ፡ ያቃልሉ ፥ በነቢያቱም ፡ ላይ ፡ ያፌዙ ፡ ነበር ።

17 ፤ ስለዚህም ፡ የከለዳውያንን ፡ ንጉሥ ፡ አመጣባቸው ፤ ርሱም ፡ ጕልማሳዎቻቸውን ፡ በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡
በሰይፍ ፡ ገደላቸው ፤ ጕልማሳውንና ፡ ቈንጆዪቱን ፡ ሽማግሌውንና ፡ አሮጌውን ፡ አልማረም ፤ ኹሉንም ፡ በእጁ ፡
አሳልፎ ፡ ሰጠው ።

18 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ታላቁንና ፡ ታናሹን ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፥ የንጉሡንና ፡
የአለቃዎቹን ፡ መዝገብ ፥ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰደ ።

19 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ አቃጠሉ ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ አፈረሱ ፥ አዳራሾቿንም ፡ በእሳት ፡
አቃጠሉ ፥ መልካሙንም ፡ ዕቃዋን ፡ ኹሉ ፡ አጠፉ ።

20 ፤ ከሰይፍም ፡ ያመለጡትን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማረካቸው ፤ የፋርስ ፡ ንጉሥም ፡ እስኪነግሥ ፡ ድረስ ፡ ለንጉሡና ፡
ለልጆቹ ፡ ባሪያዎች ፡ ኾኑ ፤

21 ፤ በኤርምያስም ፡ አፍ ፡ የተነገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲፈጸም ፥ ምድሪቱ ፡ ሰንበትን ፡ በማድረጓ ፡
እስክታርፍ ፡ ድረስ ፤ በተፈታችበትም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ ሰባ ፡ ዓመት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፥ ሰንበትን ፡ አገኘች ።

22 ፤ በኤርምያስም ፡ አፍ ፡ የተነገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ በፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ በቂሮስ ፡
በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔር ፡ የፋርስን ፡ ንጉሥ ፡ የቂሮስን ፡ መንፈስ ፡ አስነሣ ፤ ርሱም ፦ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡
ቂሮስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦



www.ethiopianorthodox.org

23 ፤ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የምድርን ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ሰጥቶኛል ፤ በይሁዳም ፡ ባለችው ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ቤት ፡ እሠራለት ፡ ዘንድ ፡ አዞኛል ፤ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፡ አምላኩ ፡
እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፥ ርሱም ፡ ይውጣ ፡ ብሎ ፡ በመንግሥቱ ፡ ኹሉ ፡ ዐዋጅ ፡ አስነገረ ፥ ደግሞም ፡
በጽሕፈት ፡ አደረገው ፨



www.ethiopianorthodox.org